እግዚአብሔር ከገና አባት ይለያል!!

(አሌክስ አብርሃም)

‹‹እግዚአብሔር መልካም ነው ....›› ማለት ሁልጊዜ ይሰጣል ማለት ብቻ አይደለም ... ሊወስድም ይችላል ..... የሰጠህን መርፌ ሳይቀር ሊመነጥቅህና መለመላህን ከውርደት ጋር ሊያቆምህ ፍርዱ በእጁ ነው .... እና ሲሰጥም ሲወስድም እግዚአብሔር መልካም ነው !! ብልጣብልጥ ስብከት ብቻ ሲበዛ ይሰለቻል !

እግዚአብሄር ለተራቡ ህዝቦች ከሰማይ መናን አውርዷል ...ለተጨማለቁበት ህዝቦች እሳትም ከሰማይ አውርዷል ! በስሙ ውስጥ ፍቅር የሚያክል እሳት አለ ! ቸር ነው መሃሪ ነው አዛኝ ነው ሩህሩህ ነው ....እናም ቸርነቱ መሃሪነቱ አዛኝነቱ ማንንም የሚያባብልበት የሚለማመጥበት እጅ መንሻ አይደለም ....

እንደው አንዳንዱ ስብከት ያበሳጫል ... እግዚአብሔር ልብስ ይጣችኋል ... እንጀራ በዶሮ ወጥ ይሰጣችኋል ... ስኒከር ጫማ ይሰጣችኋል .... አያልነሽ የምትባል ቆንጆ ሚስት ይሰጣችኋል ...ምን የሚሉት ቀልድ ነው..... ሰባኪ ቃሉን ማስተላለፍ እንጅ ቃሉን መምረጥና በጎ በጎውን መናገር ሲጀምር ህዝብ እግዚአብሔርን እንደታላቅ ወንድሙ እያየ ሲዘባነን ያበሽቃል !

በቃ እግዚአብሔርን የገና አባት አድርገው እየሳሉብን ከረጢቱን በስጦታ ብቻ ሞልቶ የሚንሳፈለል ሽማግሌ አድርገን አጉል መሳፈጥ አበዛን ..... ሹገር ዳዲዋ የሰጣት አቶዝ መስተዋት ላይ ‹‹እግዚአብሔር መልካም ነው ›› ብላ ትገጠግጠዋለች ! እዚህ እንትና የስንቱን ደሃ መሬት ቸብችቦ የገዛው ገልባጭ መኪና መስተዋት ላይ ... ‹‹መልካም በረከት ከላይ ነው ››የሚል ጥቅስም ለጥፎ ‹‹አሚን ›› እንድንል የሚነዘንዘን ሌባ አለ !

እንግዲህ ትድኑ ዘንድ ልጁን ሰጣችሁ ሲባል አሚን ለማለት የፈዘዘ ምእመን ‹‹እግዜር ባለ አስራሁለት ወንበር ሚኒባስ ይሰጣሃል ›› ሲባል ሰማይ እና ምድር እስኪናወጥ እልል ካለ .... ስለግዜር ሳይሆን ስለ 81 00 ንገሩት ...አገሩንም ጠቅሞ እድሉ ካለ ሚኒባሱን ይውሰድ !! እግዚአብሔር ግን ከፍቅር በመነጨ ፍርሃትና መንቀጥቀጥ ሊመለክ ሊከበርም የሚገባው አምላክ ነው !!

ዘና በል ብሎኛል እያልን መረን በለቀቀ ዘነዘና ስብከታችን ትውልዱን በጥቅም መንፈስ አንውቀጥ !! አደረገም አላደረገም እግዚአብሔር እግዚአብሔር ነው !! ደግሞ ከቃሉ ዝንፍ አይልም ...ሲኦል እንደሚያስገባ ያስቀመጠውን ግልፅ ሃሢያት ከፈፀምን .... የእግዜር ከረጢት ...መኪና ቤት መልካም ሚስትና ባል ቆንጆ ልጆችብቻአይደለም የቋጠረችው !! ሰምታችኋል !!

እማማ አረግየ ስዊት ለምን ብሎክ አደረጉኝ ?

(አሌክስ አብርሃም)

የሆነ ጊዜ ‹‹እገዛላታለሁ›› የምትለዋን አጭር ልብ ወለድ ፅፌ የለጠፍኩ ሰሞን ከአንዲት ልጅ መልእክት ተላከልኝ ....
‹‹ ሃይ ...አያቴ ጓደኛህ ልትሆን ስለምትፈልግ ጠይቂልኝ ብላኝ ነው ትቀበላታለህ ? ›› መልእክቱን የላከችልኝ ልጅ ቆንጆ ወጣት ነበረች ቢበዛ አስራ ስምንት አመት ቢሆናት ነው

‹‹ አንችስ ጓደኛየ አትሆኝም ›› ማለት ቃጥቶኝ ነበር ! ግን ጥያቄዋ ገርሞኝ ‹‹ምን ችግር አለው ›› አልኩና ‹‹ ማነው ስማቸው›› ስል ጥያቄ አስከተልኩ !እስካሁን አያት የሚሆኑ ሴትዮ ጋር ጓደኛ ስላልሆንኩ ምን ፌስቡክ ጣላቸው ብየ ገርሞኛል !

‹‹የፌስቡክ አካውንት ገና ልከፍትላት ነው ባክህ የሆነ የለጠፍከውን ረዥ....ም ነገር ሰው አንብቦላት ነው ሁልጊዜ የሚጥፈውን እንዲልክልኝ ይሄ የሚከፈተውን ነገር ክፈችልኝ እና አገናኝኝ ምናመን ብላኝ ነው ›› ትለኛለች ልጅቱ ...አነጋገሯ ሁሉ ለአያቷ ስትል እንጅ እኔን ማውራት እንደደበራት ታስታውቃለች !

‹‹ክፈችላቸዋ ታዲያ ምን ችግር አለው ›› ከፈተችላቸው !

‹‹አረጋየ ስዊት›› ስማቸው አረጋሽ ነው .... ጓደኛ ሆንን!!
‹‹አረግየ ስዊት›› እድሚያቸው አምሳ አምስት ይሆናል.... የሚኖሩት ልጆቻቸው እና የልጅ ልጆቻቸው ጋር አውሮፓ ሲሆን ደስ የሚሉ ተጫዋች ሴትዮ ናቸው ! የልጃቸው ልጅ ደግሞ ቀልቧ አልወደደኝም ! የክፋቱ ክፋት አረግየ ማንበብም መፃፍም አይችሉም ! ይች ነጃሳ የልጅ ልጃቸው ናት እኔ የምፅፈውን እየተረጎመች ለእርሳቸው እርሳቸው የሚናገሩትን እየፃፈች ለእኔ የምታቀብለኝ ! እማማ አረግየ ስዊት ጋር በኢንቦክስ ሁሉ እንደጉድ በዚች ልጅ አስተርጓሚነት እናወራለን !

‹‹ እኔ የምለዎት እትየ አረጋሽ ደም ... ብዛቷ እንዴት ነች ተሸለዎት ›› ብየ እፅፋለሁ .....አስተርገዋሚያችን በብስጭት
‹‹ ደም ብዛት አይባልም ደም ግፊት በል ባክህ ... አንተ ፀሃፊ ነኝ ትል የለ እንዴ በሽታ እንኳን በትክክለኛ ስሙ አትጠራም ›› ብላኝ ትነጫነጭና ለ አረግየ ስዊት አስተካክላ ትነግርልኛለች !

‹‹አቡችየ የኔ ልጅ ደህና ነኝ እግዜር ይባርክህ ጠያቂ አያሳጣህ .... አንተስ ደህና ነህ እናትህስ ደህናና ናት ....ስራው ሁሉ ›› አስተርጓሚያችን በምሬት እንዲህ ትለኛለች

‹‹ በናትህ አሌክስ በይፍሬንዴ አየጠበቀኝ ነው ቶሎ ቻው በላት ማታ ምናምን ታወራላችሁ ›› ሳስበው አያቷ ‹አረግየ ስዊት› የማያፈናፍኑ ሃይለኛ ሴት ነገር ናቸው ...
‹‹ በይ ፍሬንድ አለሽ እንዴ ?›› እላታለሁ አረግየን ትቻቸው
‹‹እሱ አይመለከትህም ዝም ብለህ እሷ ጋር አውራ ምን ልበልልህ ...?.››

ትንሽ ላበሳጫት እፈልግና ‹‹ አንድ አራት ገፅ የሚሆን ቆንጆ ታሪክ ከአስር ደይቃ በኋላ ስለምለጥፍ እንዳያመልጠወት... ስለባልና ሚስት ነው ....ባልየው በሚስቲቱ ላይ ሌላ ሴት ይዞ ሲኖር ሲኖር ሲኖር ..... በይልኝ ›› እላታለሁ
‹‹አር ዩ ክሬዚ . . . ? እዚህ ተቀምጬ ያንተን ተረት ሳነብ አልውልም እሽ ገደል ግባ ...ኦ ጋድ ...ሲኖር ሲኖር ..ባል ምናምን ...›› ስትንጨረጨር ደስ ይለኛል !

‹‹አይ እንግዲህ አርፈሽ አስተርጉሚ ካልሆነ አስራ አምስት ገፅ ግጥም ለጥፌ ታስረሽ ትውያታለሽ ! ›› ግጥም ከምታነብ ራሷን ብታጠፋ እንደምትመርጥ አውቃለሁ !

‹‹ኦኬ አሌክስ . . . እሽ በፀባይ እንግባባ .....በሃያ ሰባት አመትህ ረዥም ተረት ላንተም ጥሩ አይደለም ....ኧረ ላይፍን ቀለል አድርጋት ....ኦ ጋድ ! ዋክ ምናምን አድርግ ፓርቲ ከጓደኞችህ ጋ ውጣ ኢትዮጲያ ውስጥ ፓርቲ አለ አይደል ...?.››

‹‹ እንዴታ ...አድነት... ቅንጅት ...አረና ..... እ....ይሄ ማነው ደግሞ ምርጫ ሲደርስ ቢሮውን ቀለም የሚያስቀባው .....››

‹‹ታዲያ አንድኛቸው ጋ ሂደህ ለምን አትጨፍርም.. አም ሹር አሪፍ አሪፍ ዲጀዎች አሏቸው .....››

‹‹አንች ልጅ አረግየን ረሳሻቸው እኮ ›› እላታላሁ እንደው የትውልዱ አራምባና ቆቦነት እየገረመኝ ....

‹‹ባክህ እሷ አሁንም ስለጤንነትህ እየጠየቀች ነው.... ገና ሰላምታ ላይ ነች ....አንድ አይነት እኮ ናችሁ ›› ለእኔ የራሷን ንጭንጭ ስትፅፍ አረገየ የሚሏትን የምትፅፍ ስለሚመስላቸው ዝም ብለው ያወሯታል ‹‹ ጎረቤቱ ሁሉ ሰላም ነው . . . ዝናብስ እየጣለ ነው ...የኢትዮጲያ ሰላም ናት ? እዚህ በየቀኑ ልጆቹ ሰልፍ ነው የሚውሉት ... አለቁ ታሰሩ

ነው የምንሰማው ..... እንደው ስንት ሰው ቀራችሁ ? ››

‹‹ አሳሪወቹን ጨምሮ ዘጠና ሚሊየን ቀርተናል ! ››

‹‹ አየሩስ እንዴት ነው ....ብርድ እንዳይመታህ ደህና ነገር ደርብ ....ቡሉኮ ደሞ ጥሩ ነው ....ብሉኮ አለህ ለመሆኑ ? ... እዛ ቃሊቲ እስር ቤት የሚሸመን እንዴት ያለ ብሉኮ አለ መሰለህ ...ገዝተው ባለፈው ሀዳር ሚካኤል ልከውልኝ እዚህ ቀዝቀዝ ሲል እደርበዋለሁ..መቸም ጦቢያ ሁኖ የታሰረ ዘመድ ባይሆን ጓደኛ የሌለው አይጠፋም ... ልትጠይቅ ስትሄድ እግረ መንገድህን ቆንጆ ብልኮ ጋቢ ግዛ ! ...አቡቹየ አደራ ባይሆን በሽብር ተጠርጥሮ የታሰረ እስረኛ የሰራውን ጋቢ እንዳትገዛ....መምጫቸው አይታወቅም ... ነገር ካማራቸው መሃሉ ላይ ኮኩብ የሌለው ቡልኮ ለበሰ ብለው ክስ ይመሰርቱበሃል ! ›› ... ንፋስ እንዳይመታህ አቡቹ ›› ይላሉ ...

ልጅቱ ስታብድ እየታየኝ ሳቄን አፍኜ
‹‹ አይመታኝም እንደመከሩኝ አደርጋለሁ ብለሽ ጣፊ ›› እላታለሁ
አስተርጓሚያችን የራሷን ትጨምርበታለች

‹‹አንተንስ ወደዛ ብርድ አጠናፍሮ በጣለህ ኦረህም ተረት መፃፍ ነው ... ››

‹‹ አረግየ እርስወስ መቸ ነው የሚመጡና የሚያዩን ...አገሩ አልናፈቀዎትም ....እንደው ተራራው ወንዙ ... (ወንዙ አልሽ እላታለሁ አስተርጓሚያችንን)
‹‹አቦ ዝም ብለህ ተናገር ወደዛ .... እንዳንደኛ ክፍል አልሽ ምናምን ትላለህ እንዴ ››

‹‹ ሳሩ ...ሙጃው ...ባህር ዛፉ ...ዝግባው .... ግራሩ ....አጋሙ ..... ኮሽሙ ...ቀጋው አልናፈቀዎትም ? ››

‹‹አሌክስ ኧረ በእግዚያብሄር አጠር አድርገው ተው ተው . . . ››
‹‹ዝም ብለሽ ያልኩሽን ፃፊ አንች ልጅ ....ምንድነው ትልቅ ሰው ሲያወራ ጣልቃ መግባት ›› እልና እቆጣታለሁ ... አንጀቷ ትክን ብሎ በዝምታ ማስተርጎሚን ትቀጥላለች ....ከዛም እቀጥላለሁ

‹‹ ፅዱ በንፋስ ሻሻሻሻሸሻሸሻሸሻሸሻሸሻ ሲል ... የጥቅምት አደይ መስኩን ሲሞላው .....ደግሞ የከኩ ዛፍ ... እንጆሪው ... የወይኑ ፍሬ ....››

‹‹ ዋይን አለ እንዴ ?...›› ትላለች አስተርጓሚያችን ድንገት በመሃል
‹‹ ታዲያ ››

‹‹እንደልባችሁ ትጠጣላችኋ ? ›› አለች በመጎምዠት ‹‹አይ ፍሬው ነው ያለው ›› ‹‹ዋት ኤቨር...››

‹‹ሰካራም ! ዋይን ሲባል ጆሮሽ ቆመ ›› እላታለሁ ....ይችን ተጠቀመችባት ‹‹ ወይን ሲባል ጆሮሽ ይቆማል ሰካራም ባልቴት ብሎሻል ›› ብላ ለአረግየ ስዊት እንደነገረቻቸው ኪኪኪኪ ከሚል ምልክት ጋር ....ላከችልኝ ...

አረግየ እንዲህ አሉ ‹‹ ድሮም ልጅ ጋር አትጫወት ይወጋሃል በንጨት ማለት ይሄ ነው ....ባለጌ አሳዳጊ የበደለህ ...ምነው አሸባሪ ብለው እግር ከዎርች በጠፉልኝ ›› ብሎክ ! የዛሬ ልጆች ለተንኮል ማን ብሏቸው ..... !!

ዛሬ ሰኞ ነው ...በጧቱ የመጨረሻ ደስስስስ ብሎኛል ! ከመሬት ተነስቶ አይደለም ! በምክንያት !እደግመዋለሁ በአሪፍ ምክንያት .... እና አንዳንዴ መቸም የግል ጉዳይ እንዲህና እንዲያ ተብሎ ባይነገርም ደስታን ለወዳጅ ማካፈሉ አሪፍ ነው በሚል እንዲሁ መደሰቴን ገለፅኩ ! ምናይነት ቅዳሜ የመሰለ ሰኞ ነው !! ሃሃሃ ለምን ይዋሻል .... ከቅዳሜም ይበልጣል ! ‹‹ደስታና ሽቶ ሁለቱም አንድ ናቸው ለራስ ሲያርከፈክፏቸው ለሌሎችም ይተርፋሉና ›› ያለውን ሰውየ ወይም ሴትይት ፈልጋችሁ ማኪያቶ ጋብዙልኝ !!እናተም ባላችሁበት በራሳችሁ ሂሳብ ብሉልኝ ጠጥሉኝ !

ያው የደስታየ ምክንያት የግል ስለሆነ ምክንያቷ ትቆየን ብየ ....‹‹በወቅቱ የተወረወረች ቃል ምንኛ መልካም ናት ›› እንዲል መፅሃፉ ስለደስታ አሁን መናገር አለብኝ አልኩ .....

በጧት ነው የተነሳሁት ....መንገድ ላይ ፊታቸው የጨፈገገ የቀን ሰራተኞች ምሳቸውን ቋጥረው ወደስራቸው ሲጣደፉ ስመለከት ‹‹ና አንተ ›› ብየ ደስታየን ጨለፍ አድርጌ ብሰጣቸው በደስታ የሚፍለቀለቁ ነገር ይመስለኛል .....እና በቃ ውስጤ ያለው ደስታ ለሁሉም የኢትዮጲያ ህዝብ ተካፍሎ በመጨረሻ ብዙ የሚተርፈኝ እየመሰለኝ ....ደስተኛ ስትሆኑ ቸር የሆናችሁ ይመስላችኋል ! የጥላቻ የቂምበቀል እና የመከፋት ጉልበት የሚቆየው ቁራጭ ደስታ ውስጣችሁ እስኪፈጠር ድረስ ነው ....ጎሊያድ የሚያክል መከፋት ጠጠር በምታክል ደስታ በአፉ እንደሚደፋ ላረጋግጥላችሁ እወዳለሁ ! ካላመናችሁ ያጋጥማችሁ ! ሌላ ምን ይባላል !

.

ግን ደስታ ስላችሁ ... ከጨረባ ደስታ ይለይ ....

ማታ በአየር ላይ አንሳፏችሁ ጧት ራስ ምታት ጥሎላችሁ የሚሄድ ደስታ አለ ... የሆነ ጊዜ በፍቅር አብዳችሁ ደስ ብሏችሁ መዘዙን ጥሎላችሁ የሚሄድ ደስታ አለ .... ኪሳችሁ በፍራንካ ተሞልቶ አፍንሽንሾ ሲራገፍ የአግኝቶ ማጣት ታርጋ ግንባራችሁ ላይ ለጥፎ እያሳቀቀ ፈትለክ የሚል ደስታ አለ ! ብቻ ብዙ ደስታ አለ በእድሜ የተወሰነ ! እመኑኝ እኔ ዛሬ ደስ ያለኝ ደስታ የዛሬ አምሳ አመት ከዘራየን ይዣ ነፅ ፀጉሬን እያሻሸሁ ሁሉ እደግምላችኋለሁ !‹‹ ደስታህ ያምሽ ›› ይሉት ምርቃት ትዝ የሚለው ይህን ጊዜ መስሎኝ !! ‹‹ደስታህ ያምሽ ›› ይሉት ምርቃት ከመልካም ልደት ሳያስከነዳ አይቀርም !

እና .....ደስ ብሎኛል !!

የዩኒቨርስቲ መምህራንን ማዋከብ አገርን ከመግደል አይተናነስም !! (አሌክስ አብርሃም)

አንድ የአማርኛ ዜና ድረ ገፅ ትላንት ቅዳሜ በለጠፈው ዜና እንዲሁም ከዜናው ስር በተሰጡት በርካታ አስተያየቶች በጣም ነው ያዘንኩት ! ዜናው እንዲህ ይላል ‹‹በኮተቤ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ ትምህርቷን ስትከታተል የነበረች አንዲት የሁለተኛ ዓመት ተማሪ ውጤቷ ስለተበላሸባትና እንደገና በወሰደችው ፈተና /supplementary exam/ አስተማሪው እንደገና ‹‹ኤፍ›› ስለሰጣት እንዲያስተካክልላት ስትለምነው ውላ አላስተካክልም በማለቱ ከሌሊቱ ዘጠኝ ሰዓት ግቢው ውስጥ ያለ ዛፍ ላይ ተሰቅላ ራሷን አጥፍታለች .....›› ከዚህ ዜና ስር በርካታ አስተያየት ሰጭዎች መምህሩ ላይ የእርግማንና የስድብ ናዳ አውርደውበታል ! የሚሰቀጥጡ ፀያፍ ስድቦችንም አዝንበውበታል !

እንግዲህ ያሳዘነኝ ጉዳይ .....ሲጀመር መረጃውን ያቀረበው ድረ ገፅ ዜናውን በምንም አይነት ተጨባጭ ማስረጃ አላስደገፈም ! ከዚህም በላይ ለልጅቱ ሕይወት መጥፋት መምህሩን እንደምክንያት ለማቅረብ ሞክሯል ! በአገራችን ወግና ባህል መሰረት ማንም ይሁን ምንም ይስራ ሚች አይወቀስም! ... ይህንን እሽ ይሁን ብለን እንቀበል ....ግን ጥፋቱ የማን እንደሆነ ባልታወቀበት ሁኔታ ቋሚንስ ሰድቦ ለሰዓቢ መስጠት ለምን አስፈለገ ?

ልጅቱ ያገኘችው ውጤት በትክክል የሰራችውን ከሆነ ውጤቱ በመበላሸቱ እንደገና የመፈተን እድል ከተሰጣትና በድጋሚ ማስተካከል ካልቻለች በልመናም ይሁን በሌላ መንገድ ይህ መምህር ውጤት የማስተካከል ግዴታ የለበትም !! እንደውም ያለማስተካከል ግዴታ አለበት ባይ ነኝ ! ከዛ ውጭ ግን ልጅቱ ምንም አይነት ህገወጥ ድርጊት እስካልተፈፀመባትና ያገኘችው ውጤት በትክክል የስራዋ ዋጋ እስከሆነ ድረስ ራሷን ለማጥፋቷ መምህሩ የሚወቀስበት ምንም ምክንያት አለ ብየ አላምንም !

በእርግጥ የዚህ አይነት አሰቃቂ ነገሮች ሲፈፀሙ ከዚህ በፊትም ሰምተናል ... ውጤት ተበላሽብኝ ብላ በረኪና የጠጣች ልጅ አስታውሳለሁ (ተርፋ ተመርቃለች) ... ከህንፃ ላይ የዘለለ ልጅ ....ሰምተናል ! በእኛ አገር ተጨባጭ እውነታ ከዩኒቨርስቲ መባረር ሰማይ ምድሩን የሚያጨልም በቤተሰብም ሆነ በመሃበረሰቡ በበጎ የማያስነሳ ትልቅ ውድቀት ተደርጎ ነው የሚታየው ! የትኛው ወላጅ ነው ልጁ ተምሮ ተመራምሮ ተዓምር እንዲፈጥር የሚጠበቀው ....ተምሮ ስራ ከያዘለት በቃ ! ከዚህ የበለጠ ውጤታማነት የለም !! ከነአባባሉ ‹‹ልጀ ራሱን ሊችል / ራሷን ልትችል ትንሽ ቀረው / ትንሽ ቀራት ›› እያለ ቀን ይቆጥራል ይህ የቤተሰብ ተስፋ እንደድንጋይ ወፍጮ ልጆች ጫንቃላይ ተጭኖ በሃሳብ ቢሰልቃቸው አይደንቅም !

ለዛም ነው ከበርካታ ዩኒቨርስቲዎች የሚባረሩ ተማሪወች ወደቤተሰብ ከመመለስ ይልቅ በማይሆን ቦታ ቀልጠው የሚቀሩት ....በርካታ ሴት ተማሪዎችኮ ከግቢ ሲባረሩ ሴተኛ አዳሪ ሁነው እዛው አካባቢ መቅረታቸው የአደባባይ ሚስጥር ነው !! በእነዚህ ልጆች ላይ መፍረድ ከባድ ነው ...በሬውን ሸጦ አዲስ ልብስ ገዝቶ ዩኒቨርስቲ የላከን ቤተሰብ ‹‹ተባረርኩ ›› ብሎ ተመልሶ አይኑን ማየቱ ያሳቅቃል ....ከመስሪያ ቤቱ የስንት ወር ደመወዝ ተበድሮ ልጁን ወደዩኒቨርስቲ የሚያስገባ ወላጅ የልጁ መባረር መርዶ ቢሆንበት አይገርምም .... የተሻለ የሚባለው እንኳን ‹‹ልጀ ዩኒቨርስቲ ገባ›› ብሎ ትልቅ ድግስ ደግሶ የሚሸኝ ወላጅ ነው ! እዚህ ወላጅ ጋር መመለስም ድግሱን የበላው ወዳጅ ዘመድ በሃሜት ጥርሱ ሲዘለዝለው ትዝ እያለው ብዙሃኑ ተማሪ መመለስን የሞት ሞት አድርጎ ቢመለከተው አይደንቅም !!

የዚህ ሁሉ ችግር መነሻው የህይወትን መንገድ እንደጋሪ ፈረስ በአንድ መስመር መመልከትና ያች መስመር እንቅፋት ሲገጥማት ተስፋ መቁረጥ ላይ መወደቁ ይመስለኛል .... ለዚህም ነው በየዩኒቨርስቲው ለተማሪወች የምክር አገልግሎት የሚሰጡ ባለሙያዎች ተመድበው እንደየዩኒቨርስቲው ጥንካሬ ይህንኑ ስራቸውን በተለያየ ደረጃ የሚያከናውኑት! ውጤታማ ነው ወይ ...ሌላ ጥያቄ ነው ! ምክር እንደመድሃኒት የሰውን አካላዊም ይሁን ስነልቦናዊ ችግር በተቀመጠለት ቁርጥ ያለ ጊዜ ይነቅላል ብሎ ማሰብ አይቻልም ....ጊዜ ይወስዳል ...ሃላፊነት የሚሰማው መካሪም ተመካሪም ይጠይቃል ! በተለይ ለመለወጥ ከውስጡ የወሰነ ተመካሪ ያሻል !

በአሁኑ ጊዜ ዩኒቨርስቲዎች በአንድ ጊዜ ከሚቀበሏቸው ተማሪወች ቁጥር አንፃር እንኳን የተለየ ችግር መፍታት መደበኛውን ትምህርትም በሚፈለገው ጥራት ማድረስ መከራ መሆኑ ግልፅ ነው ! በዛ ላይ ተማሪውን ለማጥድ ዩኒቨርስቲዎች ዙሪያ የተዘረጋው የመጠጥ ቤት የጫት ቤት የወሲብ ንግድና ሌላም በርካታ የውድቀት መረብ ... ዩኒቨርስቲዎቹ ከሚያሳድሩት በጎ ተፅእኖ በላይ ወጣቱን የሚያማልሉ ጉዳዮች ናቸው ! ወጣቱ ራሱ ዩኒቨርስቲን ከሞራል ከሃይማኖትና ግብረገብነት ‹‹ እስር ›› ነፃ የሚወጣበት የነፃነት ውቂያኖስ አድርጎ አድርጎ እያየው ነው ! ከቤተሰብ ሲርቅ ለያዥ ለገናዥ እስኪያስቸግር ፈንጥዞ ልሙት የሚል ተማሪ ዩኒቨርስቲውን ካፍ እስከገደፉ ሞልቶ እያየን ነው !

ከምንም በላይ ከዚህ የጥፋት መአበል ራሱን በማዳን የህይዎት መስመሩን የማቃናት ሃላፊነት ደግሞ የተማሪው የራሱ ነው !! እዚች አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ብንሄድኮ ስንት ጉድ ነው የምናየው ... ትላንት የተከፈቱ የክፍለ ሃገር ዩኒቨርስቲዎችን የከበባቸው ጫት ቤት መጠጥ ቤት ሽሻ ቤት ያስደነግጣል ....ሴት ተማሪዎችን የሚያቃጥሩ ደላላዎች ከዩኒቨርስቲ መምህራን በላይ የሚከበሩባት አገር ላይ እኮ ነው ያለነው !! ይሄ በሆነበት አገር ተማሪ ላይ ችግር በተፈጠረ ቁጥር ሃላፊነቱን አስሮና ጠቅልሎ የዩኒቨርስቲ መምህራን ላይ መወርወር ምን የሚሉት ፍርደ ገምድልነት ነው ... አንዳንዱ የዩኒቨርስቲ መምህራንን መዘለፍ መንግስትን መቃወም ስለሚመስለው በመሳደቡ ለአገሩ በጎ ነገር ያበረከተ ሁሉ ሳይመስለው አይቀርም !

በተደጋጋሚ እንዳየሁት የዩኒቨርስቲ መምህራን ላይ ብዙ ሰው ጭፍን ጥላቻ ያንፀባርቃል !ይች አጋጣሚ የዚህ ስር የሰደደ ጥላቻ ውጤት ሁና ነው የታየችኝ ! በየትኛውም ዘመን የተበላሸ የፖለቲካ ቁርሾ ጭፍን የጥላቻ በትሩን የሚያሳርፈው የዩኒቨርስቲ መምህራን ላይ ነው ! የትም ሲንዘላዘል ከርሞ ውጤቱ አልጥም ያለው ተማሪ መፈንጫው የዩኒቨርስቲ መምህር ነው ...

ሎከሯ ቢከፈት የኮስሞቲክስ ሱቅ የሚመስል ማንም እንደእቃ ባቆመው መኪና እየጫነ ከግቢ የሚወስዳት ተማሪ ወጤቷ ሲያሽቆለቁል ‹‹ ጠይቆኝ እንቢ ብየው በዛ ወርዶ በዛ ሂዶ ሴትነቴ ›› እያለች ራሷ መሬት ላይ ጥላ የረጋገጠችውን ሴትነት በአምባ ገነን ዩኒቨርስቲ መምህር ሴሰኝነት የተነጠቀች ልታስመስለው ትሞክራለች ! እውነታውን እናውራ ካልን በራሷ ችሎታ የምትተማመን ሴት ...በሴትነቷ ውጤቷን ትቀማለች ማለት ዘበት ነው (ወይም እኔ በዚህ ዘመን እንደዚህ ይሆናል ብየ አላምንም) ሚስኪን ሁበረተሰብ የእነዚህን እንዝላል ተማሪወች ተረት እየሰማ የመምህራኑን ስም በሰነፍ ልጆቹ ስንዝር ይለካል !

‹‹ አንድ የተረገመ መምህር ኤፍ ሰጥቶ ልጄን ጣለው ልጄን አባረራት ›› እያለ ያማርራል ! ዩኒቨርስቲዎችን የሴሰኛና አምባገነን መምህራን መጠራቀሚያ ዋሻ አድርጎ ይስላቸዋል ! አይፈረድበትም ልጆቹ ናቸዋ የራሳቸውን እንዝህላልነት ለመሸፋፈን ወሬውን ይዘውለት የሚሮጡት ! ማንም መምህር ለማንም ‹‹F›› አይሰጥም.. ‹‹A ›› አይሰጥም ....ተማሪው ራሱ በስራው ኤፍም ኤም ያመጣል !! ይሄው ነው እውነታው ! እኔ የማምነው ይሄው ነው ...

በዩኒቨርስቲ ቆይታየ በርካታ ውብና ጎበዝ ሴቶች ማንም ዝንባቸውን እሽ ሳይላቸው በነፃነት ተምረው ተመርቀዋል ! የዩኒቨርስቲ መምህራኖች ሰው ናቸው... የትኛዋንም ሴት ለፍቅርም ይሁን ለወሲብ ሊፈልጓት ይችላሉ ... .መምህርነታቸውን ተገን አድርገው ሳይሆን ፍላጎታቸውን ብቻ ተከትለው ....ያኔ የሴቷ የራሷ ፍላጎት ነገሮችን ይወስናል !! በእርግጥ አንዳንድ ጋጠወጥ ባህሪ ያለው የመምህርነት ስልጣኑን እንደማስፈራሪያ ተጠቅሞ ፍላጎቱን ለማሟላት የሚሞክር የለም ማለቴ አይደለም ግን እንዲህ አይነቱ ባለጌ ሴሰኛ የበርካታ ምርጥ ዜጎች ማፍሪያ የሆኑ ዩኒቨርስቲዎችን አይወክልም !! አንዳንድ ወረቀት ጠላቱ የሆኑ ሴትነታቸውን የሁሉ ነገር ቁልፍ አድርገው ውጤት ለማጋበስ የሚሯሯጡም ሴቶች ሞልተዋል ግን ሁሉንም የዩኒቨርስቲ ሴቶች አይወክልም !!

የዩኒቨርስቲ መምህራን በዚህ አይነቱ ተልካሻ ዘ ልማድ ሲዘለፉ መኖር የለባቸውም .... ሌላው ህዝብ እንደፈለግ ሲሆን ጀርባቸውን አጉበጠው ጥናትና ምርምር ላይ እድሚያቸውን የሚፈጁ ብዙ ናቸው .... እውቀት ሲያሳድጉ ቤት ንብረት ያላፈሩ ....እንደሰው ትዳርና ልጅ ሳያዩ እድሚያቸው የሄደ .....መዓት ናቸው ! ወጣት መምህራንም ቢሆን ራሳቸውን በጨዋነትና በእውቀት እያሳደጉ ለዚች አገር በገንዘብ የማይተመን ውለታ እየዋሉላት ነው !! ያውም የሚገባቸውን ክብርና ጥቅም ሳትሰጣቸው !! በዙሪያችን ያለው ባለሙያ ሁሉ በአንድም በሌላም መንገድ የዩንቨርስቲ መምህራን ክንዶች ደግፈው ያቆሙት ነው የህክምና ባለሙያው ...አስተማሪው ኢንጅነሩ .....ሁሉም ይችን አገር እንደአገር ያቆማት ሁሉ የዩኒቨርስቲው መምህር ውጤት ነው !!

መሃበረሰቡ ተማሪው ራሱ ላልተወጣው ሃላፊነት ሁሉ ...የተማረውም ...የዩኒቨርስቲ ደጅ ረግጦ የማያውቀውም መምህራኖቹን በየምክንያቱ መስደብና ማሸማቀቅ ማዋከብ ማንንም ሳይሆን አገርን መግደል ነው !! እንደኔ እንደኔ የዩኒቨርስቲ መምህራን ስራቸውን በታማኝነትና ለተማሪወቻቸው ዓርአያ በሚሆን መልኩ ሙያቸው ብቻ በሚያስገድዳቸው መንገድ በፍፁም ነፃነት ማከናወን አለባቸው

መንግስትም ከዚህ የስራ ድስፕሊን የሚያፈነግጡና የተሰጣቸውን የማስተማር ሃላፊነት ተገቢ ባልሆነ መንገድ የሚጠቀሙ መምህራን እንዳይኖሩ ሲስተሙን ግልፅና ተጠያቂነት ያለበት ማድረግ ይጠበቅበታል .....ከዚህ ውጭ ግን የራሱን ሃላፊነት ያልተወጣ ተማሪ ውጤት በተነገረው ቁጥር እራሱን በማጥፋትም ይሁን በሌላ መንገድ የስነልቦና ጫና ፈጥሮ ያልዘራውን ለማጨድ ከሞከረ .... የድፍን ግቢው ተማሪ ገመዱን ሸምቀቆ እየሰራ ጫካ ቢወርድ ሃላፊነቱ የራሱ ነው !! ሲጀመር ራሱ ያመጣውን ውድቀት ተቀብሎ ለማረም ወኔው የሌለው ...የሞራል ብቃቱ የከዳው ዜጋ እርሱ ቢኖር እንኳ አገር መግደሉ አይቀሬ ነው !!

እረኞም እድሜና ጤና ትውልድን ለወሳኝ የኑሮ ምእራፍ ለሚያዘጋጁት ሃቀኛ የዩኒቨርሰቲ መምህራን !!

ታሪክ እግዜር ይይልህ !

(አሌክስ አብርሃም)

እንደው ታሪክ ራሱ አንዳንዴ ሲዋሽ አይን የለውም ከምር .... እስቲ ስለኪሊዮፓትራ ታሪክ ሲነግረን ምን ብሎ ነው .....?????

‹‹ውብ አማላይ የነገስታቱን ልብ የምታሸፍት ....ለአገሯ ስትል ወራሪወች ጋር አብራ እስከመተኛት የደረሰች ራሷን

መስዋእት ያደረገች ልእልት ›› ወዘተ እውነታው ግን

1ኛ .ኪሊዮ ፓትራ እስካሁን በትክክል መልኳን የሚገልፅ ምስል የላትም !!

2ኛ. የእርሷ ነው ተብሎ የተገመተ አፅም ላይ የፊት ቅርፁን አጥንተው የፃፉት እንደሚሉት ከሆነ ግን ...ኪሊዮ ፓትራ ቆንጆ ሳቢ ምናምን የሚባል የፊት ገፅታ አልነበራትም!! ...እንደውም በዘመኑ አስቀያሚ የፊት ገፅ አላቸው የሚባሉና በወንዶች የማይወደዱ ‹‹አግጫም ›› ሴቶች መካከል አንዷ ነበረች! ያኔ ረዥም አንገት እንጅ ረዥም አግጭ አይወደድም ነበር !!

....አጥኝዎቹ የተስማሙበት ነጥብ ግን ኪሊዎፓትራ ዳሌዋ ሰፋ ያለ ‹‹ኧረ ምኑን ሰጠሽ ›› አይነት የምታዘፍን ... ትንሽ ስልጣንና ሃብት ይኑረው እንጅ የጠራት ወንድ አልጋ ላይ ሳታንገራግር የምትገኝ ምኗም ለዓለም ሴቶች ምሳሌ የማይሆን አለሌ ሴት ነበረች !! እንደውም የሚቃወሚትን ሁሉ ሴትነቷን ለባለስልጣናት ለነገስታት እና በዘመኑ ለነበሩ ጦረኞች እየከፈለች ባጭር ስታስቀጥፋቸው የነበረች የተረገመች ሴት ነበረች !! እና አንዳንድ ሰዎች ለፍቅረኞቻቸው ሳይቀር

‹‹እንኪሊዮ ፓትራ ውበትሽ ማራኪ ካልተሰገደልሽ ጫፍ የማታስነኪ ....›› ምናምን ብለው ግጥም ሲፅፉ ፍቅረኞቻቸውም ፈገግ ብለው በደስታ ሲያዳምጡ ...ታሪክ እግዜር ይይልህ ያስብላል !!

...የኪሎ ፓትራ አፍንጫ ሳይሆን የኪሎ ፓትራ ዳሌ ጠቡብ ቢል ወይም አይምሮዋ ሰፋ ቢል ኖሮ የዓለም ታሪክ በተቀየረ የተቃወሚት ጥበበኞች ምሁሉ በህይዎት በኖሩ ነበረ...!!

ልቀቅ !! የዝሙት መንፈስ ....ዘፋኞቻችንን !

(አሌክስ አብርሃም)

እስከዛሬ ሚስኪን ዘፋኞቻችንን እየወቀስን እየዘለፍን እንዳሸማቀቅናቸው የገባኝ ዛሬ ነው ... ይሄ ክሊፕ የሚባል ነገር ላይ ...ዘፋኙ ሁሉ በሴት ገላ ፍቅር ማበዱ ለካ የአገሬው ዘፋኝ ላይ ምናምን መንፈስ ዙሮበት ነው .....ማን አዞረበት..... ምናልባት በኢትዮጲያ የዘፈንና ፊልም ኢንዳስትሪ አይናቸው ደም የለበሰ የውጭ ሃይሎች ሊሆኑ ይችላሉ (ኢንዳስትሪውን ለማራበሽ ለማበጣበጥ) ....

ቀልድ እንዳይመስላችሁ .....ዘፋኞቻችን ላይ አንዳች መተት ዙሮባቸዋል .....ወኔያቸውን ሰልቦ ሴት ሴት ሴት ሴት የሚያስብል ....ሴቶቻችንን እንደመርካቱ ፍየል ገበያ ለገበያ የፍየል ጅራት የምታክል ሚኒ ለብሰው በዳንስ ስም እንዲፈራገጡ ግዴላችሁም ያፍዝ አደንግዝ ያደረገባቸው አለ !!..ክሊፑ ፊልሙ ....

ሴት መጣች

ሴት ሄደች

ሴት ከዳች

ሴት ደነሰች

ሴት ሳቀች

ሴት ዋኘች

ሴት አለቀሰች ...ሴት መኪና ነዳች ..ሴት የልብሷን በሻንጣ እየጎተተች በቦሌ በኩል ሄደች ....ሴት በሄደችበት እግሯ ተመለሰች ....

ሴት በስልክ አወራች

ሴት ትልቅ የግቢ በር ከፍታ ገባች

ሴት አይስክሬም ላሰች

ደግሞ ገጠር ...ሴት ውሃ ልትቀዳ ወንዝ ስትወርድ ዱላ የያዘ ጎረምሳ አገኛት ...ሴት እንስራዋ ተሰበረ ....ሴት በነጠላ ተሸፋፍና ሜዳ ለሜዳ ተሳሳመች ....ሴት አፈረች ....ሴት ኩበት ጠፈጠፈች ...ሴት ከከተማ መኪና ይዞ በሄደ ወንድ ፍቅር ተማረከች ...ሴት ከተማ ገብታ ቡና አፈላች ...ሶፋ ላይ ተቀመጠች ...ሴት ፀጉሯን ፈረዘች ...ሴት ቴሌቪዥን አየች ...ሴት ካደች ...ሴት የተኮሳተረችበትን ዘፋኝ መልሳ ወደደችው ...ሴት ..ሴት .....ሴት .....ኡኡኡኡኡኡ

ቆይ ግን እንዲህ በመልአክ ሒሳብ የሚሸረግድላቸው ሴት ማለት እነዚህ የምናውቃቸው እናት ሚስት እህት የሆኑት ናቸው ወይስ ሌላ ..... እነዚህ ማታ ማታ ባሎቻቸው የሚቀጠቅጧቸው ጎረቤቶቻችን ናቸው ወይስ ሌላ ...እነዚህ በየመጠጥ ቤቱ ሰውነታቸውን እንዲቸረችሩ የተገፉት ናቸው ወይስ ሌላ ....እነዚህ ከአስረኛ ክፍል እንኳን ሚያሻግራቸው አጥተው በየቡቲኩ ጠባቂ የሆኑት ናቸው ሌላ ....እነዚህ አረብ አገር ፍዳቸውን እየበሉ ሚስኪን ቤተሰቦቻቸውን የሚረዱት ናቸው ወይስ ሌላ ....

ለካ የኢቲቪ ኢትዮጲያና የእውነቷ ኢትዮጲያ እንደሚባለው ....አገራችን ላይ ሴቶችም በሁለት ነው የሚከፈሉት ... የክሊፕ የውሻሽት ክበር ቀማሽ ሴቶችና የእውነቱን ኑሮ ገፊት ቀማሽ ሴቶች!! ክሊፑ ሁሉ በየጭፈራ ቤቱ

ስለሚያውደለድሉ ሴቶች እኮ ነው የሚያወራን ....ሶፋ ላይ እንደጎጆ ቤት ተከምረው ስለሚውሉት የክሊፕ ሴቶች እኮ ነው የሚያወሩን .....ኧረ የእውነት ሴቶች ወዴት አሉ .....እሽ ለዘፈን ብቁ ካልሆኑ ሙሾም ቢሆን ይሰራላቸውና በአደባባይ የሚታይ ክሊፕ ይሰራላቸው !

ሌላው ቀርቶ ስለቤት ሰራተኛ ሴት እንኳ ሲዘፈን በረባሶ የለበሰ ዘበኛ ጋር ስትዳራ ነው የሚያሳዩን ... እውነቱን እንነጋገር ከተባለ አዲስ አበባ ውስጥ ስንቷ የቤት እመቤት ነች ሽሮና በርበሬዋን ቆልፋ ሰራተኛዋ ላይ ክፉ ዘበኛ የምትሆነው ....እንኳን ሰፊ ግቢ ውስጥ ሞልቶላት አለሚን የምትቀጭ ሰራተኛ ....ሴት መቀመጫዋ ስክሪኑን ሞላው ሴት ጡቷ ስክኑን ሞልቶ ተረፈ ....ሴት ሶደሬ ሄዳ ውሃ ተራጨች .....

በጣም ሚገርማችሁ ይሄ ዝሙት ካዞረው አናት የሚፈለፈል ኮረት ጩኸት አገሬውንም እንደጋሪ ፈረስ እይታውን ሸብቦ ውበት ማለት የሴት ወሲብ ቀስቃሽ ድርጊትና ሰውነት ብቻ እንዲመስለው አደረገው ! ሰሞኑን ስለህንድ ዘፈኖች የሆነች ቁራጭ ፅሁፍ እያየሁ ነበር ....ስልሳ ፐርሰንት አካባቢ የሚሆነው የህንዶች ዘፈን ከሰብአዊ ፍጥረት ውጭ ያለው ተፈጥሮ ላይ ያተኮረ ነው ! ስለአበባ ስለመልከአ ምድር ስለዛፍ ....ስለድንጋይ ሳይቀር ውብ ዘፈኖች አሏቸው ....መንፈሳዊ ተፅእኗቸው ይበዛል ... ብትፈልጉ ስለዶሮ ላባ ሁሉ ዘፍነዋል ...ስለ እፉየ ገላም ምርጥ ዘፈን አላቸው .....

ህንድን ተውት ...እዚህ ጎረቤታችን ሱዳን ስለእሸዋ መአት ዘፈን አላቸው ... ስለግመል እንደጉድ ዘፍነዋል ....ያውም ውብ ዘፈኖች ....ስለበርሃ ስለፅሃይ ዘፍነዋል ... እኛ አገር ስለፀሃይ የተዘፈነ ዘፈን አላስታውስም ...ምናልባት ‹‹ፀሃይ ደመቀች ›› የሚል የህፃናት መዝሙር ካልሆ በስተቀር ! ስለጨረቃም የተዘፈነ ዘፈን አልሰማሁም ! እንደውም እጅጋየሁ ሽባባው (ጅጅ) ጭራሽ ጨረቃን በወደደችው ወንድ ለውጣ አገራችንን ካለጨረቃ ልታስቀራት መሞከሯን ልብ ይሏል .....

‹‹ ጨረቃ ባትወጣ ደምቃ ባትታይ አንተ ትበቃለህ ላገሬ ሰማይ ›› እርፍ !!

እስቲ አስቡት ብዙሃኑ ዘፋኝ ከቤተ ክርስቲያን ዘማሪነት እየፈለሰ ወደአለማዊ ዘፋኝነት በተቀየረባት አገር .... ጭትና ማታ የያሬድን ዜማ የቅዳሴ ድምፅ እየሰማ ያደገ ማህበረሰብ ....እንዴት ‹‹ሴት ሴት ›› ብየ ልሙት ይላል ! ምናይነት ከአለም የተለየ አመንዝራነት ቢሰፍንብን ነው ....አስራ ሶስት ወር ፀሃይ ተራራ ሽንተረር ውብ ፀአዳ ምድረበዳ ያላት አገር እንዴት በሴት ልክፍት ተይዞ ዜማ የለበሰ ዝሙት ህዝብ ላይ ይረጫል ....ከምር በጣም ነው የሚያስጠላው .... የሚቀፈውም ! ደግሞ እኮ ስለሴትም ሲዘፈን ሴትን እንድናደንቅ አያደርጉንም ....የአልቃሻው ብዛት ... ዘፈኑ ሁሉ እየየ ... ወየው ! ትታኝ ሄደች አፍር ልሽ ድንጋይ ተንተርሽ አስተምሪያት ካደችኝ ...ትካድሃ !! እኛም መሄጃ አጥተን ነው ያንተን ለቅሶ የምንሰማው ! ምድረ ሙሾ አስወራጅ !!

የሚገርማችሁ ....ዘፋኞቻችን በቃ ብቃቱ ስለሌላቸው ብቻ ነው እንዳንል ..... ለማስታወቂያ ሲሆን እንጥላቸው እስኪወርድ ስለቢራ ያላዝናሉ ! ...ስለፍራሽ ይዘፍናሉ ...ስለባንክ ይዘፍናሉ ....ስለጥርስ ሳሙና ይዘፍናሉ ... ስለፓስታ ይዘፍናሉ ....ስለቅባት ስለሎሽን ይዘፍናሉ .... ስለቤት ክዳን ቆርቆሮ .....ስለታሸገ ውሃ ይዘፍናሉ ....ስለጫማ ....እስቲ አሁን ስለሚስማር ምኑ ይዘፈናል ....ይዘፍናሉ !!

ቃ ስክት ቃ ግጥም በባለባርኔጣ

መቸ ያስፈራን እና ነጎድጓድ ቢመጣ ....ምናምን እያሉ ይዘፍናሉ ! የአይጥ መርዝ አምጥቶ የሚያከፋፍል ባለሃብት ቢከፍላቸው ስለአይጥ መርዝም ይዘፍናሉ !

ታዲያ በስርአት ወደራሳቸው ሲመለሱ ስለሴት እና ወንድ ብቻ የሚንቋርሩብን ..... ምን ነክቷቸው ነው .... ዘፋኞቻችን አደገኛ የዝሙት መንፈስ ተጠናውቷቸዋል ግዴላችሁም ! ህዝቡ እነዚህን አስፀያፊ የሴት ሰውነት የሚያስቸረችሩ ዘፋኞች ስራ ወደዛ በመወርወር የሙዚቃውን ደረጃ ከፍ ማድረግ ይችላል .... የሴት ሰውነት በማየት እና በመመኘት እኮ የወሲብ ንግድ የጦፈበት ዘመን ሆነ ...ፊልሞቻችንም ያው ናቸው .... ‹‹ዋው የኔ ቆንጆ ቁመትሽ ለፊል የሰጠ ነው ›› ተብለው ከመንገድ የሚጎተቱ ሴቶች የሞሉት ፊልም ! ሁልጊዜ ካላሳኩ ብሎ የሚጃጃልብን የፊልም ዘውድ ላይ የጃጀ ሰውየ የሚጨማለቅበት ፊል ! አንድ ቀን ሰካራም ሁኖ ከተጨበጨበለት ሁልጊዜ እንደተወላገደብንና እንደተለፋደደብን የሚኖር ተዋናይ የሞላበት ....

እንደው ፖለቲካችን ጤነኛ ስላልሆነ መንግስት የነካው ነገር ሁሉ ‹‹ሃራም›› ብለን እንጅ ለተለያዩ ጉዳይ በሀብረት የተሰሩ መዝሙሮችን እስቲ አዳምጧቸው ምን ያህል ውስጣችን እንደሚገቡ ! ዘፋኞቻችን በግል ካቃታቸው በቃ አንድ ለአምስት እየተደራጁ ይዘንምሩልን ! ደግሞ አያፍሩም እኮ አስርም ሁነው ‹‹ እኛ አንችን ስንወድሽ ካድሽን በጠራራ ›› ይሉ ይሆናል ....ያደቆነ ሰይጣን ሳያቀስ አይለቅም እንዲሉ !

ልቀቅ !! የዝሙት መንፈስ ....ዘፋኞቻችንን ! ልቀቅ እኛንም ተመልካቾችን !

የአፍ መፍቻ ቋንቋችን

(አሌክስ አብርሃም)

አንድ ተራ ዜጋ ወደ ንጉስ አክባር ቤተ መንግስት ሄደና ‹‹ ንጉስ ሆይ ልዩ ችሎታ እና ብቃት ስላለኝ ይህን ችሎታየን በፊትህ እንዳሳይ ይፈቀድልኝ ›› ሲል ንጉሱን ጠየቀ ...

ንጉስ አክባር በአስራ አምስተኛው ክፍለ ዘመን አካባቢ ህንድን ይገዛ የነበረ ንጉስ ነበር ! እንደውም የንጉስ አክባር አያት ታጅመሃልን ያስገነባ ስመ ገናና አያት ነበረ .....ታዲያ ኪነጥበብን መውደድ የዘር ውርስ ሁኖበት ይሁን አልያም የነፍሱ ጥሪ ብቻ አክባር ለጥበብ ሚች ነበር !! በዚህ ንጉስ ዘመን አገር ምድሩ ጥጋብ ነግሰበት .... ህዝቡም በረከት በዛለት ሃብታም ሆነ ! በቃ ይሄ ለኦሮ ለእለት ጉርስ ለዓመት ልብስ መጨነቅ ቀረና ህዝቡ ስእል ሙዚቃ ቅኔ ፍልስፍና ሆነ ስራው...ያው ስጋ ሲሞላለት ነፍስ ሃቄን ትጠይቅ የለ ... (ኪነጥበብ የብሶት መግለጫ የሃቅ መተንፈሻ መሆኑ አንድ ነገር ሁኖ ለአንዲት አገር የእድገት የብልፅግና ምልክት መሆኑን ያዙልኝ እዚህ ጋ)

እንግዲህ ንጉስ አክባር ቤተ መንግስት ውስጥ በምድር ላይ ምርጥ የተባሉ ጠቢቦች ሁሉ በንስር አይን ከያሉበት ተለቅመው ሳይንሱን አርቱን ሲያጎርፉት ይውላሉ .... አንቱ የተባለ የሂሳብ ሊቅ ፣ በዘመኑ አለ የተባለ ሙዚቀኛ ፣ ሰዓሊ .... ባለቅኔ በቃ ስብስብ አድርጎ በዙሪያው አስቀምጧቸዋል ! ታዲያ ማንም በአገሪቱ ውስጥ ለየት ያለ ጥበብ አለኝ የሚል ሰው ወደቤተ መንግስቱ የመግባት ጥበቡንም የማቅረብ ፈቃድ ያገኛል .... ንጉሱ ለጥበብ ሚች ነበረ ! ከጥበበኞች ጋር እንደጓደኛ ነው የሚቀራረበው !

አንድ ቀን ታዲያ መግቢያችን ላይ ያየነው ሰው ‹‹ለየት ያለ ብቃት አለኝ ለንጉሱ ላቅርብ ›› በማለት ንጉሱ ፊት ቀረበ ‹‹ እስቲ ጥበብህ ምንድነው ወዳጀ ›› አለ ንጉስ አክባር የእንግዳውን ልዩ ጥበብ ለማየት ቸኩሎ ‹‹አመሰግናለሁ ንጉስ ሆይ .....እ.....የኔ ብቃት እንግዲህ ....በአይነቱም ሆነ በብዛቱ ለየት ይላል ንጉስ ሆይ ....አስራ ስድስት ቋንቋችን አቀላጥፌ እና አሳክቸ እናገራሁ ... ከንጉስ የቅኔ እና የቋንቋ ጠቢባን አንድኛቸው እንኳን የአፍ መፍቻ ቋንቋየ የትኛው እንደሆነ መለየት እስከማይችሉ ሁሉምን ቋንቋወች እንደአፍ መፍቻ ቋንቋየ አሽሞነሙናቸዋለሁ ›› ሲል በኩራት ተናገረ !!

‹‹ንሳ አንተ! የቋንቋ ሙህራኖቸንና ባለቅኔወቸን ጥራ›› ሲል አሳላፊውን አዘዘ ንጉሱ

የንጉስ አክባር የቋንቋ እና የቅኔ ጠቢባን ... በሰልፍ .....እያደገደጉ ገቡና ቦታ ቦታቸውን ያዙ ! እነዚህ ጠቢባን እንኳን ንግግርን ሰምተው የአፍ መፍቻ ቋንቋ መለየት ይቅርና ገና ከፊት ገፅታው በፊታቸው የቆመውን ሰው ቋንቋ አብጠርጥረው ያውቃሉ ተብለው የሚሞካሹ ናቸው ! በዘመኑ የነበሩ የአለም ቋንቋወችም ላይ ጥልቅ ጥናትና ምርምር ያካሄዱ ነበሩ ! በዓለም ላይ እግር እስኪቀጥን ቢዞር ከእነዚህ ጠቢባን የላቀ ችሎታ ያለው ሰው ማግኘት ዘበት ነው !

‹‹መልካም..... በል እንግዲህ በምታውቀው ቋንቋ ሁሉ ተቀኝ ጠቢባኖቸም አፍ መፍቻ ቋንቋህ የትኛው እንደሆነ መለየት ካቃታቸው እንደ ›› ሲል ንጉሱ እንግዳውን በፈገግታ እየተመለከተ አዘዘው ፈገግታው ከእኔ ጠቢባን እንኳን ይች ሚስቱ አባሳጭታው ከጉድጓዱ የኮበለለ ቁጫጭ መለየት እያቅታቸውም አይነት ትእቢት ነበረች ! በጠቢባኑ ይተማመናላ !!

‹‹ ንጉስ ሆይ በነፃማ አይሆንም በውርርድ መሆን አለበት ›› ሲል ቅድመ ሁኔታ አስቀመጠ እንግዳው ‹‹ ይችን ይወዳል አክባር ...ንሳ አንተ የወርቅ ሳንቲም አምጣ ››

ውርርዱ በወርቅ ሳንቲም ...ተጀመረ ...ባለአስራ ስድስት ቋንቋው ሰው በአስራ ስድስቱም ቋንቋ ይናገራል .....ከእነዚህ ቋንቋወች የአፍ መፍቻ ውን ጠቢባኑ ተራ በተራ ይናገራሉ..... ከተሳሳቱ የወርቅ ሳንቲማቸውን ሰውየው ይበላቸዋል !ካወቁት ሰውየው ይበላል ! እንግዲህ አስቡት አንድ ሰው በአማርኛ ፣ በኦሮምኛ ፣ በትግርኛ ፣ በአፋርኛ ፣ በጉራጊኛ ፣ በወላይትኛ .....በእንግሊዝኛ ፣ በበቻይንኛ ወዘተ ቢናገርና አፍ መፍቻ ቋንቋው የቱ እንደሆነ ለመለየት እንደመሞከር በሉት .....

ጨዋታው ደራ ...አስገራሚው ነገር ንጉሱን ጨምሮ ከንጉሱ ጠቢባን ሁሉም የሰውየውን አፍ መፍቻ ቋንቋ ሊለዩት አልቻሉም !! ሁሉንም ቋንቋ ፅድት አድርጎ እንደቋንቋው ባለቤቶች ነበረ የሚናገረው ..... አንዲት እንኳን መለያ ሳይኖር አስራስድስት ቋንቋ በሚገርም ልሳን በሚገርም ብቃት ጥርት አድርጎ ያንተረትረዋል !! ጥርግርግ አድርጎ ሳንቲማቸውን በላው ሰውየው !

አንድ ታዋቂ ባለቅኔ የንጉሱ የቅርብ ባለሟል ብቻ ሁኔታውን ዝም ብሎ እየተመለከተ ውርርዱ ውስጥ ሳይገባ ቆየ ... ንጉሱ ይህን ባለቅኔ እንዲወራረድ ቢጋብዘውም እንደማይወራረድ አሳወቀ ‹‹በቃ ፈርቶ ነው ›› ተባለ ! በኋላ ድፍን ጠቢብ ሁሉ መሸነፉን አምኖ ለእንግዳው ክብር ምግብና መጠጥ በገፍ ቀርቦ ጨዋታው ደራ ..... ሁሉም ሞቅ እንዳለው ይህ ጥጉን ይዞ ሲታዘብ የነበረው ባለቅኔ ከመቀመጫው ድንገት ተነሳና የባለብዙ ቋንቋውን ሰው እግር የሚያልፍ መስሎ እረገጠው ....ይቅርታም ሳይጠይቀው አለፈ ....

እንግዲህ በባህላቸው ይህ ታላቅ ውርደት መናቅ እንደውም ስድብ ነው...ኧረ ረጋጩ ይቅርታ ካልጠየቀ በሻሙላ እስከመፋለም ሊያደርስም ሁሉ ይችላል ..... እናም ባለብዙው ቋንቋ ሰው ደሙ ፈላ እሳት ለብሶ እሳት ጎርሶ ‹‹ አንተ የማትረባ ደደብ ....በምን ብትንቀኝ ነው እንዲህ የምታዋርደኝ ...ጣሳ ራስ ዘባተሎ እኔ እኮ ታላቅ ጠቢብ ነኝ አንተ ብሎ ሰው ናቂ ›› ብሎ በስድብ አጥረገረገው .....

ባለቅኔው ረጋ ብሎ ስድቡን እንደምርቃት ሲያደምጥ ቆየና ወደተሰበሰቡት ሰዎችና ወደንጉሱ ዙሮ ‹‹ንጉስ ሆይ አሁን የሰውየውን አፍ መፍቻ ቋንቋ ለማወቅ እወራራዳለሁ ›› ብሎ የወርቅ ሳንቲሙን ቁጭ አደረገ ....እንደገና አዳራሹ ሁካታና ውርርድ ሰፈነበት ! ‹‹ጥሩ በል እንቀጥል ››አለ ባለቋንቋው ብስጭቱን ወዲያው ረስቶ እናም ቋንቋወቹን ያቸሃደጉዳቸው ጀመረ ባለቅኔው አንዱ ቋንቋ ላይ ሲደርስ ‹‹ይሄ ነው አፍ መፍቻ ቀዋንቋህ ወዳጀ ›› አለው ! ባለቋንቋው ደነገጠ ምክንያቱም ባለቅኔው ቋንቋውን በትክክል አውቋት ነበር ! ‹‹ በትክክል አውቀኸዋል .....ግን ይሄ ሁሉ ጠቢብ ያላወቀውን እንዴት ልታውቀው ቻልክ ›› ሲል በግርምት ጠየቀ እንግዳው ! ንጉሱን ጨምሮ ሁሉም ለመልሱ ጓጉ

ባለቅኔው ረጋ ብሎ እንዲህ አለ ‹‹ ቋንቋ በቃል ተከሽኖ በድምፅ ተሸፍኖ ከሰሚው ይሰወራል .....ሰው አፍ ከፈታበት ቋንቋ በፈለገው ቅላፄ የፈለገ ቢደበቅ አፍ ከፈታበት ባህሪ ግን የቁርጥ ቀን ሲመጣ መደበቅ አይቻለውም ... ስትበሳጭ ወይ ስትደሰት ነው ወደማንነትህ በትክክል የምትመለሰው !! አየህ ...ቅድም ስትበሳጭ ግልፍ ብሎህ የተሳደብከው በዚሁ ቋንቋህ ነበር ያ ነው ማንነትህ ›› በእርግጥም የሰውየው አፍ መፍቻ ቋንቋ ባለቅኔው ያለው ቋንቋ ነበር !

እንግዲህ እኔም እዚህ አገራችን ላይ ስታዝበ ጨዋ ፣ ታጋሽ ፣ የሰለጠነ ሰው ለመሆን የምናደርጋት ጥረት ድንገት ሃይማኖት ፣ዘር ፣ ፖለቲካ ወይም ሌላ ጉዳይ ሲነሳ .....ማንነታችን ሳትወለወል ሳትቀባባ ከነብጉሯ እንደፊጠራት ፈትለክ ብላ ከውስጣችን ትወጣና አፍ መፍቻ ባህሪያችንን ቁልጭ አድራጋ አደባባይ ታሰጠዋለች !! አፍ መፍቻ ባህሪ አፍ መፍቻ ቋንቋችን ሁና !

እና ወዳጀ ስትደሰትም ስታዝንም የስሜት ጎርፍህ እስክታልፍ ዝም ብትል የወርቅ ሳንቲም ባይኖርህ እንኳን ወርቅ ማንነትህን ጠራርጎ ከሚወስደው በሂወት ውርርድ ክብርህን ከሚያስበላህ ግልፍታህ ኋላ ‹‹ሊያልፍ ውሃ አደረገኝ ደሃ ›› ተረት እንዳትተርት ይረደሃል ....ብየ ይችን ታሪክ እንዳነበብኳት አስነበብኩህ !! የወዳጅ ሃቄን !! በል መልካም ሰኞ ይሁንልህ ! በይሁንልህ ውስጥ ይሁንልሽ ተረሳ ብለሽ አኩርፊ ደግሞ ሃሃሃ !

‹ ያሉት ከሚጠፉ የወለዱት ይጥፉ ››
(አሌክስ አብርሃም)

ሪሃና ጃቢር ትባላለች ! ኢራናዊት ናት ...እናም ‹‹ሊደፍረኝ ስለሞከረ ራሴን ለመከላከል ›› በሚል ምክንት አንዱን ወንድ በስለት ወግታ ገደለችው ! (ያው ሰሞኑን ዜናውን ሰምታችሁታል) የኢራን ፍርድቤት ታዲያ በስቅላት እንድትቀጣ ወሰነባትና ባለፈው አርብ በስቅላት ተቀጣች ! የገረመኝ የዚች ሴት ነገር ምን መሰላችሁ ...ከሞት የመትረፍ እድል ነበራት ....በኢራን ህግ መሰረት አንድ ሰው በግድያ ምክንያት ሞት ቢፈረድበት የሚች ቤተሰብ ‹‹አፉ ብየዋለሁ ›› ካለ የሞት ፍርዱ ይነሳለታል ! በዚች ሴት ጉዳይም የሚች ቤተሰቦች ‹‹አፉ ›› እንዲሏት ተጠይቀው ነበረ ....

‹‹ልጃችንን የገደለችው ሆነ ብላ በሌላ ቂም ከኋላው በመውጋት ነው ...እርሷ ግን ‹ሊደፍረኝ ሞክሯል › ብላ ነብሱን ብቻ ሳይሆን ስሙንም ማጥፋቷ አበሳጭቶናል ... ትክክለኛውን ነገር ትመን ...ሊደፍራት መሞከሩን ውሸት መሆኑን ገልፃ ይቅርታ ትጠይቅ ይቅር እንላታለን ›› ሲሉ ምርጫ አቀረቡላት
እናም ሪሃና እንዲህ አለች ‹‹ ይቅርታ አልጠይቅም ሊደፍረኝ ሞክሯል ገድየዋለሁ ይቅርታ አልጠይቅም ››

እናም ከዚሁ የማይቀየር ሃሳቧ ጋር የኢራን መንግስት በስቅላት ቀጥቷታል !! አለም ስለተጣሰው ሰብአዊ መብት እየጮኸ ነው ...እኔ ደግሞ ይች ሴት በእርግጥ የመደፈር ሙከራ ተደርጎባት ከሆነ ...በሰብአዊ መብት ስም ከሚንጫጫው አለም በላይ ለሴቶች መብት መከበር የማይረሳ አሻራዋን እንዳስቀመጠች ይሰማኛል !!

ለመኖር ስትል በጓዳ የተደረገባትን ግፍ አልሸፋፈነችም ! አንዳንዴ ሰው ምን ይለናል ማህበረሰቡ እንዲህና እንዲያ ብሎ ያዋርደናል ...ስራ እናጣለን ቤተሰብ ያዝንብናል በማለት ህመማቸውን በየጓዳው አፍነው ዝም ለሚሉ ሴቶች ....ሰው ስላመነበት ጉዳይ እንዲህም ሕይወቱን እንደሚከፍል ማወቁ ትልቅ ትምህርት ይመስለኛል ! ወንጀሉን ቃሏ እውነትም ሆነ ሃሰት ቃሏን በመቀየር ሊቀር የሚችለውን የሞት ፅዋ በድፍረት ተጎንጭታለች ! የሆነ ሁኖ በማንኛውም መንገድ ቢሆን መግደልንም ሆነ የሞት ፍርድን አልደግፍም ...
ከሕይወት የገዘፉ ቃሏ ነገር ገርሞኝ እንጅ !
በአገራችን ካለጥፋትህ የመታሰር አስር ጥቅሞች .....
(አሌክስ አብርሃም)

1 ኛ . የቤት ኪራይ አይጨመርብህም እንደውም አትከፍልም !
2 ኛ . ሁልጊዜም ለመፈታት ተስፋ ታደርጋለህ
3 ኛ . ተሰልፈህ ታክሲ አትጠብቅም
4 ኛ . መንገድ ላይ የማትፈልገውን ሰው አታገኝም
5 ኛ. ያለዎት ቀሪ ሂሳብ የምትለዋን ሴትዮ አትሰማም የስልክ ካርድም መሙላት አይጠበቅብህም
6 ኛ . ልደት ክርስትና ፀበል ቤት ሰርግ ምናምን ባትሄድ ማንም አይቀየምህም ታስረሃላ
7 ኛ. ምግብ ቤት ለምግብ ቤት አትዞርም

8 ኛ. ሰወች የሚያወሩህ የተወሰነ ሰአት ብቻ ስለሆነ አትሰለችም

9 ኛ . ስራ እሄድም ደመወዝ ደረሰ አልደረሰ አያሳስብህም

10 ኛ . ዙሪያህን ያሉት ሰዎች በትክክል ምን እንደሚሰማህ ያውቁልሃል እስረኛ ናቸዋ !

ችግሩ ግን ምን መሰለህ ...ከላይ ያሉት ዝርዝሮችን ሁሉ በግድ መቀማትህን ስታውቅ ...የቤት ኪራይ ባለመክፈልህ አትደሰትም በነፃ ማግኘት ለሚገባህ ነፃነት እድሚህን እየከፈልክ ነውና!! ....ሁልጊዜ ለመፈታት ተስፋ ማድረግህ ግን በእርግጥም ጥሩ ነገር ነው መታሰሩን ሳያውቅ የሚንከላወስ እስረኛ ስንቱ መሰለህ ... ተሰልፈህ ታክሲ አትጠብቅም ... አንተ ስትፈጠር የተሰጠህ የሰበአዊ መብት ታክሲ ላይ እንዳትሳፈር የታገድክ ነህና ...መንገድ ላይ የማትፈልገውን ሰው አታገኝም ...የማትፈልጋቸው ሰዎች እጅውስጥ ነሃ ....እና ምን ልልህ ነበር ...ዛሬ አንድ የታሰረ ወዳጀን ጠይቄ መጣሁ ....

‹‹መታሰር እንዴት ይዞሃል›› ስለው

‹‹ምንም አይል ›› አለኝና ቀጠል አድርጎ እንዲህ ሲልጠየቀኝ

‹‹አንተስ ጋ እንዴት ነው ? ››

‹‹ ት።ች።ት። እና ስ።ድ።ብ ››
አጭር ልብ ወለድ
(አሌክስ አብርሃም)

‹‹ልጅቱ ያዘዝነውን ክትፎ እየበላን እንዳለ ...ያዘጋጀችውን ጉርሻ ጠረንቢዛው ላይ ወዳል ሰሃን በልሳ ፊት ለፊታችን ተቀምጠው በፍቅር የሚያወሩትን ፍቅረኞች የጎሪጥ እየተመለከተች .....እንደድሃ አጥር ዘር ዘር ባሉ ጥርሶቿ ፈገግ አለችና ... ‹‹እኔኮ ግርም የሚለኝ የወንዶች ውሸታምነትና ‹ቁሌታምነት› ነው ›› አለች ... ከእውቀት እውቀት ከመልክም መልክ ከአመልም አመል የነሳት ልጅ ስለሆነችና የሚቀርባት ወንድ ስላጣች ቀንታ ነው ብየ አሰብኩ ››

የሚል አንድ ድርሰት ፃፍኩ እንበል ...ምሳሌ ነው ! እናም አስተያየት ሰጭወች መጡና እንዲህ አሉ ...

1 ዋው እጅህ ይባረክ በጂቱ ፈገግ አደረከኝ (ደብሮኝ ነበረ)

2 አንተ ደደብ የሴት ልጅ ክብር አልገባህም :: እቤትህ ቁጭ በልና አንብብ ዝም ብለህ አትዘባርቅ !

3 አሌክስ የቀረፅካት ገፀ ባህሪ ከምትለው ነገር ጋር አብራ አትሄድም ... ለምሳሌ የበአሉ ግርማ ከአድማስ ባሻገር ላይ ሉሊትን ታውቃታለህ አይደል ...እሷ እድገቷ አኗኗሯና የምታደርገው ነገር ተፃምሮቱ .....እና ስትፅፍ ገፀ ባህሪያቶችህ እራሳቸው እንዲናገሩ እንጅ አንተ ጣልቃ አትግባ

4 ስማ አሌክስ... መልክ እንደተመልካቹ ነው ..ላንተ ያላማረህ መልክ ለሌለው ውብ ሊሆን ይችላል

5 ስርዓተ ነጥብ አለመጠቀምህ መልእክትህን አንባቢህ አንተ ባሰብክበት መንገድ እንዳይረዳው አድርጎታል...አሌክሶ ደግሞ ለምንድነው ጠረንቤዛ የምትለው ? ጠረጴዛ ነው የሚባለው !

6 ‹ቁሌታም › የሚለው ቃል ካንተ አይጠበቅም እንደውም አንተ አሌክስ አይደለህም አታጭበርብር

7 እፀብ እና ድንቅ ሁኝ ተፈጥሪያለሁ ይላል መዝሙረኛው ዳዊት ...አንተ የፈጣሪን ፍጡር የምትሳደበው ማን ሁነህ ነው !!

8 አገራችን በስንት ችግር ተወጥራ አንተ ስለሴት ጥርስ ስለሴት ቂ ..ትፅፋለህ ...ተረታም

9 ይሄ አሌክስ አብርሃም የሚባል ልጅ ግን አጨብጫቢዎቹ ጎበዝ ቦበዝ ሲሉት ጨርሶ ተጨማለቀ

10 አሌክሶ በፊት ከምትፅፊያቸው አንፃር ሲታይ ትንሽ እየወረድሽ ነው ...ጭብጨባ እንዳያጠፋሽ ወደበፊቱ ብቃትሽ ተመለሽ ..ይሄን እኔ ራሱ በግራ እጀ እፅፈዋለሁ....እና የፊደል ስህተት ታበዛለህ ለምሳሌ ‹ጠረንቤዛው ላይ ወዳል ሰሃን መልሳ ለማለት በልሳ ›› ነው ያልከው ...እያየህ እንጅ አሌክ አትቸኩል የት ለመድረስ !

11. አሌክስ እኔ የዙሪያ ወሬ አልወድም ፊት ለፊት ልምከርህ ትንሽ ትእቢት እየጀማመረህ ነው አንተ የትኛው እውቀት ኦሮህ ነው ከእውቀት እውቀት የላትም የምትለው ... እውቀት እኮ ተራ ነገር ነው ማንም ሁኔታው ከተመቻቸለት መማር አያቅተውም ..

12. ‹‹11››ቁጥርየ ያልከውን እጋራለሁ ሰውየው ትእቢት ጀማምረዋለች

13. ቁጥር ‹12› አሌክሰንማ ለቀቀቅ ቀሽሞች !

14. እኔኮ የሚገርመኝ ይሄ 12 ቁጥር የሚባል ሰውየ አሌክስን ተቃውሞ የፃፈን ሰው ሁሉ እያጀበ መጮሁ ነው !

15 ኦ በቀጣዩ ምርጫ በመሳተፍ በአገራችን ጉዳይ የበኩላችንን እንወጣ

16 አንተ ሰውን ብሎክ እያደረክ ፀሃፊ ነኝ ትላለህ ...እነበአሉ ግርማ ጥይት ተቋቁመው ፅፈዋል እንኳን ትችት ...ተረታም ! መክሸፍ እንደአሌክስ አብርሃም !!

17 አሌክሶ የምትጠቀማቸው አረፍተ ነገሮች ትንሽ ረዘም ይላሉ ...አጠር ባለ አረፍተ ነገር ብዙ ሃሳብ መግለፅ የሚሻል ይመስለኛል ...አላስፈላጊ ቃላት እና ይሄ ወደጎን የምትደረድረው ነጥብ የፅሁፉን አሰልችነት ከፍ የሚያደርገው ይመስለኛል

18 .ቁጥር 17 ነጥብ ምናምን እያልክ አትቀባጥር አዋቂ ከሆንክ ፅፈህ አሳየና እዚህ አገር ትችት ብቻ ነው የምታውቁት ምቀኞች! ሰው ሲወደድ አትወዱም !

19 አሌክሶ ተንዛዛ !ስራ ገቢ ስለሆንኩ አጠር እያደረክ ብትፅፍልን ...ገና ብዛቱን ሳየው ነው ማንበብ ያቆምኩት

20 አሌክስ የዛሬ አመት ሴቶችን የተሳደብከው ትዝ ይልሃል ..ሴት እኮ እናት ሴት ሚስት እህት ናት ...

21 አሌክሶ ከዘመኑ ሰወች ጠጋ ብለሻል መሰለኝ ...በዚህ ሰአት ለሴት ክትፎ የሚጋብዝ ኢትዮጲያዊ እንድም የገዥው ሆዳም ቡችላ ካልሆነም የገዥው መደብ ነው!

መደምደሚያ - ከላይ ከተዘረዘሩት አስተያየት ሰጭወች በመነሳት እስኪ ቁጥሩን በመጥቀስ ለመማማር የሚረዳንን አስተያየት ስጡ... በሌላ አባባል ትችትና ስድቡን ለይታችሁ አሳዩኝ !! ብዙ ወዳጆቹ ትችት ለመቀበል ዝግጁ አይደለህም የሚል አስተያየት ይሰጡኛል ! እናተ ብትሆኑ የቱ ትችት የቱ ስድብ ይሆንባችኋል ...በዚህ ምሳሌ አስተምሩኝ ! ከምር አስተምሩኝ ...ወይ እኔ ወይ አስተያየት ሰጭወቹ ‹‹ትችትና ስድብ ›› መለየት አቅቶናል !!

አንተስ ራስህ ?!

(አሌክስ አብርሃም)

....እንግዲህ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አብረውት በተለያዩ ቦታወች ሲዞሩ ተዓምራቱን ሲመለከቱ በራሳቸውም እጅ በሰጣቸው ስልጣን ተዓምር ሲደርጉ የቆዩ ደቀመዛወሙርቱን አስከትሎ ፊሊጶስ ቂሳሪያ የሚባል አገር ደረሰ ! እና ደቀመዛሙርቱን እንዲህ አላቸው ...

‹‹እንደው ለመሆኑ ሰወች እኔን ማን ይሉኛል ›>..... ቃል በቃል ‹‹ሰዎች የሰውን ልጅ ማን ይሉታል ›› ደቀመዛሙርቱ የሚባለውን ለመንገር ተራኩቱ

‹‹አንዳንዶች መጥምቁ ዩሃንስ ነህ ይሉሃል ››

‹‹ኤሊያስም ነው የሚሉ አሉ ››

‹‹ከነቢያት አንዱ ተገልጦ ነው ይላሉ .....›› ሁሉም የሰሙትን ነገሩት ...ዝም ብሎ አዳመጠና (መቸም እንኳን ያኔ ዛሬም ከልባችሁ የምትነግሩትን ሲሰማ የጉድ ነው) ሰማቸው ሰማቸውና ... እንዲህ ሲል ጠየቀ

‹‹ መልካም ! እናተስ ራሳችሁ እኔን ማን ትሉኛላችሁ ››

ጭጭ አሉ ደቀመዛሙርቱ !

ሰምኦን ጴጥሮስ የሚባለው ደቀመዝሙር ‹‹አንተ ክረስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ ›› አለ !! ጴጥሮስ ደፋር የተሰማውን የሚናገር ለማጥፋትም ለንስሃም ቅርብ ደቀመዝሙር ነበር (እኔማ ስወደው)

ክርስቶስቶስም ‹‹ የዬና ልጅ ስምኦን ሆይ በሰማያት ያለው አባቴ እንጅ ስጋና ደም ይህን አልገለጠልህም !! አንተ ጴጥሮስ ነህ በዚችም አለት ላይ ቤተክርስተያኔን እሰራለሁ ..የገሃነም ደጆችም አይችሏትም !! ›› ....በኋላ ሳየው ጴጥሮስ ማለት ለካ ጠንካራ አለት ማለት ነው .....

ታላቁ መፅሃፍ ታዲያ ለእኔ ከዚህ አጭር የሚመስል ዘላለማዊ ንግግር ምን አስተማረኝ መሰላችሁ .....ለካ ስለተባለው ነገር ማውራት ‹‹እንዲህ ይላሉ እንደዛ ይባላል›› ማለት ...ማንም ሰው ይችላል !! በድፍረት እና ፊት ለፊት የራስን እውነት ያመኑበትን ቃል መተንፈስ ግን ሃይል ይጠይቃል ...እምነት ይጠይቃል እናም ጠንካራ እውነት ለትውልድ የሚተርፍ ሃቅ የሚመሰረተው አሉ ተባለ በሚሉ ሰወች ላይ ሳይሆን የተገለጠላቸውን ... ሃላፊነት ወስደው በግልፅ በሚስቀምጡ አለት መንፈስ ባላቸው ሰወች ላይ ነው .... !!

ዘመኑን ስታዩት ሬዲዮውን ክፈቱት አሉ ተባለ ...ቴሌቪዥኑን ክፈቱ አሉ ተባለ ...መፅሔት ጋዜጣው አሉ ተባለ .... ፖለቲካው አሉ ተባለ ...ስፖርቱ አሉ ተባለ ...ትምህርት እራሱ አሉ ተባለ ያስተምርና የአሉ ተባለ መምህራን ያመርታል
‹‹እና እናተስ ምን ትላላችሁ ›› ብላችሁ ብትጠይቁ መልሱ በጣም ይገርማል

‹‹ እንግዲህ እኛን አንዳንድ ሰወች እንደሚሉን..... ›› ብለው... አሉ ተባለ ..... ኡኡኡኡኡኡ ኧረ እራሱ የዘመኑን ድርሻ የሚል ነገ በእርሱ አለት እሳቤ ጠንካራ ፍልስፍና ላይ የሚቆም ትውልድ ከየት ይፈጠር .....? እስቲ አሉ አትበለኝ አንተ ራስህ ምን እንደምትል ልስማህ ...እስኪ እነትና አትበለኝ አንተ ራስህ ማነህ ? እስኪ አንተ ራስህ የምትለውን ፃፍ ራስህ የምታስበውን ሳል ...ተናገር .....አሉ አሉ አሉ ....እና ታዝበህ ከሆነ አሁን እኔ ምን ብየ ተነሳሁ ....‹‹ መፅሃፍ ቅዱስ እንዳለው !! ›› እንዳለው ብየ ታሪክ አውሪ ሁኜ ከቀረሁ መቸም ቢሆን መፅሃፉ እንዳለው እንደማልሆንም ማወቅ ደጉ ነገር ነው ወዳጀ ! በጎ ስታጣቅስ ለመኖር እንደማለት !! አለበለዚያ እዚህ ቃል እንዳሳመርክ መኖር ነው !! እላለሁ ....ማን ..... እኔ ! እኔ ራሴ !!

ፍቅር ምን ያደርጋል !
(አሌክስ አብርሃም)

አባባ ሙጋቤ የዚምባብዌው ፕሬዝደንት አዲስ ህግ አውጥተዋል በዩኒቨርስቲወች ውስጥ መሳሳም ክልክል ነው !! ‹‹ እያንዳንድሽ ምድረ የዩኒቨርስቲ ማቲ እኛ በስንት ብድርና እርዳታ ትማሪያለሽ ብለን ብለን በገነባነው ዩኒፈርስቲ

ከንፈርሽን አሞጥሙጠሽ መሳሳም ከሆነ ስራሽ ወዮልሽ ...

ካሁን በኋላ ከንፈሬ ተመቸኝ ብለሽ ዩኒቨርስቲወች ውስጥ መሳሳም ወንጀል ነው ! ሌላም ከስነስርአት ያፈነገጠ ነገር ማድረግ ቅጣቱ የከፋ ነው !! ደሃ አርፎ ሲማር እንጅ ሲሳሳም አያምርበትም መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገራት ተርታ ስንሰለፍ እንሳሳማለን እስከዛው አንድ ተማሪ ይሳሳምና ውርድ ከራሴ ጨረስኩ !››

ይሄ ህግ በዚምባቡየ አነጋጋሪ ሁኗል ! ጠንክረን ተምረን የኒቨርስቲ ስንገባ እንሳሳማለን ብለው ተስፋ ያደረጉ ተማሪወች ሁሉ ብስጭት ...ብስጭትጭት ብለዋል ! የዝንባቡየው የውጭ ግንኙነት መርህ የሚያበሳጫቸው ምእራባዊያንም ጉዳዩን እያናፈሱና ‹‹ሙድ›› እየዬዙበት ይገኛሉ !

የዝንባቡየ ወጣቶች ተበሳጭተዋል ... ‹የመሳሳም ነፃ አውጭ ግንባር የሚባል አቋቁመው ‹‹ጨቋኙን ›› የሙጋቤ አገዛዝ ለመገርሰስ ጫካ እንዳይገቡ ያሰጋል (ሃሃሃ) አንድ የዝንባቡየ ገጣሚም እንዲህ ሲል መግጠሙን የወሬ ምንጮቻችን ሹክ ብለውናል

‹‹ፍቅር ምን ያደርጋል ትላለች ባልቴት
እንክት አርጋ በልታ የራሷን በፊት ››

ሙጋቤን ማሸሞሩ ነው !! በነገራችን ላይ የኢትዮጲያ ወንጀለኛ መቅጫ ህግም በአደባባይ ከንፈር ለከንፈር መሳሳምን ይከለክላል አሉ ...እውነት ነው ? ከሆነ ሙጋቤን ቀድመናቸዋል !እንግዲህ እንዲያ ኮሆነ ህጉ ሚሊኒየም አዳራሽና ስቱዲየም ለእስር ቤትነት ይዘጋጁልና ...ማን ይተርፋል !

የአመፅ ጥሪ !!
(አሌክስ አብርሃም)

በቃ ርእሱን ስታዩ ሽምቅቅ አላችሁ አይደል ? .... ግራና ቀኝ ዞር ዞር ብላችሁ ሰው አለመኖሩንም

አረጋገጣችሁ ችግሩ ከአይናችሁ መስሏችሁም አይናችሁንም አሻሻችሁ ….. (ሃሃሃ) እስቲ ምን ትሆኑ ይሄው ለአመፅ ጠራኋችሁ !! ! ጉዳዩ ወዲህ ነው ጓዶች ! እንደው አመፅ ፣ ህገ መንግስቱን በጉልበት መናድ ፣ ዘር ፣ ሃይማኖት ፣ ብሔር ፣ ምርጫ የሚሉ ቃላት በተነሱ ቁጥር ተሸማቀን አለቅንኮ ጎበዝ ! ‹‹ የሚያስፈራ ዝምታ እንጅ የሚያስፈራ ቃል የለም ›› ብየ ታሪካዊ ጥቅስ ላጣቅስ እንዴ ? ይሄው አልኩላችሁ !

እ…… ወደተነሳሁበት ሃሳብ ስመለስ ዛሬ የፈለኳችሁ ከላይ እንደገለፅኩት ‹‹ለአመፅ ›› ነው ! (አይይይ ምንድንው አስር ጊዜ መደንበር ቆፍጠን በሉ እንግዲህ አመፅ ነው ብያለሁ አመፅ ነው) በቃ ብትችሉ ሁላችሁም ጓደኞቹ ድብን ያለ አመፅ በማመፅ በጉልበት የምንንደው አንድ ጉዳይ አለ !

እዚህ ፌስ ቡክ ላይ ከመጣሁ እንግዲህ ወደ ሁለት አመት ሊሆነኝ ነው ….መጀመሪያ አካባቢ ስመጣ የፌስቡክ አየር ስላልገባኝ ቀልቀል ብየ ነበር ….. አሁን ግን እድሜ ሲገፋ እርጅናንም በሁለት አመት ስጠጋት ሰከን ብየ ጨዋ ልጅ ሆንኩ … ተረጋጋሁ (አሁን ነበር ማግባት ሃሃሃ) ምናባቴ ይሻለኛል ቁም ነገር ላወራ እነሳና መሃል ላይ ይዘባረቅብኛል ! ይሁን እንግዲህ አመል ከሆነ ቻሉኝ !

እና ዋናው ነጥቤ ምን መሰላችሁ ….. ፌስ ቡክ ላይ በምርጥ ፅሁፋቸው በሚያነሷቸው ነጥቦች ብስለትና ውበት የምደመምባቸው አሪፍ አሪፍ ፀሃፍት ሁሉ ቀስ እያሉ እንደዳውዶ መሬት እየተንሸራተቱ ስድብ እና ዘለፋ ውስጥ መነከራቸው ግራ አጋባኝ ! ስድቦቹ ራሳቸው የፀያፍነት ደረጃቸው ከፍ እያለ ከግለሰብ ወደቤተሰብ ….ከቤተሰብም ወደትውልድ ቦታ….. ቋንቋና ብሔር …. ብሎም ወደአገር እያደጉ ፌስቡክን የብልግና ጥግ ሊያደርጉት ምንም አልቀራቸው ! በስራም በእድሜም ትልልቅ የምንላቸው ሰወች ሁሉ ‹‹አባባ ማሙሽ ›› ሁነው ቁጭ አሉ ! ታዲያ ይሄ ነገር ያማረራቸው አንዳንድ ሰዎች ፌስቡክን የጎሪጥ ማየትና የስድብ ፍንጣሪ ፍራቻ ጥጋቸውን ይዘው ቁም ነገራቸውን ሳያካፍሉን የመቅረታቸው ነገር ለእኔ አሳዛኝ እየሆነብኝ ነው !

አንድ ነገር ልንገራችሁ …ፌስቡክ ላይ ታላላቅ ሰወችን መፍጠር የምንችለው እኛ ነን ! (ማካበድ አይደለም) አንድ ምሳሌ ላንሳ በአማራ ክልል በተለይ ለታዳጊዎችና ወጣቶች የሚዘጋጅ የኪነጥበብ ውድድር ነበር …. በስነፅሁፍ ፣በስእል፣በቅርፃቅርፅ ፣ በድራማና በሙዚቃ በየአመቱ ውድድር ይካሄዳል …ይህ ገና ኢቲቪ ‹አይዶል› ምናምን ሳይጀምር በፊት ነው ! ታዲያ የአሸናፊ ወጣቶች ስራ ይሰባሰብና ‹‹መቅረዝ ›› በምትል መፅሃፍ በአንድ ላይ ታትሞ ለአንባቢ ይቀርባል …ያኔ ፌስ ቡክ አልነበረም !

እነዛ መድረኮች የጥበብ ሰዎችን ከህዝብ ማግኛ አይነተኛ መንገዶች ነበሩ …ህዝቡ የጥበብ ሰዎቹን አክብሮ ሞራል ይሰጣል ያበረታታል…….. እና ከያኔው መቅረዝ ላይ ስራቸው ታትሞ ካየኋቸው ፀሃፍት መካከል ዛሬ ላይ አንቱ የተባሉ በርካታ ደራሲያን አሉ…. እማኝ ጥቀስ ካላችሁኝ ….ዛሬ በስራዎቹ ጠብ እርግፍ የምንልለት ደራሲ አዳም ረታ አንዱ ነው …. የአዳም ረታን ስራ ለመጀመሪያ ጊዜ ያነበብኩት በዚች አሸናፊ የሆኑ ስራዎች በሚታተሙባት መቅረዝ መፅሃፍ ባልሳሳት ቅፅ ሁለት ላይ ነበር !! በዚሁ መፅሃፍ የአሸናፊወች ዝርዝር ውስጥ የምታገኙት ግሩም ገጣሚና ደራሲ ዶ/ር በድሉ ዋቅጅራ ደግሞ ‹‹እውን አባትህ አንተን ወለደ›› በሚል ግጥሙ ተካቷል !! (በኋላ ከፍ ያለ እውቅና እና አድናቆት በተቸረው ፍካት ናፋቂወች በሚል የግጥም መድብሉ ላይ የታተመ ግጥም መሆኑን ልብ ይሏል)

ሁለተኛ እማኝ ስንነቅስ …..የስድስት ኪሎ ካምፓስ ባህል ማእከልን የስነፅሁፍ ምሽቶች ለእናተ መንገር ለቀባሪ አረዳው ይሆንብኛል … የቀደመውን ለመታዘብ ንጉሱን የተገዳደሩ ደርጉን ‹የተሳፈጡ› እና ለህዝብ ነፃነት ቦብእራቸው የተፋለሙ እልፍ ትንታግ ወጣቶች የተፈጠሩበት መድረክ ለመሆኑ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ፕሬስ ያሳተመውን ‹‹የኮሌጅ ቀን ግጥሞች›› በማንበብ መረዳት ይቻላል …ወዲህ በእኛ ዘመን ደግሞ ….በእነዛ ምሽቶች በታዳሚወቹ የነጠረ አስተያየት እና ሙያዊ ሂስ የአድናቆት ጭብጨባና ማበረታቻ የተፈጠሩትን ፀሃፍት ቁጥር እንዘርዝር ብንል የትየለሌ ነው ….ብቻ እነ በእውቀቱ ስዩምን ጨምሮ በርካታ እሳት የላሱ ገጣሚያን አጭርና ረዣዥም ልቦለድ ፀሃፊወች ሌሎችም የኪነጥበብ ሰወች በእነዛ ምሽቶች ተወልደዋል !!

ዛሬስ ? ....ዛሬ ይህ መድረክ ጓዙን ጠቅልሎ ፌስቡክ ላይ ሁኗል መገናኛው ....አዎ አሁን ሁላችንም ያለንን ሃሳብ በተከሰተልን መልኩ በግጥም በልብወለድ ...በፎቶ ...በዘገባ ... በወግ የምናቀርብበት መድረካችን ፌስ ቡክ ሁኗል ! እርስ በእርስ ተዋወቅንበት የተቸገሩትን ለመርዳት የተጠራራንበት ....የተበደሉ ለምን ተበደሉ ብለን የጮህንበት መድረካችን ፌስቡክ ሁኗል ! በሃሳብ መስማማት በሃሳብ መቃረን ከተራው ኗሪ እስከትልቅ የመንግስት ሚንስትሮች በግንባር ገጥመን የምንነጋገርበት መድረክ ፌስ ቡክ ሁኗል ! ከእለት ውሏችን አዲስ ከገዛነው ልብስና ጫማ አዲስ ከተሰራነው የፀጉር ስታይል እስከዘመናት ታሪክና አለም አቀፍ ስኬቶቻችን የምንዘግብበት መድረካችን ፌስቡክ ሁኗል !! ሃዘናችንን በጋራ ተካፍለናል በደስታችንም ጨፍረናል እዚሁ ፌስ ቡክ ላይ !!

ታዲያ ከሰሞኑ (ነገሩ እንኳን ቆየ አሁን ላይ የተባባሰ ስለመሰለኝ እንጅ) በርካታ ወዳጆቻችን ምንም የማይፈይድ እና ተስፋ የቆረጠ ሰው አይነት አዝማሚያ ያለበት ፅሁፍ መለጠፍ ማብዛታቸው የሚያሳዝንና ይህን ትልቅ ማህበራዊ መድረክ የመጥፎ ተምሳሌት አምባ ማድረጉን ተያይዘውታል ! አላማቸው በግልፅ ትኩረት መሳብ እንደሆነ ግልፅ ነው .... ሳር ቅጠሉን በፀያፍ ስድብ በማጥረግረግ ህዝብን በጅምላ አላዋቂ መሃይም አድርጎ በማቅረብ ‹‹ህዝቡ ልክ ልኩን ሲነግሩት ይወዳል›› አይነት ልክ የለሽ ትእቢትና ለዛ ቢስ አፈንጋጭነት ታጥቀው ፌስቡክን በተኮላሸ ሽለላቸው እየሞሉት ነው ...

ትላንት ‹‹ወይ ዘንድሮ ሚስቴ ሆነች ዝንጀሮ ›› ብሎ ገጥሞ ትኩረት ያልሰጠነው ወዳጃችን ‹‹ አማራ ምናባቱ ወይም ትግሬ እንዲህ... ኦሮሞ እንደዛ ›› በሚል ፅንፈኛ ትችት ብቅ ሲል በኮሜንት እናጥለቀልቀዋለን .....በእርግጥ እኛ ኮሜንት የምንፅፈው ይህንን ሰው ከስህተቱ ለማረም አልያም ተብሳጭተን ምላሽ ለመስጠት ሊሆን ይችላል... ወደድንም ጠላንም ግን የሰጠነው አስተያየት ምንም ይሁን ምን ለተራ ድርጊቱ እውቅና ከመስጠት ውጭ ምንም አይፈይድም
‹‹ ፓ እንትና እኮ ለእንትና እንዲህ ብሎ መለሰለት››
‹‹ተው እንጅ እስቲ ልየው ›› በቃ ራሳችን ማስታወቂያ ሰርተን ቁጭ ! እርሱም ቢሆን የሚፈልገው ይሄንኑ ነው ‹‹ፓ እሱ እኮ አነጋጋሪ ...እሷ እኮ አደገኛ ነቋሪ ምናምን ›› መባል ! እናም በዙሪያው ሰወች ሲተራመሱ ለራሱ የጎደለበትን በራስ መተማመን በጨረባ ተስካር መሙላት ....

ጓዶች ! እስቲ ስድብ እንጥላ ! ከልብ የጠላነውን ነገር ማየት መስማት አንፈልግም አይደል.... እንደዛ! ከልብ መውደድ ቢያቅተን እንዴት ከልብ መጥላት ያቅተናል ! ....አንዳንዱ ሰው ደግሞ ስድብ ያለበት አካባቢ ማነፍነፍ ይወዳል !በቃ ሰወች ከተሰዳደቡ ታዝባችሁ ከሆነ የሃይማኖት የዘር ፖለቲካ ንትርኮችና ስድድቦች ሲነሱ ከሃሳብ የረዘመ ዛዛታውን እየጎተተ አፉን ጠርጎ ለንትርክ መሰለፍ የሚቀናው ሰው አለ ! የዚህ አይነቱ ሰው ለሃይማኖቱ ቀናኢ ከሆነ ሞቅ ሲል ማሚሚቅ ብቻ ሳይሆን ሁልጊዜም ስለእምነቱ ሊፅፍ ሊያስተምር ከፊለገም ሊሰብክ ይገባል ....ተኝቶ ኖሮ ሃይማኖቱ የተነካ ሲመስለው አቧራውን አራግፎ ከዘፍጥረት እስከራእይ ማውራት ነገር ከማሚሚቅ ውጭ አንዳች መንፈሳዊ ፋይዳ አለው ብየ አላምንም !! ምክንያቱም የእምነት መነሻው ንትርክ ሳይሆን ፍቅር ነውና !

የፖለቲካ ጉዳይ ፀሃፊ ተንታኝና አስተያየት ሰጭወችም ቢሆኑ እንደጫጩት ከምንግስት ባለስልጣናት አፍ የወደቀች ቃል እየለቀሙ ከማራገብ የተሸለ ከዝቅተኛው መሃበረሰብ ጀምሮ በትምህርት እስከገፋው ዜጋቸው በሚረዳው ግልፅና ምክንያታዊ ሃሳብ በጉዳዮች ላይ ጥልቅ ወቅታዊና መፍትሄ ላይ ያተኮረ ፅሁፍ ቢለጥፉ መልካም ነው (በዛ መንገድ እየሄዱ እያሳወቁን እያስተማሩን ያሉ ቢኖሩም) ... የአንዱን ባለስልጣን ስም ጠርቶ አህያ ውሻ ማለት ማንም አያቅተውም ... ማንም የማያቅተውን ነገር ለመናገር ለምን ጊዜ እናባክናለን .....አንድ የተረዳሁት ነገር ስድብ የፌስቡክ ማህበረሰብን ትኩረት ይስባል ....ግማሹ ተሳዳቢውን መካሪ ግማሹን ለስድቡ ተመጣጣኝ ስድብ መላሽ ሁኖ እዛው አመድ ለአመድ ሲንፏራፏር ይውላል ! አስቦበት ለመጣ ተሳዳቢ ስድብም ምክርም ምን ይሰራል እንዳላዩ ማለፍ እያለ !

ታዲያ ማንም ሰው የሚፅፈው እንዲነበብለት ሰዎች አስተያየት እንዲሰጡት ይፈልጋል ! እንዳዛ ካልሆነማ ምን ሊሰራ ወደጀመዓው ይመጣል ? እንግዲህ ትልቁ ችግር እየታየ ያለው እኛው የፌስቡክ ታዳሚዎች ላይ ነው

....እባካችሁ እባካችን እነዚህን የስድብ የዘለፋ የማናናቅ እና በዘመኗ ምንም ሳትሰራ እድሜዋ እንዳመለጣት መጥፎ ባልቴት ማይረቡ አሽሙሮችና አሰስ ገሰስ አፍ እላፊወች ለሚለጥፉ ሰዎች ምንም አይነት አስተያየት አንስጥ !! በእርግጠኝነት እነዚህ ሰዎች ‹‹ጭር ሲል አይወዱም ›› ዛሬ በምንቸገረኝ የምናሳርፋት ላይክ የዚህ አይነት ከቆሸሸ መንፈስ የሚወጡ ፅሁፎች ስር የሚሰጡ ማናቸውም አይነት ኮሜንቶች ነገ ፀሃፊወቹን የማይወርዱበት የትእቢት ጣራ ላይ ሰቅለው ለግጭታችን እርስ በእርስ ለመጣላታችንና ላለመከባበራችን መነሻ መሆናቸው እንደማይቀር እናስተውል !

በዛ ላይ ብዙ ነገር መስራት የሚችሉ ልጆችን አሪፍ ስራቸውን ኮሜንትና ላይክ እየነሳን ሲሳደቡ ወደግድግዳቸው መንጋጋታችን ‹‹ስድብ የወለደው እውቅና ›› እንዲጥማቸው በማድረግ እንደተሳደቡና ባለቤት እንደሌለው ውሻ አላፊ አግዳሚ ላይ እንደጮኹ እንዲኖሩ ማበረታታት ይሆንብናል ! ስድብ ላይ እናምፅ .....ማንም ይሁን ምንም ይሁን ሲሳደብ ባለመመለስ ላይክ ባለማድረግ ሌላው ቢቀር ለመምከር ባለመሞከር ስድቡን እዛው ብቻውን እንዲሸከማትና እራሱ ደጋግሞ እንዲያነባት እናድርግ ! ሰው ያመጣልህን ስጦታ ካልተቀበልከው ለራሱ ይዞት እንደሚሄደው ሁሉ የላከልህን ስድብ ቦታ ካልሰጠኸውና ካልተቀበልከው ለራሱ ይዞት ነው የሚሄደው !

እና በስድብ ላይ በማመፅ ምርጥ ፀሃፊወቻችን ምርጥ አሳቢወቻችን ምርጥ ለጥቡብ የተሰጠ ጭንቅላት ያላቸው ጓደኞቻችንን የማያውቁበትን ገፋፍተን ተሳዳቢ ገፋፍተን አሽሙረኞች አናድርጋቸው ! እኔ በስድብ ላይ ካመፅኩ በጣም ቆይቻለሁ ማንም ስድብ ነክ ጉዳይ ከለጠፉ ዞሬ አላየውም ለምን ዙሬ አይዋለሁ .... ለዚህ ኮሜንት እያሰላ ለሚሳደብና ለሚዘልፍ ሰው ምክርም ኮሜንት ነው ግሳፄም ኮሜንት ነው የስድብ ምላሽም ኮሜንት ነው ...ዝምታ እና መረሳት ግን ወደመስመሩ ይመልሰዋል አልያም ሌላ ስድብ እውቀታቸው የሆነ መሰሎቹ ጋር ጅራቱን ሸጉቦ ይሄዳል !! እህ በስድብ ላይ እናምፅ ? ...ይሄን የንትርክና ያለመከባበር አስቀያሚ የስድድብ ግንብ በማስተዋል ጉልበታችን እንናደው ??

ድሮም ሰው አሁንም ሰው !!
(አሌክስ አብርሃም)

ከአንድ ሰዓት በፊት ልክ ከምሽቱ 4፡ 30 አካባቢ ቤቴ ቁጭ ብየ እንደገና የታተመውን የዳኛቸው ወርቁን ‹‹ አደፍርስ ›› አነባለሁ ! ድንገት የሆነ የሚንደፋደፍ ድምፅ ሰማሁ .... መጀመሪያ ድምፁ ከውጭ የመጣ መስሎኝ ነበረ ....ቆይቶ ግን ቤቴ ውስጥ መሆኑን አረጋገጥኩ .... (ቆይ ሰስፔንስ ላድርገው) ...ደፍ ደፍ ደፍፍፍ ,....ጓ ... ከሸሸሸሸሸ ....ድምፁ ከጨለመው ኪችን ውስጥ ነበር የመጣው ቢላ ምናምን ሲንኳኳ በቃ

የሆነ ሰው በኪችኑ መስኮት ዘሎ እንደገባና አንገቴን ቆርጦ የሚጥልበትን ቢላ እየመረጠ እንደሆነ አሰብኩ ....ገዳየ ደደብ ካልሆነ በስተቀር ከሁለት ቢላ አንዱን መምረጥ ይሄን ያህን አቧራ የሚያስነሳ ቤት የሚያተረማምስ ጉዳይ አልነበረም ....

መቸም ያች ትንሷ የሽንኩርት መክተፊያ ቢላ እንኳን የእኔን አንገት ሽንኩርትም ለመክተፍ እንደምታስቸግር ግልፅ ነው ...ጠላቴ የፊለግ ገዝፎ ጎሊያድን ቢያክልም ያችን ቢላ ይዞ ወደሳሎን ከመጣ አልፈራውም ! ‹‹አንገት ለአንገት›› ተናንቄ ነው የምሞተው ....ያንኛው ቢጫ እጀታ ያለው ቢላ ባይሆን እሱ ሳይሻለው አይቀርም ዘለግ ያለ ስለቱም የሰጠ ቢላ ነው ... እስቲ አሁን ያንን የሚያህል ቢላ ለምን ብየ ገዛሁ ? ...ያው ለዚሁ ይሆናላ ! ይሁን ግዴለም ነገ ሽንብራቸውን እየቆረጠሙ ታሪኬን ለሚያወሩ የእድሩ ሰወችም በሽንኩርት መክተፊያ ቢላ ሞተ ከሚሉ ....‹‹ጎራዴ የሚያህል ሳንጃ የሚያስንቅ ቢላ ከያዘ ሰው ጋር በባዶ እጁ ሲፋለም ሞተ ››ቢሉ ለእድሩም ለእኔም ክብር ነው !

ከቻቻቻቻቻክሽ .....የሆነ ነገር ተሸከርክሮ በመውደቅ ተሰበረ የሸክላ ሰሃን መሰለኝ .....ደንባራ ! ይሄ ሰውየ ነብሰ ሊያጠፋ ነው ወይስ እቃ ሊጨርስ የመጣው ? ‹‹ ኧረ የኔ ወንድም ቀስ ብለህ አሽብረኝ ...ምናልባት እግዜር ብሎ ብተርፍ እንኳን እንድጠቀምበት እቃውንም አትፍጀው ›› ልል ከንፈሬ ላይ ደርሶ ተውኩት ‹‹ንቆ መተውን የመሰለ ነገር የለም ›› ማንም ነብሰ ገዳይ ጋር እኖ ከመካፈት በቀረችው ሰዓት ንስሃ ብገባ አይሻልም ? ....በዚህ ቅፅበት ድርርርርር የሚል ድምፅ ሰማሁ ይሄ ድምፅ ስቶቭ ስለኩስ ከስቶቩ የሚወጣ ድምፅ ነው ... እንዴ ...ቆይ ይሄ ወሮ በላ ስንቄን አስቋጥሮ ነው እንዴ ወደጀሃነብ የሚልከኝ .... እና ምን ስቶቭ አለኳኮሰው ወይስ ዘልዝሎ ሊጠብሰኝ ነው !

ሻሻሻሻሻ ሸሸሸሸሸሸ የእቃ ማጠቢያው ውሃ የተከፈተ መሰለኝ ....በቃ ነብሰ ገዳየ ሴት ናት !! ነብሰጋዳይነቷን ረስታው ጓዳ ስራዋ ላይ አተኩራ ሳይሆን አይቀርም .... ድሮም ‹‹አጥፊየ ሴት እነደሆነች ቀልቤ ነግሮኛል ›› መች አጣሁት የዛሬ ሰባት አመት ሴት ስትገለኝ ህልም ሁሉ አይቻለሁ .... እውነቴን እኮ ነው እንዝናና ብላ አንድ ሚሊየን ሜትር ጥልቀት ያለው ገድል ጫፍ ላይ ስንደርስ ገፈተረችኝ
ወ
ር
ጀ

ወ
ር
ጀ
ሳላርፍና ሳልፈጠፈጥ ከህልሜ ነቃሁ ! መውረዱን የዛን ጊዜ ጨርሻለሁ እንግዲህ ዛሬ የመፈጥፈጡ ተራ ይሆናል .... ይሄው መቸ ህልሜ መሬት ጠብ ይልና .... ውሃው ሲንሻሻ እቃ ሲንሳዳሳድ እቃ እያጠበች እንደሆነ ጠረጠርኩ ....እኔኮ ሴቶች ግርርርርም የሚሉኝ ንፅህናቸው !! ....እንኳን ወደውን ሊገሉንም መጥተው ቤቱ ካልፀዳ ለምን ሊገድሉት ያሰቡት ሰው ተገትሮ ዘላለም አይኖርም ትተውት ወደስራ ነው ... ታዲያ እድሚያቸውን ጓዳ በመንሳዳሳድ ሲፈጁት ሊገድሉት የቀረቡት ገዳያቸው ሁኖ ያርፋል !

ገዳየ ሴት መሆኗን ሳውቅ ተፅናናሁ ....ለምን ዮዲት ጉዲት አትሆንም ...አሳዳጊ የበደላት ጀረሬ ካልሆነች በስተቀር ያንን ሁሉ ኪችኑን የሞላ የቆሸሸ እቃ ተራምዳ መጥታ እንኔን አትገድልም ! ሴት ልጅ እቃ ከተራመደችማ ከመገደሏ በፊት በቁሟ ሞተች ! ወግና ባህላችን መግደልን ባይከለክላትም እቃ መራመድን ግን እንደነውር ነው የሚያየው ! ‹‹ ማነሽ አጃክስ ገዝቸ ልምጣ እንዴ ደግሞ ሱቁ ሁሉ ዝግ ነው ›› ልል ፈለኩና አንዳንድ ሴቶች ወንድ ልጅ በጓዳ ስራቸው ጣልቃ ገብቶ ሲናገር እንደማይወዱ ትዝ ሲለኝ ተውኩት ! ለምን አበሳጭቻት እድሚየን እንድታሳጥረው እገፋፋታለሁ ....እረ እንደፈለጋት ትሁን ምናገባኝ !

በሰላም በመከባበርና በፍቅር ብትገድለኝ ይሻላል ... በእነዛ አለንጋ ጣቶቿ (መቸም መልከጥፉ ሴት ነብሰ ገዳይ አትሆንም ጣረ ሞት ራሱ ቆንጆ ሴት ተመስሎ ነው የሚመጣው ይባላል በአፈ ታሪክ) እና ይች ቆንጆ ሴት

ፀጉሬን እያሻሸች የሚያማምሩ እግሮቿ ስር አንበርክካ ....በራሴ ቢለዋ ሽክ ብታድርገኝ ይሻላል..... ከሞቱ አይቀር በቆንጆ ልጅ እጅ ሲጥ ነው ! ምናባቱ !! አገር ሰላም ካልሆነ በዱር በገደል የአሞራ ሲሳይ መሆን የወንድ ልኩ ነው ! ሰላም ከሰፈነ ግን ለማን ብየ ሆስፒታል አልጋ ላይ የማንም ነጭ ለባሽ እያሽካካብኝ ልሙት .....የሚወዲት ደረት ላይ ደገፍ እንዳሉ አልያም ክንዲን ተንተርሰው ...ግጥም ማለት በስንት ጠዓሙ !

እያቃሰታችሁ ድክም ባለ ድምፅ የመጨረሻዋን ትንፋሽ ሰብስባችሁ ውዳችሁን ወደላይ እያያቸኋት (ደግሞ ባለቀ ሰዓት ከታች ወደላይ ሲታዩ ሴቶች በጣም ውብ እንደሚሆኑ ከብዙ ሚጆች ፈገግታ መረዳት ችያለሁ) .....‹‹የኔ ማር አንዴ ሳሚኝ ›› ትሉና በበሽታ አልያም በአደጋ የደረቀ ከንፈራችሁን ታሞጠሙጣላችሁ .... እ.....ሚ ስትላችሁ ከንፈሯ ላይ ግጥም ! መአሰላም !! ችግሩ የእኛ አገር ጎረቤት ነፍሳችሁ እስኪወጣ ከቦ በየት በኩል ያሳስማችኋል ...ሚስታችሁም የመጨረሻችሁ መሆኑን ብታውቅ እንኳን አይናይናችሁን ከማየት ውጭ አትደፍርም ! መቸስ ሊስታምም ብርቱካን አንከርፍፎ የመጣ ጎረቤት ‹ውጣልኝ › አይባል !

አሁን ገዳዮቹ የተባረኩ ሁነው እንጅ ‹‹ምናባቱ ደግሞ ለሱ ቆንጆ ገዳይ መላክ ›› ብለው አንዱን ወጠምሻ የጉልበት ሰራተኛ ቢልኩብኝ ምን ይውጠኝ ነበር ? ....አሸዋና ሲሚንቶ በጠገበ መጅ ባወጣ መዳፉ አንገቴን አንቆ በአረቄ በደፈረሰ አይኑ አፍጥጦብኝ ....በተነፈሰ ቁጥር ከአፍንጫው ቀዳዶች ጀሶ እየቦነነ .... ጥርሱን እንደፋሲካ ቢላ እያፋጨ አንገቴን ጠምዝዞ ሲያበቃ እንደብሎኬት ከፎቅ ቢወረውረኝ .....ሆሆ ....ኧረ እንኳንም ገዳየ ሴት ሆነች .....

ኳኳኳኳ አለ ጓዳው ‹‹የኔ ቆንጆ እንዲህ ጓዳውን ተምነሽነሽበት ባይሆን ተጠንቀቂ እዛ ከስቶቩ ጎን የተላጠ የኤሌክትሪክ ሽቦ አለ የኔ ማር የኔ ነብሰ በላ ›› አልኳት በውስጤ ! ለመጀመሪያ ጊዜ እስከዛሬ ሚስት አለማግባቴ ፀፀተኝ ! ....ባገባ ኖሮ እኔ ሳሎን ተቀምጬ እንዲህ የድስት የሰሃንና ማንኪያ ኦኬስትራ እያዳመጥኩ ቀጥሎ የሚቀርበውን ምግብ አስብ ነበር ....በቃ ሚስት እኮ ጓዳ ውስጥ ስታንኳኳ የሚረብሽ ነበር የሚመስለኝ ለካ የሆነ ሙዚቃ ነው ድምፁ... ጃዝ ነው ...ጋሽ ሙላቱ አስታጥቄ ኪችኔ ውስጥ ጃዝ እየተጫወተ እኮ ነው የሚመስለው !

ፍርርርርርርር ፊውውውውው አለ የሆነ ነገር .....ሙዚቀኛ ዳዊት ፍሬው ጋሽ ሙላቱን ሊያጅብ ፍሉቱን ይዞ በኪችኔ መስኮት ዘሎ ገብቶ ይሆን እንዴ ? ዝም አለ ሁሉም ነገር ..አሁን ፍርሃቴ ብን ብሎ ጠፋና ‹‹ማናባቱ ነው ደፍሮ ቤቴ የገባው ›› ብየ ግልፍ ሊለኝ ሲል መልሶ ድምፁ መጣ ታ ታታታታታ ታ ታታታ ....አሁን የመረረው መጣ ...በመጨረሻ ያበጠው ይፈንዳ ብየ ተስፈነጠርኩና ወደኪችን ሄድኩ ....ለማንኛውም ብየ ከመኝታ ቤቴ የቁም ሳጥኑን ብረት በማውረድ እስኪጣመም አጥብቄ ጨብጬ በመያዝ ወደበሩ ተጠጋሁ .....በሩን ግን መክፈት በየትኛው ልቤ ....እኔኮ ራሴን ጀግና አድርጌ ነበር የማየው ለካ እንዲህ ነኝ ....

<<ከሁሉም ጭቅጭቅ ለምን ፊልም ላይ እንደማየው በሩን በእግሬ ገንጥየ አልገባም >>አልኩና ወደኋላየ አንድ ሶስት ርምጃ ተራመድኩ ...ወደፊት ልንደረደር ስል ‹‹አከራየ ›› ትዝ አሉኝ ....በራቸው ከሚገነጠል ኢትዮጲያ ብትገነጣጠል የሚመርጡ ንብረታቸው ነፍሳቸው የሆነ ነዝናዛ ሽማግሌ ናቸው ! በነገራችን ላይ ይሄ ሰውየ ዚያድ ባሬን ሊዋጉ ጓደኞቻቸው ሲዘምቱ እሳቸው ሃረር ላይ ቁስለኛ ማመላለሻ በቅሎ ያከራዩ ነበር ...አሁንም ይሄው ኦሮ ላቆሰለው ኗሪ ቤት ያከራያሉ ! አሁን እያርገውና ብሞት ከአስራ አምስት ቀን በኋላ ሬሳየ ቢገኝ አሁን ነው የሞተው ማለታቸው አይቀርም እስከዛሬ ኦሯል ብለው ኪራይ ሊቀበሉ !! እሳቸው ጋር ማን ይነዛነዛል ባይሆን ቀስ አድርጌ በሩን ገፋ ባደርገውና ጥጌን ይዤ ገዳየ ብቅ እስክትል መጠበቅ እንደሚሻል አሰብኩ ...

በቃ ብቅ ስትል አናቷን !! ...መቸስ ሄልሜት አድርጋ ልትገድለኝ አትመጣ ! ይሄ ቆንጆ የጦር ስልት ነው ! ስትራቴጅካዊ ቦታ ይዤ በሩን ገፋ አደረኩት ....ገና በደንብ ሳይከፈት ገርበብ ከማለቱ ከውስጥ እንደጥይት የሆነ ነገር ተወንጭፎ ወደሳሎን ሲገባ አየሁ .... በድንጋጤ የያዝኩት ብረት ከእጀ ወደቀ ! ከዛማ ምኑ ቅጡ ....ሳሎኑ ተተረማመሰ ...ይሄን ሁሉ ስታስጨንቀኝ የነበረችው .....የሌሊት ወፍ ነበረች !! በመስኮቱ አናት ላይ ባለው የአየር ማስገቢያ ቀዳዳ ገብታ .... መውጫ በማጣቷ ነው ይሄ ሁሉ ረብሻ ! የተረገመች !!

ሳሎን ውስጥ አንዴ ከግድግዳው አንዴ ከእቃው እየተጋጨች ቆይታ በራሷ ጊዜ ምንጣፉ ላይ ዝልፍልፍ ብላ ወደቀች ….. ክንፏን ተመርኩዛ ለመነሳት ሞከረች …. አልተሳካላትም … ጭንቅል ጭንቅሏን ብየ ልገድላት ጠጋ ብየ አየኋት…..(ቀን የጣለውን መቸም በዚህ አለም ላይ እንደሌሊት ወፍ አስቀያሚ ፍጥረት ካለ ይገርመኛል ….እንዴት ነው ምታስጠላው ….በዛ ላይ ፊቷ የሽማግሌ ሰው ፊት ይመስላል ትንንሽ ጡቶች አሏት የዶሮ ጥፍር የሚመስሉት እግሮቿ በስስ የስጋ ቲሹ የተያያዙ ዣንጥላ የሚመሳስሉ ናቸው ….. አይኗ ደግሞ አተላለቁ ክፍት ክድን ይላል ! እንኳን ለማየት ለመግደልም ታስጠላለች ! ቢሆንም በያዝኩት ብረት አንዴ ነርቻት አፋፍሽ ልጥላት አሰብኩ !

ታዲያ በመሃል ድንገት አንድ የተረገመ ሃሳብ በለጭ አለብኝ …..ይሄ ሩቅ ምስራቅ አካባቢ እንህንድ እነቻይና ምናምን የሚከተሉት እምነት አለ አይደል እሱ ትዝ አለኝ ….ነብስ ያው ነብስ ነው የሰውም የእንስሳትም ነፍስ ያው አንድ ነው ከላይ ስጋው ብቻ ነው የሚለያየው ….እና ዛሬ ሰው የሆነ በሞተ በሶስት ቀኑ የበግ ዝጋ ለብሶ በግ ሁኖ መልሶ ይወለዳል …በቃ ምናልባት ለፋሲካ የምታርደው ባለፈው አመት የሞተው ያ ደግ አጎትህ ሊሆን ይችላል እንደገና በግ ሁኖ ተፈጥሮ …. አሁን ለዘመን መለወጫ የገዘሃት ዶሮ ለምሳሌ እውቋ ድምፃዊት ዊትኒ ሆስተን ዶሮ ሁና ኢትዮጲያ ውስጥ ተፈጥራ ሊሆን ይችላል …ማን ያውቃል ! (የኛ ነገር ስንረጋጋ እኮ ነው በአንድየ የምናምነው …ስንፈራ ስንደሰት የማናምንበት ጉድ የለም !)

እና የዚህ እምነት አስተምሮት ልክ ቢሆን …ይች የሌሊት ወፍ ባለፈው አመት በመኪና አደጋ የሞተችው የጓደኛየ የኤሊያስ ፍቅረኛ ብትሆንስ እንደውም ነብሷን ይማርና በቁሟም የሌሊት ወፍ ይመስል በየጭፈራ ቤቱ ስትዞር ነበር የምታድረው… ከሌሊቶች በአንዱ አንድ የሰከረ ጓደኛዋ የሚነዳውን መኪና መንገድ ስቶ ገደል አስገብቶ ነው የጨረሳቸው ….. እና ይች የሌሊት ወፍ እሷ ልትሆን አትችልም …..ማን ውቃል … ወይም እኒያ ደግ ጎረቤታችን እማማ ዙሪያሽ ‹‹አቡችየ ›› እያሉ የከረሜላ መግዣ የሚሰጡኝ እሳቸው ቢሆኑስ …እሳቸውም ሰካራም ባላቸውን ሲጠብቁ ሌሊቱን ውጭ ለውጭ ነበር የሚሄዱት ….

ጨነቀኝ …ቀስ አድርጌ በወረቀት አፋፍሽ ከነሂቷ በመስኮት ወረወርከዋት …..እናም እጀን ተጣጥቤ ወደምኝታየ ሄድኩ …ሃሳቡ ግን እንዴት ከአይምሮየ ይውጣ …. እዩትላችሁ አንዱ አዳኝ ቀበሮዋን እያሳደደ ተኩሶ ገደላት እንበል እሱን ደግሞ ነበር ደርሶ ገደለው ….ከዛ እንደገና ሲፈጠሩ ቀበሮው ሰው አዳኙ ደግሞ ቀበሮ ሁነው ተፈጠሩ ….እንግዲህ አዳኝ ታዳኝ ድራማው ምን ሊመስል እንደሚችል አስቡታ …….

የሩቁ ይቅር እዚህ ፌስቡክ ላይ ያለነው ጓደኞሞች ድሮ በዛንኛው ስጋችን ምን ነበርን ? …ከምንሰጠው ኮሜንት ከምንፅፈው እና ከምንለጥፈው ፎቶ በመነሳት መገመት ይቻል ይሆን እንዴ? … ለምሳሌ አንዳንዱ ድሮ በሬ ሁኖ ከሞተ በኋላ ሰው የሆነ እስኪመስለኝ ኮሜንቱም ሃሳቡም ተዋጊ ነገር ነው …. ሌላኛው ከአንድ ሃሳብ ወደሌላ ሲዘል ሃሳቡ ሁሉ ተንኮል ሲሆን ሄ ድሮ ጦጣ ነበር ያስብላል …. የዘር የሃይማኖት እንከን እየመዘዘ ሲያፋጅ የምናየው በቀደምት ፍጥረቱ እባብ እንዳልነበረ ምን ማረጋገጫ አለን …

እውነት ግን ጠንከር ያለ ምርምር ቢሰራ ድሮ ምን እንደነበርን ማረጋገጥ ሳይቻል አይቀርም …. ከመሬት ተነስቶ ሌሎችን መራገጥና ማናፋት የሚያበዛ ሰው ሲገጥመን በዛንኛው ኑሮው አህያ የነበረ ይሆን ብየ መጠርጠሬም አይቀርም ….. እኛ በሰው ሂሳብ ልናሰምን ስንጣጣር አስቡት እስቲ …. እንደዛ እያሰብኩ ደግሞ ደጋግ ልበ ንፁህ ወዳጆቸን ሳስብ …. እኒህ ልጆች ድሮ መልአክ የነበሩ ሳይሆኑ አይቀርም እላለሁ !! ትዝ ሲለኝ መልዓክት አይሞቱም ለካ ….በቃ እነዚህ ምርጥ ጓደኞቸ ድሮም ሰው አሁንም ሰው ናቸው …!!

ጠቅሞ ላይጠቅም
(አሌክስ አብርሃም)

ጓደኛየ አለምነህ ‹‹ትልቅ ሰው›› ነገር ነው መካሪ ምናምን ! የዘጠነኛ ክፍል ተማሪወች እንደነበርን አለምነህ ጋር ተዋወቅን ....እንዴት እንደተዋወቅን ረስቸዋለሁ እንኳን እንዴት እንደተዋወቅን እንዴት ጓደኛ ለመሆን እንደበቃንም ትዝ አይለኝም ብቻ እስካሁን ጓደኛ ነን ! ባህሪው በጣም ደስ ይላል .... በተለይ ለኔ እርሱ ጋር ስቀመጥ ባህላዊ ቲያትር የምመለከት ነው የሚመስለኝ (ባህላዊ ቲያትር የሚባል አለ እንዴ? . . . እኔኛ) እናቴ ታዲያ እንዲህ አለችኝ ‹‹ አሁን ገና ኑብስ ያለው ቁም ነገረኛ ጓደኛ ጋር ገጠምክ››

እንዴት መሰላችሁ በቃ አለምነህ ይመክራል የመምከር ፀጋ አለው ‹‹ አብርሽ መቸስ ሰው ከፈጣሪ የተሰጠው አንዱና ትልቁ ፀጋ አይኑን በአይኑ ማየት ነው ...እንግዲህ ልጆች አይደለንም አግብተህ ወልደህ ማየት ምኞቱ ነው ...›› ይላል
‹‹ እሽ ›› እለዋለሁ
‹‹ አብርሽ አትቀልድ ወዳጄ ‹‹ ቃል የእምነት እዳ ነው ›› እዳለ ባለቅኔው ዝም ብለህ እሽ አትበል ...እሽ እኮ ት.....ልቅ ቃል ነው ...ቃል ኪዳን ነው ››
‹‹ታዲያ ምን ልበል ››
‹‹እሱማ ምን ትላለህ ያልከውን አድርግ እንጅ ››
‹‹ እሽ ›› እለዋለሁ ! እንሳሳቃለን

‹‹ እኔ የምልህ አብርሽ እንደው የሚቀርቡህ ሴቶች ሁሉ በፀባይ ብትል በመልክ ብትል ግሩም ናቸው ...(እስኪ አሁን ግሩም የሚለውን ቃል ከየት አመጣው ?ይገርመኛል) ....አንተም ብትሆን አንድ ያልተመቸህ ነገር ቢኖር እንጅ ሳውቅህ ከዛ ከዚህ የምትል ልጅ አይደልህም ...ረጋ ያልክ ከይሲ ነህ ›› ሁለታችንም እንስቃለን ! አለምነህ እየሰደበኝ እንኳን ያስቀኛል ....ረጋ ያለ ተሳዳቢ ነው

‹‹አያስቅም አብርሽ ...ጥርስህን ያርግፉውና አያስቅም ...እስቲ አሁን ሰሎሜ ጋር በምን ተለያያችሁ ምን ጎደላት ንገረኝ አብርሽ ንገረኝ ›› ሰሎሜ ጓደኛየ ነበረች
‹‹ ሰሎሜ ት....ንሽ ዝምታ ታበዛለች ››
‹‹ዝምታ እኮ ብልህነት ነው ... ‹የእግዚአብሔር ፈቃድ ይሁን ዝም አልን ›ይላል መፅሃፉ ብልህ ከዝምታ ውስጥ ብዙ ቁም ነገር ይማራል ››

‹‹ ታዲያ የሶሎሜ ዝምታ በዛሃ ! አያስተምር አያዝናና በቃ ዝም!! .... በስልክ ሳይቀር ዝም ትላለች ራሷ

ደውላልኝ ሁሉ ዝም ትላለች ›› እውነቴን ነበር ሰሎሜ አስደንጋጭ ውበት የሰጣት ልጅ ነበረች ምን ያደርጋል ....ሶል ስላት አየት አድርጋኝ ዝም ሶሊ ስላት ፈገግ ብላ ዝም እንዴት ነበር ውሎ ስላት ‹‹ምንም አይል›› ብላ ዝም በቃ ዝም ! እጀን በለስላሳ እጆቿ እየነካካች ብቻ ዝም ! ሰሎሜ ሄለን ኬለርን ትመስለኝ ጀመረ ! በዳሰሳ ብቻ ነው ወጓ !በእርግጥ ሰትዳስሰኝ በእጇ ውስጠ አልፎ ልቤን የሚሞቀው ፍቅር ብዙ የሚነግረኝ ነገር አለ ! ቢሆንም በዛ ባዶ ቃል ፍቅር ባይሆም ፍቅርም የቃል ቅመም ጣል ካልተደረገበት ደንዙዝ ይሆናል ! ቀስ እያልኩ መራቅ ጀመርኩ በመጨረሻ በቃ ሶል እንለያይ ስላት እጀን በእጆቿ ጠበቅ አድርጋ ይዛ ……..ዝም !

‹‹ እኮ ፍቅር ማለት እኮ ይሄ ነው ዝምታዋን ካልሰማህ ምኑን አፈቀርካት ...ደግሞ ስትጋቡ ይከፍትላት ይሆናል ››
‹‹ ኧረ ባክህ ተወኝ አፏ የተሰራው ከቀለበት ነው እንዴ ሳገባት የምታወራው ? ››

‹‹ እሽ ናርዶስ ምን ጎደላት ...››

‹‹ናርዶስ እንኳን አሪፍ ልጅ ነበረች ግን ወሬዋ ሁሉ ,ካራት, ሆነ ....እኔ ደግሞ ካራት ሰለቸኝ ›› እውነቴን ነው ናርዶስ ስቃ የምታስቅ ከሳቅ የተሰራች ልጅ ነች ! የምትስቅበት ነገር ብታጣ ‹‹ እንዲህ ቡጥጥ ብለን ሳንስቅ መቀመጣችን እያስቅም ›› ብላ የማይቋረጥ ቅጭልጭል ሳቋን ትለቀዋለች ! መንገድ ላይ እኔና ናርዶስን ያየን ሰው ፈገግ ማለቱ አይቀርም በቃ የሆነ ሳቋ የሚጋባ አይነት ልጅ ናት ...አባቷ ወርቅ ቤት አላቸው ወርቅ ነጋዴ ስለሆኑ ነው መሰል ማንኛውንም ሰው በጥርጣሬ ነው የሚያዩት የሆኑ የደህንነት ካሜራ ነገር ናቸው !

ናርዶስ ለመጀመሪያ ጊዜ ስታስተዋውቀን ‹‹ እንደምነህ ›› አሉኝ ከእግር እስከራሴ ‹ስካን › አድርገውኝ ሲያበቁ

‹‹ደህና ››

‹‹ ምነው ደህና ብቻ ...እግዚአብሔር ይመስገን ማንን ገደለ ...ያው እንግዲህ ልጇ ነህ ያየሁትን ጥፋት መምከር ነው እኔ መደባበቅ አልወድም ›› አሉኝ ሳቁ መጣብኝ ! ናርዶስ ትስቃለች ! እንግዲህ ቶሎ ተጋቡና የልጅ ልጅ አሳዩና (ኧረ ጎራው ናርዶስ ብትወልድ ሰው ሳይሆን የዘጠኝ ወር ሳቅ የምትወልድ ነው የሚመስለኝ) አጉል ነገር ላይ ሁሉ ትስቃለችኮ ከምር እየሳቁ ((እንትን)) አይገርምም ? (እንደው ግመና አይወራም እንጅ)

እንግዲህ ናርዶስ ከሳቋ ቀጥሎ ወሬዋ ሁሉ ወርቅ ብር እና ካራት ነው ‹‹ አብርሽ ሃያ አንድ ካራት ወርቅ ሃብል ግዛ በናትህ እዚህ አንገትህ ላይ በጣም ነው የሚያምረው ›› ትለኛለች ስለሃብል ከአስራ ስምንት ካራት ጀምራ እስከምናምን ካራት ጥግብ እስክትል ካወራች በኋላ ስለቀለበት ትቀጥላለች ...‹‹ ወንድ ልጅም ጎላ ያለ ቀለበት ሲያደርግ ነው የሚያምረው በዛ ላይ ራስህንም ለመጠበቅ ጥሩ ነው ››

‹‹ በወርቅ እንዴት ነው ራስ የሚጠበቀው ..ከሰላቢ ነው ...ከቡዳ ›› እላታለሁ

‹‹ ኧ ከሰው ....ደህና ቀለበት ማለት የብረት ቦክስ በለው ፀብ ቢፈጠር እንኳን ለቦክስ ...ሂሂሂሂሂሂ››

‹‹እንዴ ለምን ፀብ ይፈጠራል ››

‹‹ወንድ አይደለህ እንዴ አንዳንዴ ባይፈጠር እንኳን ራስህ መፍጠር አለብሃ ››

‹‹ ምን ቦክስ ነው የምፈጥረው ›› ተገርሜ እጠይቃታለሁ

‹‹አዋ ››

‹‹ እንዴዴዴዴዴ አብደሻል እስኪ አስቢው ነገር አፈላልጌ መንገደኛ ጋር ስጣላ ››

‹‹ ማን መንገደኛ ጋር አለህ ››

‹‹እና ….››

‹‹ አንዳንዴ እኔም ጋ ቢሆን …የፍቅር መግለጫ እኮ ነው ሂሂሂሂሂ›› በቃ ናርዶስ ከማጌጫ እስከመቀጣቀጫ ምርጫዋ ሃያ አንድ ሃያ አራት ካራት ወርቅ ነው …በኋላ እንደታዝኩት የእውነትም አንድመታት ትፈልግ ነበር ‹‹እንደወንዶቹ አንዳንዴ በጥፊ ብትለኝ ..›› ያለችኝ ቀን እንደወንዶቹ በሂድኩበት ቀረሁ ! የካራቱ ሲገርመኝ ጭራሽ በፍቅር ስም ካራቱ ! ስንት አመል አለ …ታዲያ ከረዥም ጊዜ በኋላ ናርዶስን አግኝቻት ስትስቅ ደነገጥኩ

.. ፊት ለፊት ወርቅ ጥርስ ገጭ ብሎ ተተክሏል (በዚህ ዘመን ወርቅ ጥርስ) አንድ ግልፍተኛ ጓደኛ ይዛ በቦክስ ጥርሷን አውልቆት ነበር ‹‹ ወንድ ልጅ እንዴት ሴት ላይ እጁን ያነሳል በማሪያም ›› አለችኝ ቀጠል አድርጋም እንዲህ አለችኝ ‹‹ ነገሩ ነው እንጅ ያው በህግ አፍንጫውን ተይዞ ሃያአራት ካራት የወርቅ ጥርስ አስተከለልኝ ሂሂሂሂሂ ››

በነገራችን ላይ አለምነህ የማወራውን ሁሉ እንደማያምነኝ አውቃለሁ ከትዳር ለመሸሽ የፈጠርኩት ነው የሚመስለው ….

‹‹አሽ ሌላው ይቅር ሊዲያን ለምን ተጣላሃት …ሊዲያ ምን ይጎድላታል እንደዛ አብደህላት ከንፈህላት ስትደውልልህ ጫማህን ሁሉ ረስተህ የምትሮጥላት ልጅ ምናይነት ሰይጣን መሃላችሁ ገባ አብርሽ ››

‹‹ ኧረ ሰይጣን አይደለም ››
‹‹እና ምንድን ነው …ባለፈው አግኝቻት ‹ምንም ክፉ ደግ ሳንነጋገር ራቀኝ › አለችኝ ‹‹ቢያንስ ስልክ <ተጠቅሞ> ምክንያቱን ሊነግረኝ ይገባል ›› አለችኝ ! ተገቢ ነው ? ቢያንስ ቁጭ ብሎ በአኩበሮት በዚህ በዚህ ምክንያት በቃሽኝ አይባልም ? ››

‹‹ እንዴ እኔ የሷ መጠቀም እና ጥቅም ሰለቸኛ ›› እውነቴን ነው …ሊዲያ ጥሩ ልጅ ናት ግን ስታወራ ቃል ስለምትመርጥ ወሬዋ ሁሉ አርቲፊሻል የሆንብኛል …በእርግጥ እርሷ ዘመናዊነት አድርጋ ነው የምታየው እኔ ግን ….. ለምሳሌ ቢሮዋ እሄዳለሁ አይደል ? ተቀመጥ ለማለት ‹‹ ወንበር ውሰድ ›› ትለኛለች ያችን የፈረደባት ((ቱክ ኤ ቸር)) ቀጥታ ወስዳ መሆኑ ነው ! ምነው ሽዋ ! ‹‹አረፍ በል›› ‹‹ተቀመጥ ›› ወላ ተወዘፍ ብባል የሻለኛል

…..ሌላው ያስመረረኝ ቃሏ ‹‹አመሰግናሁ›› በአንድ ደይቃ አስር ጊዜ ‹‹አመሰግናለሁ›› ልትል ትችላለች ምስጋናው አይደለም ችግሩ …የተጠና አርቲፊሻል እንዲሁ አፍ ላይ የከረመ ልማድ መሆኑ ነው ነፍሷ እንደማያመሰግን ያስታውቃል ! ማመስገን ጥሩ ነው ሲባል እኮ ምስጋናን እንደሁለት ነጥብ በየቃሉ መሃል መሰንቀር አይደለም ኤጭጭ ለዛ ያጣ ምስጋና እንዴት ይቸካል !

በተለይ ደግሞ ያስመረረኝ ይሄ ‹መጠቀም › የሚል ቃሏ ‹‹ ካፍቴሪያ ስንጠቀም ፣ሶፍት መጠቀም ፣ስልክህን ልጠቀምበት፣ መፀዳጃ ቤት ልጠቀም …›› ወይም ስልክ ደውየላት ካላነሳች መልሳ ደውላ ‹‹ይቅርታ ሃኒ መፀዳጃ ቤት እየተጠቀምኩ ነበር በዛ ላይ ስልኬ ካርድ ጨርሶ በማሚ ስልክ ነው ተጠቅሜ የደወልኩልህ ›› ትለኛለች ደግሞ ሌላ ቀን ‹‹አብርሽየ ጫት እና መጠጥ አለመጠቀምህ እንዴት እንደሚያስደስተኝ ›› በእርሷ አነጋገር ብስጭቴ ከቀጠለ ወደፊት ሄሮይን ሳይቀር ልጠቀም እችላለሁ ብየ ፈራሁ !

‹‹ሃኒ ከንፈርህ ደረቀ ለምን ቻፕስቲክ አትጠቀምም … ኮምፒውተር ብዙ ሰአት ስለምትጠቀም መነፅር ለአይንህ ብትጠቀም ….. ›› ….ታዲያ እንዴት ነው ይችን ልጅ ለትዳር ‹መጠቀም› የሚቻለው !

መጀመሪያውንም ጠቅሞ ላይጠቅም ቃል ከምታጠረቃቅም ልጅ ጋር ፍቅር መጠቀሜ ተገቢ አልነበረም ! ከዚህ ሁሉ መጠቀም በኋላ የመረረው ጉዳይ ላይ ‹‹ኮንዶም መጠቀም ›› እንዳለብን ስነግራት ደብሯት ነበር

...‹‹አታምነኝም ›› አለችኝ ! ለእኔ የመጨረሻው ስልጣኔ ራስን መጠበቅ ነው ቃል እያጠረቃቀሙ ሂወትን መበተን የዘመነው ስልጣኔ የማይጠቅም መራቀቅ ነው ! ‹‹ኮንዶምን መጠቀም ....አርፎ ከመቀመጥ የበለጠ ብልህነት አይደለም ››

((((ቆይማ እዚጋ የባለጌ ጥያቄ ልጠይቃችሁ (የባለጌ ነው ብያለሁ የማይመቸው ይዝለለው) እ.....(ሂሂሂ አፈርኩ) ምን መሰላችሁ እንትን ....ማለት ሴቶች ውድድ የምታደርጉት ባላችሁ ጋር ወይም በቃ ‹ሃኒያችሁ› ጋር ((እንትን)) ማድረግ ቢያምራችሁ በቃ በጣም ቢያምራችሁ ማለቴ እጅግ በጣም ቢያምራችሁ (ክጃሎት አናታችሁ ላይ ቢወጣ ሂሂ) እና በቃል ‹እናድርግ› ብላችሁ ለመጠየቅ እንዴት ነው የምትገልፁት .....ይገባኛል ሳትናገሩት በፊት አይናችሁ ሲስለመለም ገና ድሮ ‹ሃኒያችሁ › ልብሱን ሊያወልቅ ይችላል ግን በቃ ቃል አውጥታችሁ ብትናገሩት ብለን እናስብ ...የእኔ ጓኛ ሊዲያ ልትል የምትችለውን ስገምት እንዲህ ይመስለኛል ‹‹ሃኒ ወሲብ እንጠቀም ››)))

ጓደኛየ አለምነህ ታዲያ ይሄን ሁሉ ብሶቴን ያው እንደወትሮው ሳያምነኝ ሲሰማኝ ቆየ !ያው ከትዳር ለመሸሽ የምፈጥረው ሰበብ ነው የሚመስለው ! እየሳቀ አስተናጋጇን ጠራና ‹‹ እህቴ እስቲ ‹የተጠቀምንበትን› ሂሳብ አምጭልን›› አላት
አስተናጋጇ መጀመሪያ የታዘዘችን ልጅ ስላለበነረች እንዲህ ስትል ጠየቀችን

‹‹ይቅርታ ምንድን ነው የተጠቀማችሁት ››
‹‹ እኔ የተጠቀምኩት ሻይ ነው ....›› ብሎ የእኔን ሊናገር ሲል ፈጠን ብየ እንዲህ አልኩ
‹‹ እኔ ሁለት ቡና ጠጥቻለሁ !!›› ‹‹ጠጥቻለሁ›› ቃሉ ራሱ እንዴት ደስ ይላል ....

‹‹በል አብርሽ ያለችንን ጊዜ ተጠቅመን እንገናኝ አንጠፋፋ ››
‹‹ እሽ ››
ተሳሰቀን ተለያየን ....እኔም እሽ አበዛሁ መሰል !A

የአገር ክህደት
(አሌክስ አብርሃም)

የአስረኛ ክፍል ተማሪ እስከምሆን ድረስ ብዙ ሰው ወንድምና እህቶቸን ጨምሮ ‹‹የአይምሮ እድገት ውሱንነት ›› ያለብኝ ይመስላቸው ነበር ! እነሱ እንኳን ቃል በቃል የሚሉኝ ‹‹ ዘገምተኛ ›› ነበር !እናቴ ግን ጎረቤትም ይሁን ቤተሰብ ይሄ ቃል ከአፉ ከወጣ ልትገ,ለው ነው የምትደርሰው ...አራስ ነብር ትሆናለች ! እንደውም አንድ ቀን ትንሽ እህቴን አሚት ሊጠይቁ ብርቱካን ይዘው ወደቤታችን የመጡ እንግዶች ‹‹ ውይ ይሄ ነው እንዴ ዘገምተኛው ልጅሽ›› ብለዋት ብርቱካናቸውን አሳቅፋ ከቤት አባራቸዋለች ! እዚህ ድረስ ናት የኔ እናት !

ታዲያ ሁልጊዜ ሰወች ፊት እንደዛ ነብር ትሁን እንጅ ሰወቹ ከሄዱ በኋላ ራሴን እያሻሸች ስቅስቅ ብላ ታለቅስ ነበር !

በእርግጥ እኔም ነገሩ ሲደጋገም ችግር ያለብኝ መስሎኝ ራሴን ተጠራጥሬው ነበር ....በዛ ላይ አንድ ቦታ ከተቀመጥኩ አልንቀሳቀስም ....አንዳንድ ቀንማ ወንበሩ ከተመቸኝ ጧት ቁጭ ያልኩ አስራአንድ ሰአት አካባቢ ነበር የምነሳው ! ይሄ ባህሪየ የገረማቸው ጎረቤታችን አባባ አስፋው አንድ ቀን ‹‹ይሄ ልጅ ባንዲራ ሲሰቀል ቁጭ ያለ ባንዲራ ሲወርድ ነው እንዴ የሚነሳው ›› ብለው ስለጠየቁ እናቴ ክፉኛ ተቀይማቸዋለች !

ቤተሰቦቸ ባህሪየን ጠንቅቀው ስለሚያውቁ አንድኛቸው ምሳየን እዛው ያመጡልኛል ! የሚገርመው ደግሞ ያን ሁሉ ሰአት ስቀመጥ ምንም አለመስራቴ ነው .... አላነብም አልንቀሳቀስም በቃ ቁጭ ! አንድ ቃል እንኳን አልናገርም ! ቁልጭ ቁልጭ እያልኩ ቁጭ !በሂወቴ የምወደው ነገር ቢኖር መቀመጥ ! ለዚህ መቀመጤ ‹‹መጣድ ›› ብለው ስም አወጡለት ...‹‹አቡቹ ሳይጣድበት በፊት ሶፋውን አዘጋጁት›› ይባባላሉ እህቶቸ !

ከዚህ ባህሪየ የተነሳ አንዳንዴ መኖሬን እየረሱ አጠገቤ ሚስጥር የሚያወሩበትም ጊዜ ነበር ...እህቴ እራሷ ከጋሽ አሰፋ ልጅ ፍቅር እንደያዛት አጠገቤ ቁማ ለአነዲት ጓደኛዋ በስልክ ስታወራ ዝንብ እንኳን አጠገቧ የቆመ አልመሰላትም

‹‹ ወይኔ ሳሪየ ካላየሁት እኮ በቃ ስሰቃይ ነው የማድረው ... አሁንማ በቃ ከሱ ሌላ ምንም ማሰብ አልቻልኩም ብርርርርር ብየ እቤቱ ብሄድ ደስታየ ....ምግብ በአፌ ከዞረ ሁለት ቀኔ ››
‹‹ ምግብማ ብይ የኔ ቆንጆ በባዶ ሆድሽ ምን በወጣሽ ›› ትላታለች ጓደኛዋ
‹‹ ምኑን በላሁት ›› ትመልሳለች እህቴ እዝን ባለ ድምፅ

እህቴ የእኔን መኖር ትርሳ እንጅ እኔ በሁለት ምክንያት በጣም ገርሞኝ ነበር ...! ዛሬ እቤታችን በግ ታርዶ ስለነበር ሁለት ሁነው ዱለቱን ሲያጣድፉት በአይኔ በብረቱ አይቸ እንዴት ነው ‹‹ ምግብ በአፌ ከዞረ ሁለት ቀኑ ›› የምትለው ? ወይስ እውነትም አይምሮየ ችግር አለበት ?...ምናልባት ከሁለት ቀን በፊት የሆነውን ነገር ቅድም የሆነ አስመስሎ አሳስቦኝ ይሆን ?....አይ ይሄው ዱለት የበላችበት እጇ ገና ሳትጣጠበው እንደተንከረፈፈ ነው በስልክ የምታወራው !

ሁለተኛው እና ዋናው ገራሚ ጉዳይ .....አሁን የአቶ አሰፋ ልጅ ምኑ ይፈቀራል በእግዚአብሔር ? ዱለት ፊት !በዛ ላይ ለለፈለፈ የማይጠግብ ....ከእናቱ ማህፀን ሲወጣ ለለቅሶ የከፈተው አፉ እስከዛሬ አልተዘጋም ! ታዲያ ይሄንን ልጅ ያፈቀረች እህቴ እንዴት ነው እኔን ‹‹ዘገምተኛ›› የማትለኝ? ...የዚች አገር ትልቁ በሽታ እኮ ካላግባብ የፈጠነውን ጋር እያወዳደሩ በአግባቡ የሚራመደውን ‹‹ቀርፋፋ ›› አድርጎ ማሰብ ላይ ነው !

ፖለቲካውም እንደዛ ነው ...ፍቅሩም እንደዛ ነው ... ደርግ በወታደራዊ እርምጃ ሩጫውን ሲያስነካው ህዝቡ ሃይለስላሴን ‹‹ዘገምተኛ›› አላቸው ... ያው ሯጩ ዞሮ ሲመለስ ፍጥነቱን መቆጣጠር አቅቶት አጨብጫቢወቹ ላይ ወጥቶእየጨፈለቀ ፈጃቸው .... እንደጥይት የሚፈጥነው ኢህዴግ ፈትለክ ሲል ደርግን ‹‹ ከርፋፋ ›› ያሉትም አያሌ ናቸው ከዛ ....ምን ልል ነበር ?? አ...ዎ ! ሁሉም የራሱን ርምጃ አይለካምና ባለፈው እርምጃ የአሁን ሩጫውን ያሞካሻል.... ሩጦም ተንቀርፍፎም ሰው ስንዝር ይጨምር ይመስል !

ይህ ‹ዘገምተኛነቴ› እናቴን ሲያስጨንቃት ኖረ ። አንድ ያልገባኝ ነገር ሰወች እራሳቸው እያዘገሙ ሌላው የፈጠነ ከመሰላቸውም ራሳቸውን ዘገምተኛ አድርገው ከማሰብ ይልቅ ሌለውን ‹ሰላቢ› ማለት ይቀናቸዋል .... እንዴት ማለት ጥሩ ...ትምህርት ቤት የክፍል ስራ ሲሰጠን አንደኛ የምጨርሰው እኔ ነኝ ! ፈተናም እንደዛው ! እና ልጆቹ ‹ሰላቢ› ብለው ስም አወጡልኝ ...እንግዲህ ትምህርት ቤት ‹ሰላቢ› እቤቴ ደግሞ‹ ዘገምተኛ› እንደሆንኩ አስረኛ ክፍል ደረስኩ ! የሰውን ስም ልጠፋ እህ ብለን ካዳመጥነው ህዝቡ ራሱ ዘገምተኛ ይሆንብናል ! አንድ ቀን ታዲያ እናቴ እንዲህ ስትል መከረችኝ

‹‹ አቡችየ እንደው ቁጭ ብለህ አይንህ ከርተት ከርተት ከሚል መፅሃፍ ከጓደኞችህ ተውሰህ አንብበበት እስቲ …ወይ የአባትህ መጣፍ ቅዱስ አለ እሱን አንብበበት ማን ያውቃል ነቃ ያደርግህ እንደሆነ ››

ምንም አልመለስኩላትም ዝም ! ማንበብ አልወድም ! ሰወች ሲያነቡ ዘገምተኛ ይመስሉኛል ! ዝም ብየ ሳስበው መፅሃፍ ግርምምምምምምም ነው የሚለኝ …መጀመሪያ ፊደል አለ … ፊደሎቹ ራሳቸው አንዳንዶቹ ጅራት ሌላዎቹ ቀንድ ቅጥያ ጉትቻ አላቸው (አቤት የሰው ለጅ ስራ ፈትነት) …..ከዚህ ሁሉ ቅጥልጥል በኃላ ደግሞ ፊደሎቹ ተደማምረው ቃል ይሆናሉ …ቃላቱ ሃረግ…. ሃረጋቱ አረፍተ ነገር ….አረፍተ ነገሩ አንቀፅ….. አናቅፁ ታሪክ….. ታሪኩ ምእራፍ …..ምእራፉ መፅሃፍ … ሲጀመር ፀሃፊው ምን ልሁን ብሎ እንደሚፅፍ ይገርመኛል …መፃፍ ከስጋ ይልቅ የነፍስ ጉዳይ ይመስለኛል…. የነፍስን ጉዳይ በስጋ ለመግለጥ የሚደረግ ድካም !

ፅሁፍ ማለት የተለጠጠ ንግግርም ይመስለኛል …..አሁን ባለፈው አንዱ ለእህቱ የፍቅር ደብዳቤ ፃፈላት እህቱ ለጓደኛዋ ጮክ ብላ ታነብላታለች …. ደብዳቤ ፀሃፊው ምን ብሎ ቃላቱን አንኳተተው መሰላችሁ ….‹‹ሰኒየ እንደወንዝ ዳር ቁጨማ መለል ብሎ የወጣ ቁመትሽ ለሚመለከተው ሁሉ መግነጢሳዊ ሞገድ በዙሪያው እየበተነ ሽቅብ ወደደመና እንደሚተኮስ ሮኬት ወደላይ ያርጋል ›› እኔ ብሆን ‹‹ሰናይት ቁመትሽ ረዥም ነው ›› ነበር የምለው !! …የቱ ነው መግነጢሱ ? የቱ ነው ወደደመና የተተኮሰው ያረገው ? …..ልክ እንደዚህ ደብዳቤ የአንዳንድ ደራሲያኖች ፅሁፍም መግነጢስ ይበዛበታል …በራዲዮ ሲተረክ ስንቱን ሰማሁት …ለዚች አገር ሳይንስ ያስፈልጋታል ይሄ ሁሉ መግነጢስ ተሰብስቦ አንድ ሮኬት ካላመጠቀ ምን ዋጋ አለው ! ተረት ምን ይጠቅማል ቃል መደረት ምን ይፈይዳል … ይሄን ብናገር ‹‹ደነዝ›› ይሉኛል ይሄን ባልናገር ‹‹ዘገምተኛ ››ይሉኛል !

እንዲህና እንዲያ እያልኩ እያሰብኩ አንድ ቀን በር ላይ ቁጭ እንዳልኩ (ብዙ አልቆየሁም ጧት ሶስት ሰአት ተቀምጬ ወደ ስድስት ሰአት አካባቢ) ጩልሌው መጣ …. ጩልሌው የሰፈራችን ታዋቂ ሌባ ነው ! እኔን አይወደኝም… ምክንያቱም አንዴ በር ላይ ቁጭ ካልኩ የተሰጣ ልብስም ይሁን ውጭ ጋ የተቀመጠ እቃ በፅናት ስለምጠብቅ በቃ አበሳጨዋለሁ (ራሱ ነው የነገረኝ …ስትወለድ ጀምሮ ዘቡሌ ነገር ነህ አለኝ አንድ ቀን)

ቀጥ ብሎ ወደኔ መጣና ‹‹ አቡቹ ነፍሴ ….›› አለኝ ቀጥ ብየ አየሁት በፊስታል የሆነ ነገር ይዟል ! ሰላምታው የሚደምቀው የሆነ ነገር ሲፈልግ ነው ….የሌባ ሰላምታ !
‹‹ስማ ይሄንን መፅሃፍ ግዛኝ ! ዝም ብለህ ከምትቀመጥ በቃ ትጨመጭመዋለህ ›› አለኝ እውነቱን ለመናገር ‹‹ታነባለህ ›› ቢለኝ አልገዛውም ነበር ‹መጨምጨም› ቃሉ ደስ ይላል ! በነገራችን ላይ የጨ ዘር ያለበት ቃል ደስ ይለኛል ‹ጨምላቃ› ራሱ ስድብ አይመስለኝም ! …እና ከነፊስታሉ መፅሃፉን ሰባት ብር ገዛሁት (ምን ይሁን ምን አላየሁትም) ቆይቸ ከፊስታሉ ውስጥ ሳወጣው በቆየ ጋዜጣ የተሸፈነ ዳጎስ ያለ መፅሃፍ ነው ! የሸፋን ጋዜጣው ፖሊስና ርምጃው ይላል !! መፅሃፉን ሳልገልፅ የሸፋን ጋዜጣው ላይ ያለውን ዜና ማንበብ ጀመርኩ ‹‹ ባሏን ኮኮስ ቅባት አልገዛህልኝም ብላ በተኛበት በገጀራ የጨፈጨፈችው ሴት ተያዘች ›› ይላል ! ሳገባ ለሚስቴ በየሳምንቱ ኮኮስ ቅባት እገዛላታለሁ ብየ ለራሴ ቃል ገባሁ …. ማንበብ ያስተምራል ለካ !

መፅሃፉን ስገልጠው እንዲህ ይላል ርእሱ ‹‹የኢትዮጲያ ወንጀለኛ መቅጫ ህግ ›› ! ይች ሽፋኑ ላይ ያለች ሴት በዚህ ህግ መሰረት ምን ይፈረድባት ይሆን ብየ አሰብኩ ….ቆይ ግን ባሏ ገጀራውን ገዝቶ እቤት ማስቀመጡ ከኮኮስ ቅባት ይልቅ ለገጀራ ቅድሚያ መስጠቱ ምንን ያመለክታል ….ሚስቱ ሳስባት አሳዘነችኝ ፀጉሯ አሳክኳት ሊሆን ይችላል እኮ …(ሃሳቤ አሳቀኝ) በመንገዱ የሚያልፉ ጎረቤታችን ‹‹ እናቴ አቡቹ ብቻውን መሳቅ ጀመረ …እናቱ እንደሆነች ሰው አትሰማ …ፀበል ብትወስደው …››› ብለው ከንፈራቸውን መጠጡ(ሌላ ስም ሲለጥፉልኝ) …..ፊስታሉን ሳነሳው ከስር ደግሞ አንዲት መፅሃፍ መኖሯን ተመለከትኩ ተነሽ ያለች ሰማያዊ መፅሃፍ ….በወርቃማ ቀለም ‹‹የኢትዮጲያ ፌዴራላዊ ዲሞክሪያሲያዊ መንግስት ህገ መንግስት ›› ይላል አንዱን በቀኝ ሌላውን በግራ እጀ መዳፍ ላይ አስቀምጬ ክብደታቸውን ለካሁት

‹‹ የወንጀለኛ መቅጫ ህጉ ከህገመንግስቱ ይገዝፋል እንዴ ? ›› ብየ አሰብኩ …. ለእህቴ ይሄን ስነግራት

‹‹የመፅሃፍ ይዘትን በገፁ ብዛት የሚለኩ ማተሚያ ቤቶች ናቸው ›› አለችኝ አልገባኝም ! እህቴ ሲበዛ አንባቢ ናት …እርሷ እያነበበች እኔ ግን ሳላነብ በዝምታ እኩል አራት ሰአታት ሳሎን ብንቀመጥ ሰወች እሷን እንደምሁር በማዳነቅ እኔን ‹‹ዘገምተኛ ›› ይሉኛል ! እውነታው ግን መፅሃፍት የዘገምተኛው አለም ነፀብራቅ መሆናቸው ነው…..ደራሲወች ደግሞ ዝግመቱን አሳምረው ይቀምሩታል…ሰወችም እያዘገሙም ቢሆን የደራሲውን ሃሳብ ይረዳሉ ወይም ለዘላለሙ አይረዱትም !

በዚህ የረዥት ዝግመት ውስጥ እያለሁ ነበር ሁልጊዜ በረንዳችን ላየ ተቀምጬ አላፊ አግዳሚውን ስመለከት አንዲት ወተት የምታደርስ ልጅ ትኩረቴን የሳበችው ….አንድ ቀን ድንገት አይን ለአይን ተጋጨን ደነገጥኩ … ሙሉ ቀን እሷን ሳስብ ዋልኩ ….ዝምታየ ላይ ሌላ ትልቅ አዚም ተጨመረ ….እረሳታለሁ ብየ አስቤ ነበር ….ግን ጧት ከእንቅልፌ ስነሳ አይምሮየ አንደኛ ያቀረበልኝ ያደረ ፋይል ይችኑ ወተት አመላላሽ ልጅ ነበር ! ትላንት መቸ ነበር ?…አሁን ነው መሰል! ….አይምሮየን እስካሁን አላምነውም ! ምናልባት አዝግሞ ቢሆንስ ትላንት ላይ ቁሞ …..

ይቀጥላል !

‹‹ይሄም ያልፋል ››
(አሌክስ አብርሃም)
ነገሩ እንኳን ቁም ነገር ሁኖ አይደለም እንደው ትዝ ብላኝ እንጅ

አንዲት ወጣት የስራ ባልደረባ ነበረችኝ …ሳሮን የምትባል (ሳሪ ሂሂ) ቢሮ ውስጥ የማይወዳት የለም … ለሁሉም ሰው የምትጨነቅ …በቃ ማንም ካዘነ እርሷ አሳዳ ነው የምታፅናናው ለቅሶ አሳዳ ትደርሳለች የታመመ ትጠይቃለች የምታውቀው ሰው እንኳን ባይኖር አንዳንድ ቀን ብርቱካን ገዝታ ሆስፒታል ትሄድና አንዱን ህመምተኛ ጠይቃ ተዋውቃም ትመለሳለች ! ታሪከኛ ልጅ ናት !

አንድ ቀን ታዲያ የዛሬ አመት አካባቢ ነው … ቡና ልጋብዝህ ብላኝ አንድ ካፌ ውስጥ ተቀምጠናል ….ድንገት ከእኔ በስተግራ ወዳለው ጠረጴዛ ዙራ የሆነ ነገር እየችና ፊቷ በሃዘን ቅጭም አለ …በዛ ላይ አስር ጊዜ በሃዘን ከንሯን ትመጣለች ….እንደውም ጭራሽ አይኗ እንባ ኳተረ ! ምንድነው ጉዱ ብየ ቀስ አልኩና ወደምታይበት አቅጣጫ ዞርኩ …. አንድ ጎረምሳ ፊረንጅ ተቀምጧል ….‹‹ምን እያደረገ ›› አትሉኝም ?…… ቡና እየጠጣ አይደለም …ምግብ እየበላም አይደለም ……እያለቀሰ ! ከምር ስቅስቅ ብሎ እያለቀሰ! ስቅ ስቅ እያለው ቀይ ፊቱ ቲማቲም መስሎ ያለቅሳል ….(ለካ ፊረንጅም ሲያለቅስ አበሻ ነው የሚመስለው !)

እናም ወዳጅ እንዲህ አለችኝ ‹‹አብርሽ በናትህ ይሄን ፊረንጅ ላፅናናው አገራችን ላይ መጥቶማ እንዲህ ሲሆን ዝም ማለት ከምር ጭካኔ ነው እግዜርስ ይወደዋል ? ››
‹‹ይሻላል ? ማፅናናት ኤክስፖርት ማድረግ ልትጀምሪ ነው? ›› አልኳት ለቀልድ
‹‹አንተ ደግሞ በማይቀለደው ትቀልዳለህ ›› አለችና ተነስታ ወደፊረንጁ መንገድ ጀመረች ድንገት ከመሃል ተመልሳ በሹክሹክታ እንዲህ ስትል ጠየቀችኝ ‹‹ ስማ አብርሽ ‹ ይሄም ያልፋል> ማለት በእንግሊዝኛ ምንድነው ?››

አይ ሳሪ ዛሬ በሆነች ጉዳይ ትዝ ብላኝ ብቻየን እንደጅል ሳኩ ! ሳሪ ዛሬ አሜሪካ ነች (ሂሂሂ)
‹‹ሽረ ይሄም ያልፋል በእንግሊዝኛ ምንድነው ሳሪ ያበደርኩሽን መልሽ ››

የሙዚቃ ክሊፖቻችን ላይ የሚዘወተሩ እቃወች
ለአዲስ ጉዳይ መፅሄት ብቻ የተፃፈ
(አሌክስ አብርሃም)

በእኔ አመለካከት የሙዚቃ ነፍስ ዜማው ሲሆን ግጥም ስጋና አጥንቱ ነው ። ስጋ ደግሞ የተለያየ መልክ የተለያየ መጠን ይኖረዋል ። ልክ እንደሰው አካል ... ስጋን በመዋቢያ ማሸሞንሞን በአልባሳት ማሸብረቅ ይቻላል (ባለቤቱ ካልሰነፈ) ነብስን ግን የሚያስውባት ያው ተፈጥሮዋ እና ታድግ ዘንድ የምናጠጣት ፍቅር ነው ። እናም ዜማው ያላማረ ዘፈን ግጥሙ የቱንም ያህል ጥልቅና ምጡቅ ቢሆን አይስበኝም ! ነብስ የሌለው አካል ይሆንብኛል።

እንግዲህ አንዱ የዘፈን ስጋ ማሳመሪያ ‹‹ሜካፕ›› የሙዚቃ ክሊፕ ነው ። ክሊፕ በራሱ ግጥም ነው . . .ክሊፕ በራሱ ግን ዜማ አይደለም ! ትልቁ መተላለፍም ይሄው ነው ! እንደው በቴሌቪዥናችን አንድ ዘፈን እያየን (የሚታይ ዘፈን) ብንታዘብ የምናወጣው እልፍ አቃቂር የምንገረምበት መዓት ግርምት እንዳለ ሁኖ ክሊፖቻችን ላይ በተደጋጋሚ የሚታዩ መገልገያ ቁሳቁሶችን ድግግሞሽና ተመሳሳይነት ደግሞ ሌላው የትዝብት አይናችን መጣያ መሆኑ አይቀርም ...እኔም ዛሬ በዜማና ግጥሙ ተንደረደርኩ እንጅ መነሻየ በአገራችን ወቅታዊና ዘመናዊ ሙዚቃ የክሊፕ ቤተኛ የሆኑ ቁሳቁሶችን አልፎ አልፎ እያነሳን እንድንጨዋወት ነው ። ለመሆኑ ክሊፖቻችን ላይ በተደጋጋሚ የሚታዩ ቁሳቁሶችን ታዝባችሁ ይሆን ? የእኔን ትዝብት እነሆ

ጠመንጃ

በአገራችን የሙዚቃ ክሊፖች ውስጥ ጠመንጃ ከሳክስፎን እኩል ከማሲንቆ አቻ ተደጋግሞ ከመታየቱ ብዛት በአንዳንድ ዘፈኖችላይ የሙዚቃ መሳሪያ ይመስለኝ ጀምሯል ! በሹርባ የተዋበች በወርቅ የተሸቆጠቆጠች ድምፃዊት ኮለል ያለ የፍቅር ዘፈን እየዘፈነች እናተም የተወዛዋዦች እንቅስቃሴ የድምፃዊቷ ለዛ ደስ ብሏችሁ ቴሌቪዥኑ ላይ እንዳተኮራችሁ ድንገት ሰውነቱ ላይ ጥብቅ ያለች ቁምጣ የለበሰ አናቱ ላይ ሽርጥ የጠመጠመ ታጋይ መትረየሱን ይዞ ከተፍ ይልና ያንተከትከዋል .....ይህ ነገር በቀለምም በቅንብርም ዘፈኑ ጋር ፈፅሞ ስለማይሄድ ከነበራችሁበት ስሜት መንጥቆ ያወጣችኋል ! የዚህ ሲገርማችሁ ብዙ ሳይቆይ ክላሽንኮቭ ጠመንጃውን እንደያዘ ፊትለክ እያለ በሸንተረሩ ላይ የሚሮጥ ሌላ ጦረኛ ይከሰታል ...የባህል ዘፈኖቻችንማ ጠመንጃ የተሸከመ ወንድ ከሌለ ወዮላችሁ የተባሉ ይመስል ብረት አንቀው ብረት ብረት የሚል ለዛ ቢስ ዘፈናቸውን የሚያንቆረቁሩብን የትየለሌ ናቸው !

መኪና

የሚበረክቱት ዘመንኛ ዘፈኖቻችን መነሻቸው ፍቅር መድረሻቸው ፀብ ነው ... የፀቡ ምክንያት ደግሞ ሁሌም

አንድ አይነት !! ሴቷ ጥቅም ፈልጋ ሌላ ወንድ ስታይ ወይም ወንዱ ‹‹ምንም ሳይጎድልበት ›› ሌላ ሴት ጋር ጎራ ሲል ….በቃ! ክሊፖቻችን ላይ ከዚህ ሌላ የፀብ ምክንያት ካያችሁ ታዘቡኝ ።

እንግዲህ ዘፋኙ ወንድ ነው እንበል ፤ ያፈቀራት ልጅ ልቧ ውልቅ እስከሚል ዘንጣና ተቆነጃጅታ ወንበር ላይ ተቀምጣ አይኗን እያስለመለመች አብረው ዋይን ሲጠጡ ነበር …. ያውም በመሃል ስጦታ ይሰጣታል ‹‹ዋው› ትላለች እጇን ደረቷ ላይ ጣል አድርጋ ….ድንገት ግን ሌላ ወንድ(ባለመኪና) አየችና እሱን ክዳው እዛንኛው ጋር አጉል ነገር ጀመረች…መኪናወቹ ሁልጊዜ ተመሳሳይ መሆናቸው ደግሞ ይገርማል …

ምናለ የጭነት መኪና ሹፌር ብትወድ ….አንዳንዴ እንኳን በሃቂቃው እንደሚታየው የታክሲ ሹፌር ወዳ ብትከደው ምናለ የኤክስካቫተር ሹፌር አይታ ብትወድ (ክህደቱ ልማታዊ ይሆን ነበር) ሁሌ ፓጃሮ፣ ሁልጊዜ ቪ ኤይት …..ብቻ የሆነ ሁኖ ክሊፕ ላይ መኪና አይጠፋም ! መኪና ውስጥ ስትገባ ወይም ባለመኪናውን ስማው ስትወርድ ዘፋኙ ግንብ ለግንብ እየተከለለ ተደብቆ ይከታተላታል … ስትሳሳም ቢያያትም ምንም አይናገርም ‹‹ቻይ››ነው ! (አክተር ታጋሽ ነው)

ስልክ

ያው የቅድሚ ልጅ ተደብቃ ስልክ ማውራቷና ዘፋኙም ተደብቆ ስታወራ በመስማቱ እራሱን ይዞ ሶፋ ላይ ሲወድቅና በሃዘን ሲዘፍን ይታያል …ብቻ ክሊፖቻችን ላይ ስልክ ይበረክታል በተለይ ክሊፕ ላይ የምትተውነው ቆንጆ ክህደት ስትጀማምር ስልክ ነፍሷ ነው ! ከሃዲው ወንድ ከሆነ ስልክ ሲደወልለት ወጣ ብሎ ማናገረ እንዲሁም ስልክ ሲጠራ የሴት ስምና ምስል ስልኩ ላይ መታየት ይዘወተራል ። ስልክ ስልክ ….

የልብስ መያዣ ሻንጣ

እንግዲህ ዘፋኙ የልጅቱ ነገር ከአቅሙ በላይ እንደሆነ ይነግረናል … ‹‹ደሃ በመሆኔ ነው ግዴለም ፈጣሪ ይሄን ጉድ ይይልኝ የስራሽን ይስጥሽ ›› ብሎ በድህነቱ የተካደው ሽበላ ‹‹ግራውንድ ፕላስ ዋን › ቤቱን ለ‹ከሃዲዋ› ወዳጁ ትቶላት ሻንጣውን እየጎተተ ውልቅ ይላል ። የልብስ ሻንጣ ዘመናዊ የሙዚቃ ክሊፖቻችን ላይ በብዛት ከሚታዩ እቃወች የመጀመሪያውን ደረጃ ሳይዝ አይቀርም …እንደውም አንድ ጊዜ መርካቶ የመንገድ ሻንጣ ልገዛ ሂጀ ሻጩ ያለው ነገር ትዝ አለኝ ‹‹ አንበሳየ ግዴለህም ግዛው ለክሊፕ ሁሉ የሚሆን ሻንጣ ነው ››

እንግዲህ ንብረት ቆጠራችንን እዚህ ላይ ገታ አድረገን እስኪ ሃቂቃ ኑሯችንን ከምናባዊ ክሊፓችን እናመሳክረው ….እስቲ አሁን ማን ይሙት ሌላው ቢቀር በዚህ ዘመን በሚከሰቱ ፍችወች ‹‹ፈጣሪ ይፍረደኝ ›› ብሎ ሻንጣውን ይዞ ውልቅ የሚለው ማነው ? በበኩሌ …እኔ እስካሁን ሰወች ሲፋቱ ሻንጣ ይዘው ውልቅ ሲሉ ያየሁት ክሊፕ ላይ ብቻ ነው …እኛ ሰፈር ያየሁት ሽማግሌ ወይም ፖሊስ ይዘው መርፌ ሳይቀር ሲካፉሉ ነው … ያውም ‹‹ይሄ የአያቴ ባርኔጣ ነው አላካፍልሽም ….ይሄነኛው የድሮ ባሌ የገዛልኝ ጫማ ነው ››እየተባባሉ እንዲህ አይነት ክሊፕ ግን ቢሰራ የህያው አለም ነፀብራቅ ምናምን ይሆን ነበር …

ቀላል እኮ ነው ለምሳሌ ግጥሙ እንዲህ ቢሆን
ምናለ መጥበሻው ለኔ ቢሆን ፍቅሬ
ማንኪያው ላንች ይሁን ግዴለሽም ፍሬ (ፍሬ ብትሆን ሚስቱ)
ለፍቸ ደክሜ የቋጠርኳት እቃ
ትዳሬን ስፈታ ተበተነች በቃ
ቃ
ቃ ይላሉ ተቀባዮቹ ! በር ላይ መጥበሻ የብረት ድስት ምናምን ይዘው እየጨፈሩ … አሁን ህዝቡም ብሶቱን ያያል (ሃሃሃ)

ወደቁም ነገሩ ስንመለስ …..ስለመለያየት ክሊፕ የሚሰሩ ሰወች ስቱዲዮ ከመሄዳቸው በፊት ፍርድ ቤት ጎራ

ብለው የፍች ጉዳዮችን ቢመለከቱ ጥሩ ነው ባይ ነኝ ! የቀበሌ ቤት እንዳትካፈለው ሚስቱን በገጀራ ሰንዝሮ ስለሳተ ወንድ ሊሰሙ ይችላሉ ...እነሱ ባለፎቅ ቪላ ለፈቷት ሴት ‹‹ውሰጅው ›› ብለው ቅጥፖት የሚመስል ክሊፕ ይሰራሉ ...እንዲህ ቢሆንማ ማን ትዳር ላይ ይቆያል ? ስንት አለ ንብረቱን ላለመካፈል እየተቃሰለ ቁጭ ያለ! ባሁኑ ሰአት አገራችን ላይ ቤት ይቅርና የስልክ ቀፎ ከትዳር አጋር በላይ ስሜት የሚሰጣቸው ስንቶች ናቸው ? ማንስ ነው ሚስቱን ሌላ ወንድ ጋር አይቷት ‹‹ቻልልኝ ሆዴ›› ብሎ እንዳላየ የሚሆን ...ሴቶች ላይ በጥርጣሬ አንዴ አሲድ አንዴ ጥይት ሲያርከፈክፍ ያየነው የትኛውን ወንድ ነበር ታዲያ ? የገሃዱ አለም ነፀብራቅ ከሆነ በደንብ ማንፀባረቅ ነው !

ኧረ ዘፋኞቻችን ...ቢያንስ ፍርድ ቤት ቀርባችሁ በሰላም ስትፋቱ እቃ ስትካፈሉ ምናምን አሳዩን እንጅ የምን ውሃ ቀጠነ ብሎ ሻንጣ መጎተት ነው ! (መለያየት ካልቀረ ህጋዊ ፍች የሚታይበት ክሊፕ ስሩልና)

እንደው ካነሳነው አይቀር የቆዩ ዘፈኖችን በአዲስ መልክ እንደሚዘፈኑት ለምን ለቆዩ ዘፈኖች ክሊፕ አይሰራም ? ...እውነቴን ነው ጥሩ ጥሩ ፊልም የሚመስሉ ክሊፖች ይወጣቸዋል ...ለምሳሌ
ያንባሰል ማር ቆራጭ ይወርዳል በገመድ
አደራ ቢሰጡት ይበላል ወይ ዘመድ .....

ለሚለው ግጥም እንደደብረዳሞ አይነት ረጅም ገደል ላይ ወገቡን በገመድ የታሰረ ማር ቆራጭ ቁልቁል ሲወርድ የሚያሳይ ክሊፕ አይታያችሁም ? ሁልጊዜ ሆቴል ለሆቴል ሶደሬ ለሶደሬ ከመዞር እንዲህ አይነት ‹‹አድቬንቸር ክሊፕ›› ቢሰራልን የአገራችንን ‹‹የክሊፕ ጥቡብ›› አንድ ደረጃ ከፍ ያደርጋል የሚል ሃሳብ አለኝ (ሃሃሃ) በሉ ደግሞ ገደል ለገደል እየዘራችሁ ‹‹ድምፃዊ እከሌ ተፈጥፍጦ ሞተ ›› በሚል ዜና የፈረደበትን ዜና አንባቢ ‹‹ቢዚ›› እንዳታደርጉት ! ሌላ ቀለል ያለ ዘፈን ልጠቁማችሁ እና ላብቃ ....

የድምፃዊ ባህሩ ቃኘ ዘፈን ....
‹‹ያዝ እጂን ...ዝጋ ደጂን ...ሳም ጉንጪን ››....ይችስ ? ይችንማ ብዙሃኑ ዘፋኞቻችን ይወዷታል ! ባይሆን ማስገደድ ነው ብላ ቆንጂ ሻንጣዋን እየጎተተች መኪና ወዳለው ሌላ ወንድ ፈትለክ እንዳትል ጠንቀቅ ብለን !

ስንት ሃሳብ አለብን ...ቢሆንም
(አሌክስ አብርሃም)

እዚህ አፍንጫችን ስር ሱዳን ሁለት ደነዞች አልስማማ ብለው አስር ጊዜ አዲስ አበባ እየመጡ ይነታረካሉ.... ህዝባቸው በችግር ይሰደዳል ይራባል ! አገር ሳይሆን ምሽግ ገንጥለው የወሰዱ ይመስል ገና ዳዴ የምትል ሙጥቅላ አውራጃ የጦር ቀጠና አድርገው ደም ይራጫሉ !
እዛ ቅጡ የጠፋት ወፈፌ ግብፅ ውሉ ባለየለት ድንፋታ ‹‹ፈርሚ አልፈርምም ›› ንትርክ ታደነቁረናለች ሳትወድ ብግድ መፈረሚ ላይቀር .....እንደንቁራሪት ውሃ ለውሃ መጮህ ምንድን ነው !
እዛ ማዶ ደግሞ ናይጀሪያ ቦኮሃራም የሚባል ኖራ ጭንቅላት ከፊቱ ያገኘውን ህዝብ ይፈጃል በጥይት ነሽ በቦንብ ነሽ ...ሰላማዊ ሰው ፈጅቶ ‹‹ዛሬ ስራ ቀዝቅዟል አርባ ሰው ብቻ ነው የገደልኩት›› ይለናል ኢራቅን አስር ሽ ወፈፌወች እያመሷት ነው ! አሜሪካ ስልችት ብሏት ከሩቅ ነገሩን ታያለች ፈትፍታ ፈትፍታ ባመጣችው ነገር ! ነገረኛ !

‹‹ማን ከማን ያንሳል›› ያለው አልሸባብ ዙሪያችንን እየዞረ ቦንብ ያፈነዳል ይሄው ኬኒያ በቀደም ፈንጅ አደንድቶ ህዝቡን ፈጀው ...ቱሪስቶችም ‹‹ፍንዳታ የሚሳበኝው በፊልም ነው ›› ብለው ከኬኒያ ቅርት !! የቱሪዝም ገቢዋ ሽምድምድ ! አልሸባብ ይሉት ቢጠርጉት የማይፀዳ ሽረሪት !

እዚች እግራችን ስር ሰውየው አኩርፈው ቁጭ ብለዋል አባባ ኢሳያስ አፈወርቂ ... ወደብን ያህል ነገር ለክሊፕ መስሪያ ብቻ እንዲውል ፈርደው ዘፋኞቻቸው በጀልባ እየተንሳፈፉ ኮሪና ይሉናል ...የአገር ኢኮኖሚ እንደሽንኮራ እየተመጠጠ !

ወ.....ዲያ ማዶ ብራዚል ላይ አለም ያብዳል ያውም ልብሱን ጥሎ ...ፊፋ ደግሞ ራሱ አለምን ሁሉ ለእብደት ሰብስቦ ሲያበቃ ‹‹የአለም ዋንጫ ለአለም የአየር ብክለት መጨመር ትልቅ አስተዋፅኦ እያደረገ ነው ›› ይለናል ! አንችው ታመጭው አንችው ታሮጭው አሉ ! የአለም ዋንጫ ማለት የአለም አገሮች ተሰብስበው የሚጫወቱት እቃቃ ይመስለኛል እኔ !

እና እኛ ስንት አሳብ አለብን እንኳን ሌላ ነገር ሰማችን ራሱ እየጠፋብን እኮ ነው ! አዎ ስማችንን ሳይቀር በምንረሳበት በዚህ ውጥንቅጥ አለም ውስጥ.... መሬት ውሻ እንዳየች ድመት ብትነፋፋና ሰማይ ብትነካ ሰማይም ጊዜ እንደጣለው ዶክተር ኢንጅነር መሬት ወርዶ ዘጭ ቢል ..ባጭሩ ሰማይ ዝቅ መሬት ከፍ ቢል የማንረሳው አንድ ጉዳይ አለ
.
.
.
.
ነገ .....

ቅ
ዳ
ሚ
ነ
ው !! እደግመዋለሁ ቅዳሜን ከምንረሳ ሰኞን ለዘላለም ማክሰኞን ለግማሽ ዘላለም እሮብን ለእሩብ ዘላለም ሃሙስን ለሲሶ ግማሽ ዘላለም እንርሳ አርብነ ግን ቅዳሜን የምናስታውስበት ቀናችን ነውና እንርሳህም ብንለው አይረሳን ማን ላይ ቁመን ቅዳሜን ልናበስር !

‹‹ኩማንዶው ››
(አሌክስ አብርሃም)

በህፃንነቴ የተሸወድኳት ሁልጊዜ ትዝ ስትለኝ ለብቻየ የምታስቀኝ አጋጣሚ ናት .....
ጋሽ አስፋው እና እማማ ዘቢደሩ የሚባሉ ባልና ሚስቶች የቤተሰባችን ጥብቅ ወዳጆች ነበሩ ! . . . ታዲያ ሁልጊዜ ማታ ማታ እኛ ቤት ቡና ስለሚፈላ ጋሽ አስፋው ቤታቸው ከመግባታቸው በፊት (ካመሹባት) እኛ ቤት ጎራ ብለው ቡና ጠጥተው አንዳንዴም ራት በልተው ይሄዳሉ ! ሚስታቸው እማማ ዘብይደሩም ቡናው ሲፈላ ይጠሩና ባልና ሚስቱ ባንድ ላይ እኛ ቤት ነው የሚያመሹት ! ብዙ ጊዜ እርስ በርስ አይስማሙም ጋሽ አስፋው ‹‹ትንሽ›› ስለሚጠጡ ሚስታቸው በአስፈሪ ቁጣ ስድብና ርግማን ያወርዱባቸዋል ! ባል ሲሰክሩ ፈሪ ነው የሚሆኑት ሚስት ደግሞ የባላቸው ስካር አራስ ነበር ነው የሚያደርጋቸው ...ከድሮ ጀምሮ ባል ይሰክራሉ ሚስት ይሳደባሉ ይራገማሉ !

አንድ ቀን ታዲያ ቡናው ተፈልቶ እትየ ዘብይደሩ ተጠሩና መጡ . . . ጋሽ አስፋው ግን አመሹ . . .ቢጠበቁ ቢጠበቁ የውሃ ሽታ ! እትየ ዘብይደሩ ከህፃንነታቸው ጀምሮ የሚያውቁትን ስድብና እርግማን አጠረቃቅመው ግማሹን ምላሳቸው ላይ ቀሪውን ደግሞ የምላሳቸው ሲያልቅ ቶሎ ለመተካት ጉሮሯቸው ላይ አስቀምጠው በር በር ሲያዩ . . . የጋሽ አስፋው ድምፅ ከውጭ ተሰማ ‹‹ወይኔ አስፋው ...ወንዱ ...በኖርኩበት መንደር ልደፈር ... ይሄ እኔን ብቻ አይደለም ሚስቴንም ልጆቸንም መድፈር ነው ...አንላቀቅም ›› እያሉ ብቻቸውን እያወሩ እና እየፎከሩ መጡ !

በሩን ከፍተው ሲገቡ ቤት ውስጥ የነበርነው ሁሉ በድንጋጤ ታመስን ! ግንባራቸው ተፈንክቶ ጋቢያቸውና ካፖርታቸው በደም ተሸፍኗል ! ሁሉም ሰው ደነገጠ ...‹‹ቶሎ በሉ ማሰሻ ጨርቅ ...ተኩሱላቸው ቁስሉን ....›› ተንጫጫ ሰው ሁሉ እናቴ በተለመደ ርጋታዋ የምጣድ ማሰሻ አምጥታ እሳት ላይ ጫፉን አስጠጋችው ....ጭሱ ቤቱን ሞላው የተቃጠለ ጨርቅና የጎመንዘር ሽታ ቤቱን ሞላው (ሊያስለኝ ነበር) ወዲያው ጫፉ በእሳት የተያያዘውን ጨርቅ መሬት ላይ ደፍጥጣ እሳቱን ካጠፋች በኋላ አባ አስፋው ቁስል ላይ ተኮሰችው . . . ስትደጋግመው ደሙ ቆመ ደማቸውና የጨርቁ ጥላሸት ተደባልቆ እርጅና ከሸበሸበው ቆዳቸው ላይ ‹‹አብስትራክት›› ስእል ሰራ .... ወዲያው እናቴ አንድ አይናቸውን ጨምሮ በሻሽ አሰረችላቸው . . .

‹‹ምን አገኝቶዎት ነው ጋሽ አስፋው እንዲህ የደም ጎርፍ . . . ››
‹‹ደበደቡኝ ››
‹‹እንዴዴዴዴዴዴ ህግ ባለበት አገር እነማን ናቸው ››
‹‹ አንጀቴ ህግ . . . ››
‹‹እኮ ተናገር ማነው እንዲህ በኖርንበት አገር የደፈረን ›› አሉ እማማ ዘቢደሩ ደሙ ስላስደነገጣቸው ስድቡንና ርግማኑን ረስተው ከባላቸው ጎን በእልህ እንደቆሙ !
‹‹ምናባቴ አውቄው ወርቄ ›› ሚስታቸውን ወርቄ ነው የሚሏቸው
‹‹እንዴት ያሉ ሰወች ናቸው አታውቃቸውም እናስቀፈድዳቸዋለን ...››
‹‹ኧረ እሱስ አንድ ነው . . .የገደል ስባሪ የሚያህል ጉድ ለወሬም አይመች . . . ጎልያድን አክሎ ፊቴ ቢገተር እማይበጃቸሁ እንስ ይበል ፊቴ ዳዊትን አክየ ቁጭ !! እዚህ ጡርየ በር ላይ ቁሞ ሳየው የምን ምሰሶ ነው ብየ ላልፈው . . . ለካ ሰው ነው. . . በስማም ምኑን ቢበላው ያንን አከለ .... ›› ብለው አማተቡ ....ከዛም ቀጠሉ

ንግግር የለ ምን የለ ያንን ቢዘረጋ ጎጥምን ነክቶ የሚመለስ እግሩን አንስቶ ቢሰነዝርብኝ በእግሩ የቀዘፈው ንፋስ ጋቢየን ከላየ ላይ ሊገፈው . . . ››
‹‹አሃ ምን አድርግ ብሎ ነው ደርሶ እሚራገጥ ›› አለ አባቴ
‹‹ምናባቴ አውቄ መድሃኒያለም አባቴ ይወቅ እንጅ . . .የእግሩ ርዝማኔ እናቴ ይሄን አናተ በር የቆመ የኢኒትሪክ ግንድ ያህላል ...እንደው ቸ.....ው ቢያረገው ‹‹አስፋው አንበሳው ›› አልኩና ጎንበስ ስል የጡርየ የኮክ ዛፍ ላይ

የተንዥረገገውን ኮክ ሁሉ አርግፎ ሜዳውን ሁሉ ኮክ ሞላው . . .››

‹‹አሃ ምን ያለ ሰው ቢሆን ነው በብትር እንኳ ከማይደረስበት ዛፍ ላይ ኮክ የሚያረግፍ ›› አለች እናቴ ተገርማ እኔም ተገርሚያለሁ . . .የእማማ ጡርየ ኮክ ርቀቱ የትና የት በአጥሩ ብቅ ብሎ የደረሰ የኮክ ፍሬው ተንዥርግጎ ምራቅ ሲየስውጠኝ ነው የከረመው ! በድንጋይ ብንሞክር በብትር ብንጠራራ አንደርስበት ብልን የመንደሩ ውጫጭ ሁሉ ተስፋ ቆርጠን ትተነው ነበር . . . አሁን አቶ አስፋው የምስራች ይዘው ከተፍ አሉ ‹‹ሜዳውን ሁሉ ኮክ ሞላው ›› ወቸ ጉድ ምናይነት የተባረከ ሰው ነው ... ተቁነጠነጥኩ !

‹‹ኩማንዶ ሳይሆን አይቀርም ›› አሉ ጋሽ አስፋው
‹‹አሃ ኩማንዶ የሆነ እንደሁ ዛዲያ ማንንም አንደአህያ ይርገጥ ተብሏል እንዴ . . .››

‹‹ ኩማንዶ ነው ያስባለኝ .....እንግዲህ አንድ ሁለቴ እንደመከትኩት በሶስተኛው በጨለፍታ ፊቴን አገኘው . . . አለም ተደባለቀብኝ ሰማይ ልሁን መሬት ልቤን ሰወረው ›› አሉ ጋሽ አስፋው !

ከዛ በኋላ ያወሩትን ግን አልሰማኋቸውም ቀስ ብየ ወደጓዳ ገባሁና አቃ የያዘ ፌስታል እቃውን መሬት ላይ ደፍቸ ፌስታሉን አጣጥፌ በኪሴ በመቆጠር በጓሮ በር ወጣሁ .... ጨለማው ሳያስፈራኝ ወደማማ ጡርየ ቤት በረርኩ ሜዳውን የሞላውን ኮክ እያፈስኩ በፌስታሌ ስሞላው ታየኝ ፌስታሉ ይበቃኝ ይሆን . . .ካልበቃኝ እመለሳለለሁ . . . ስሮጥ ውሻወች ጮሁ ወይ ፍንክች . . . ልክ የተባለው ቦታ ስደርስ ፍጥነቴ ቀነስኩ ደግሞ ኮክ ረግጨ በጀርባየ እንዳልዘረጋ (ሃሳቡ ጣፈጠኝ) ከእግሬ ስር ያለውን መሬት ኮክ ሞልቶ አሰብኩት .. . አንዱን የበሰለ ኮክ ረግጨው ጭፍልቅ ሲል . . .

መጀመሪያ እግሬን በጨለማው ውስጥ ልኬ መሬቱን ፈተሽኩ . . .ከዛም ቀስ ብየ ተቀመጥኩና መሬቱን በእጀ አሰስኩት አፈር. . . ድንጋይ እንደገና አፈር ...ጠጠር ....የጠርሙዝ ስባሪ .....ጠጠር . . .አካባቢውን አንድ ሳይቀር እየተንፏቀቅኩ በጀም በእግሬም ዳሰስኩ ወፍ የለም ! ምናልባት ‹ኩማንዶው › ለቅሞ ወስዶት ይሆን እንዴ ....ልክ ይሄን ሳስብ ኮማንዶው ትዝ አለኝ ! እንደውም ከኋላየ እንደቆመ ከበደኝ ቅፍፍ አለኝ .....ፍርሃት ለቀቀብኝ አሁን ከኋላየ ቁሞ ቢሆንስ በዛ በእግሩ እንደበሰለ ኮክ ቢደፈጥጠኝስ(በጨለማው ውስጥአማተብኩ) ቀስ ብየ ወደኋላየ ዞርኩ ሰው የለም ! ግን ፈራሁ በጣም ፈራሁ ....ድንገት ብርርርር ብየ ሩጫየን ወደቤቴ አደረኩት . . .

እያለከለኩ እቤት ስደርስ ጋሽ አስፋው አሁንም ያወራሉ ‹‹ እግሩን ሲያነሳው ጨረቃዋን በካልኾ ያወረዳት ኮክቦቹን ከሰማይ ያረገፋቸው ነበር የመሰለኝ እቤት እግር አረዛዘም እናተ ምኑን ቢበላው ነው እንደዛ .... ኩማንዶ ነው ግዴላችሁም ›› ይላሉ . . . ጨረቃዋን ደግሞ የት ይሆን ያወረዳት ኮክቦቹንስ ያረገፋቸው የት ይሆን ... ያ የተረገመ ‹ኩማንዶ› ...

ከዛን ጊዜ ጀምሮ ሚስታቸው እማማ ዙብይደሩ ባላቸው ሲሰክሩ ‹‹ኪዳነምረት እናቴ ኩማንዶ ትላክብህ ›› ይሏቸዋል
ጋሽ አስፋው ታዲያ ‹‹ አይ ወርቁ ኑሮ ያሰከረውን ሰው የኩማንዶ ርግጫ መቸ ሊመልሰው ብለሽ ›› ይላሉ አባቴ በመስማማት ራሱን ይነቀንቃል !

ጧት እናቴ ጋሽ አስፋውን እንዲህ አለቻቸው ‹‹ጋሽ አስፋው ለፖሊስ እናመልክት እንዴ ››
‹‹ለምኑ ›› ብለው ጠየቋት በግርምት
‹‹አሃ ለኩማንዶው ነዋ ››
ፈገግ ብለው ወደኋላቸው ገልመጥ አሉና ድምፃቸውን ቀንሰው ‹‹ዝም በይ ! ዙብይደሩ እንዳትቆጣ እዚሁ ፈልስሚው ነው ...ኩማንዶም የለ ሞቅ ብሎኝ አዚች ዳገቷ ላይ ወድቄ ነው ›› አሉ አየሳቁ እናቴ አፏን አፍና በሳቅ ፈረሰች ! እኔ ግን ጋሽ አስፋውን ተቀየምኳቸው እንደውም ረገምኳቸው ‹‹በምሽት አፈር ሲያስቧድዱኝ እንዳስመሹኝ መድሃኒያለም ኩማንዶ ይላክበዎት ›› ጋሽ አስፋው ዛሬ በሂወት የሉም በ‹‹ኩማንዶ ጥቃት››

ሳይሆን ታመው አርፈዋል !

ለአዲስ ጉዳይ መፅሔት ብቻ የተፃፈ

ጠቅሞ ላይጠቅም
(አሌክስ አብርሃም)

ጓደኛየ አለምነህ ‹‹ትልቅ ሰው›› ነገር ነው መካሪ ምናምን ! የዘጠነኛ ክፍል ተማሪወች እንደነበርን አለምነህ ጋር ተዋወቅን ....እንዴት እንደተዋወቅን ረስቸዋለሁ እንኳን እንዴት እንደተዋወቅን እንዴት ጓደኛ ለመሆን እንደበቃንም ትዝ አይለኝም ብቻ እስካሁን ጓደኛ ነን ! ባህሪው በጣም ደስ ይላል .... በተለይ ለኔ እርሱ ጋር ስቀመጥ ባህላዊ ቲያትር የምመለከት ነው የሚመስለኝ (ባህላዊ ቲያትር የሚባል አለ እንዴ? . . . እኔኛ) እናቴ ታዲያ እንዲህ አለችኝ ‹‹ አሁን ገና ነብስ ያለው ቁም ነገረኛ ጓደኛ ጋር ገጠምክ››

እንዴት መሰላችሁ በቃ አለምነህ ይመክራል የመምከር ፀጋ አለው ‹‹ አብርሽ መቸስ ሰው ከፈጣሪ የተሰጠው አንዱና ትልቁ ፀጋ አይኑን በአይኑ ማየት ነው ...እንግዲህ ልጆች አይደለንም አግብተህ ወልደህ ማየት ምኞቴ ነው ...›› ይላል
‹‹ እሽ ›› እለዋለሁ
‹‹ አብርሽ አትቀልድ ወዳጄ ‹‹ ቃል የእምነት እዳ ነው ›› እዳለ ባለቅኔው ዝም ብለህ እሽ አትበል ...እሽ እኮ ት.....ልቅ ቃል ነው ...ቃል ኪዳን ነው ››
‹‹ታዲያ ምን ልበል ››
‹‹እሱማ ምን ትላለህ ያልከውን አድርግ እንጅ ››
‹‹ እሽ ›› እለዋለሁ ! እንሳሳቃለን

‹‹ እኔ የምልህ አብርሽ እንደው የሚቀርቡህ ሴቶች ሁሉ በፀባይ ብትል በመልክ ብትል ግሩም ናቸው ...(እስኪ አሁን ግሩም የሚለውን ቃል ከየት አመጣው ?ይገርመኛል) ....አንተም ብትሆን አንድ ያልተመቸህ ነገር ቢኖር እንጅ ሳውቅህ ከዛ ከዚህ የምትል ልጅ አይደልህም ...ረጋ ያልክ ከይሲ ነህ ›› ሁለታችንም እንስቃለን ! አለምነህ እየሰደበኝ እንኳን ያስቀኛል ....ረጋ ያለ ተሳዳቢ ነው

‹‹አያስቅም አብርሽ ...ጥርስህን ያርግፈውና አያስቅም ...እስቲ አሁን ሰሎሜ ጋር በምን ተለያያችሁ ምን ጎደላት ንገረኝ አብርሽ ንገረኝ ›› ሰሎሜ ጓደኛየ ነበረች
‹‹ ሰሎሜ ት....ንሽ ዝምታ ታበዛለች ››
‹‹ዝምታ እኮ ብልህነት ነው ... ‹የእግዚአብሔር ፈቃድ ይሁን ዝም አልን ›ይላል መፅሃፉ ብልህ ከዝምታ ውስጥ ብዙ ቁም ነገር ይማራል ››

‹‹ ታዲያ የሶሎሜ ዝምታ በዛሃ ! አያስተምር አያዝናና በቃ ዝም!! .... በስልክ ሳይቀር ዝም ትላለች ራሷ ደውላልኝ ሁሉ ዝም ትላለች ›› እውነቴን ነበር ሰሎሜ አስደንጋጭ ውበት የሰጣት ልጅ ነበረች ምን ያደርጋል ....ሶል ስላት አየት አድርጋኝ ዝም ሶሊ ስላት ፈገግ ብላ ዝም እንዴት ነበር ውሎ ስላት ‹‹ምንም አይል›› ብላ ዝም በቃ ዝም ! እጇን በለስላሳ እጆቿ እየነካካች ብቻ ዝም ! ሰሎሜ ሂለን ኬለርን ትመስለኝ ጀመረ ! በዳሰሳ

ብቻ ነው ወጓ !በእርግጥ ሰትዳስሰኝ በእጇ ውስጠ አልፎ ልቤን የሚሞቀው ፍቅር ብዙ የሚነግረኝ ነገር አለ ! ቢሆንም በዛ ባዶ ቃል ፍቅር ባይሆም ፍቅርም የቃል ቅመም ጣል ካልተደረገበት ደንዙዝ ይሆናል ! ቀስ እያልኩ መራቅ ጀመርኩ በመጨረሻ በቃ ሶል እንለያይ ስላት እጇን በእጆቿ ጠበቅ አድርጋ ይዛ ……..ዝም !

‹‹ እኮ ፍቅር ማለት እኮ ይሄ ነው ዝምታዋን ካልሰማህ ምኑን አፈቀርካት …ደግሞ ስትጋቡ ይከፍትላት ይሆናል ››
‹‹ ኧረ ባክህ ተወኝ እፏ የተሰራው ከቀለበት ነው እንዴ ሳገባት የምታወራው ? ››

‹‹ እሽ ናርዶስ ምን ጎደላት …››

‹‹ናርዶስ እንኳን አሪፍ ልጅ ነበረች ግን ወሬዋ ሁሉ ,ካራት, ሆነ ….እኔ ደግሞ ካራት ሰለቸኝ ›› እውነቴን ነው ናርዶስ ስቃ የምታስቅ ከሳቅ የተሰራች ልጅ ነች ! የምትስቅበት ነገር ብታጣ ‹‹ እንዲህ ቡጥጥ ብለን ሳንስቅ መቀመጣችን አያስቅም ›› ብላ የማይቋረጥ ቅጭልጭል ሳቋን ትለቀዋለች ! መንገድ ላይ እኔና ናርዶስን ያየን ሰው ፈገግ ማለቱ አይቀርም በቃ የሆነ ሳቋ የሚጋባ አይነት ልጅ ናት …አባቷ ወርቅ ቤት አላቸው ወርቅ ነጋዴ ስለሆኑ ነው መሰል ማንኛውንም ሰው በጥርጣሬ ነው የሚያዩት የሆኑ የደህንነት ካሜራ ነገር ናቸው !

ናርዶስ ለመጀመሪያ ጊዜ ስታስተዋውቀን ‹‹ እንደምነህ ›› አሉኝ ከእግር እስከራሴ ‹ስካን › አድርገውኝ ሲያበቁ

‹‹ደህና ››

‹‹ ምነው ደህና ብቻ …እግዚአብሔር ይመስገን ማንን ገደለ …ያው እንግዲህ ልጇ ነህ ያየሁትን ጥፋት መምከር ነው እኔ መደባበቅ አልወድም ›› አሉኝ ሳቁ መጣብኝ ! ናርዶስ ትስቃለች ! እንግዲህ ቶሎ ተጋቡና የልጅ ልጅ አሳዩና (ኧረ ጎራው ናርዶስ ብትወልድ ሰው ሳይሆን የዘጠኝ ወር ሳቅ የምትወልድ ነው የሚመስለኝ) አጉል ነገር ላይ ሁሉ ትስቃለችኮ ከምር እየሳቁ ((እንትን)) አይገርምም ? (እንደው ግመና አይወራም እንጅ)

እንግዲህ ናርዶስ ከሳቋ ቀጥሎ ወሬዋ ሁሉ ወርቅ ብር እና ካራት ነው ‹‹ አብርሽ ሃያ አንድ ካራት ወርቅ ሃብል ግዛ በናትህ እዚህ አንገትህ ላይ በጣም ነው የሚያምረው ›› ትለኛለች ስለሃብል ከአስራ ስምንት ካራት ጀምራ እስከምናምን ካራት ጥግብ እስክትል ካወራች በኋላ ስለቀለበት ትቀጥላለች …‹‹ ወንድ ልጅም ጎላ ያለ ቀለበት ሲያደርግ ነው የሚያምረው በዛ ላይ ራስህንም ለመጠበቅ ጥሩ ነው ››

‹‹ በወርቅ እንዴት ነው ራስ የሚጠበቀው ..ከሰላቢ ነው …ከቡዳ ›› እላታለሁ

‹‹ ኧ ከሰው ….ደህና ቀለበት ማለት የብረት ቦክስ በለው ፀብ ቢፈጠር እንኳን ለቦክስ …ሂሂሂሂሂሂ››

‹‹እንዴ ለምን ፀብ ይፈጠራል ››

‹‹ወንድ አይደለህ እንዴ አንዳንዴ ባይፈጠር እንኳን ራስህ መፍጠር አለብሃ ››

‹‹ ምን ቦክስ ነው የምፈጥረው ›› ተገርሜ እጠይቃታለሁ

‹‹አዋ ››

‹‹ እንዴዴዴዴዴ አብደሻል እስኪ አስቢው ነገር አፈላልጌ መንገደኛ ጋር ስጣላ ››

‹‹ ማን መንገደኛ ጋር አለህ ››

‹‹እና ….››

‹‹ አንዳንዴ እኔም ጋ ቢሆን …የፍቅር መግለጫ እኮ ነው ሂሂሂሂ›› በቃ ናርዶስ ከማጌጫ እስከመቀጣቀጫ ምርጫዋ ሃያ አንድ ሃያ አራት ካራት ወርቅ ነው …በኋላ እንደታዝኩት የእውነትም አንድመታት ትፈልግ ነበር ‹‹እንደወንዶቹ አንዳንዴ በጥፊ ብትለኝ ..›› ያለችኝ ቀን እንደወንዶቹ በሄድኩበት ቀረሁ ! የካራቱ ሲገርመኝ ጭራሽ በፍቅር ስም ካራቱ ! ስንት አመል አለ …ታዲያ ከረዥም ጊዜ በኋላ ናርዶስን አግኝቻት ስትስቅ ደነገጥኩ

.. ፊት ለፊት ወርቅ ጥርስ ገጭ ብሎ ተተክሏል (በዚህ ዘመን ወርቅ ጥርስ) አንድ ግልፍተኛ ጓደኛ ይዛ በቦክስ ጥርሷን አውልቆት ነበር ‹‹ ወንድ ልጅ እንዴት ሴት ላይ እጁን ያነሳል በማሪያም ›› አለችኝ ቀጠል አድርጋም እንዲህ አለችኝ ‹‹ ነገሩ ነው እንጅ ያው በህግ አፍንጫውን ተይዞ ሃያአራት ካራት የወርቅ ጥርስ አስተከለልኝ ሂሂሂሂሂ ››

በነገራችን ላይ አለምነህ የማወራውን ሁሉ እንደማያምነኝ አውቃለሁ ከትዳር ለመሸሽ የፈጠርኩት ነው የሚመስለው ….

‹‹አሽ ሌላው ይቅር ሊዲያን ለምን ተጣላሃት …ሊዲያ ምን ይጎድላታል እንደዛ አብደህላት ከንፈህላት ስትደውልልህ ጫማህን ሁሉ ረስተህ የምትሮጥላት ልጅ ምናይነት ሰይጣን መሃላችሁ ገባ አብርሽ ››

‹‹ ኧረ ሰይጣን አይደለም ››
‹‹እና ምንድን ነው …ባለፈው አግኝቻት ‹ምንም ክፉ ደግ ሳንነጋገር ራቀኝ › አለችኝ ‹‹ቢያንስ ስልክ <ተጠቅሞ> ምክንያቱን ሊነግረኝ ይገባል ›› አለችኝ ! ተገቢ ነው ? ቢያንስ ቁጭ ብሎ በእኩብሮት በዚህ በዚህ ምክንያት በቃሽኝ አይባልም ? ››

‹‹ እንዴ እኔ የሷ መጠቀም እና ጥቅም ሰለቸኛ ›› እውነቴን ነው …ሊዲያ ጥሩ ልጅ ናት ግን ስታወራ ቃል ስለምትመርጥ ወሬዋ ሁሉ አርቲፊሻል የሆንብኛል …በእርግጥ እርሷ ዘመናዊነት አድርጋ ነው የምታየው እኔ ግን ….. ለምሳሌ ቢሮዋ እሄዳለሁ አይደል ? ተቀመጥ ለማለት ‹‹ ወንበር ውሰድ ›› ትለኛለች ያችን የፈረደባት ((ቴክ ኤ ቸር)) ቀጥታ ወስዳ መሆኑ ነው ! ምነው ሽዋ ! ‹‹አረፍ በል›› ‹‹ተቀመጥ ›› ወላ ተወዘፍ ብባል የሻለኛል

…..ሌላው ያስመረረኝ ቃሏ ‹‹አመሰግናሁ›› በአንድ ደይቃ አስር ጊዜ ‹‹አመሰግናለሁ›› ልትል ትችላለች ምስጋናው አይደለም ችግሩ …የተጠና አርቲፊሻል እንዲሁ አፍ ላይ የከረመ ልማድ መሆኑ ነው ነፍሷ እንደማያመሰግን ያስታውቃል ! ማመስገን ጥሩ ነው ሲባል እኮ ምስጋናን እንደሁለት ነጥብ በየቃሉ መሃል መሰንቀር አይደለም ኤጭጭ ለዛ ያጣ ምስጋና እንዴት ይቸካል !

በተለይ ደግሞ ያስመረረኝ ይሄ ‹መጠቀም › የሚል ቃሏ ‹‹ ካፍቴሪያ ስንጠቀም ፣ሶፍት መጠቀም ፣ስልክህን ልጠቀምበት፣ መፀዳጃ ቤት ልጠቀም …›› ወይም ስልክ ደውየላት ካላነሳች መልሳ ደውላ ‹‹ይቅርታ ሃኒ መፀዳጃ ቤት እየተጠቀምኩ ነበር በዛ ላይ ስልኬ ካርድ ጨርሶ በማሚ ስልክ ነው ተጠቅሜ የደወልኩልህ ›› ትለኛለች ደግሞ ሌላ ቀን ‹‹አብርሽየ ጫት እና መጠጥ አለመጠቀምህ እንዴት እንደሚያስደስተኝ ›› በእርሷ አነጋገር ብስጭቴ ከቀጠለ ወደፊት ሄሮይን ሳይቀር ልጠቀም እችላለሁ ብየ ፈራሁ !

‹‹ሃኒ ከንፈርህ ደረቀ ለምን ቻፕስቲክ አትጠቀምም … ኮምፒውተር ብዙ ሰአት ስለምትጠቀም መነፅር ለአይንህ ብትጠቀም ….. ›› ….ታዲያ እንዴት ነው ይችን ልጅ ለትዳር ‹መጠቀም› የሚቻለው ! መጀመሪያውንም ጠቅሞ ላይጠቅም ቃል ከምታጠረቃቅም ልጅ ጋር ፍቅር መጠቀሜ ተገቢ አልነበረም ! ከዚህ ሁሉ መጠቀም በኋላ የመረረው ጉዳይ ላይ ‹‹ኮንዶም መጠቀም ›› እንዳለብን ስነግራት ደብሯት ነበር

...‹‹አታምነኝም ›› አለችኝ ! ለእኔ የመጨረሻው ስልጣኔ ራስን መጠበቅ ነው ቃል እያጠረቃቀሙ ሂወትን መበተን የዘመነው ስልጣኔ የማይጠቅም መራቀቅ ነው ! ‹‹ኮንዶምን መጠቀም ....አርፎ ከመቀመጥ የበለጠ ብልህነት አይደለም ››

((((ቆይማ እዚጋ የባለጌ ጥያቄ ልጠይቃችሁ (የባለጌ ነው ብያለሁ የማይመቸው ይዝለለው) እ.....(ሂሂሂ አፈርኩ) ምን መሰላችሁ እንትን ....ማለት ሴቶች ውድድ የምታደርጉት ባላችሁ ጋር ወይም በቃ ‹ሃኒያችሁ› ጋር ((እንትን)) ማድረግ ቢያምራችሁ በቃ በጣም ቢያምራችሁ ማለቴ እጅግ በጣም ቢያምራችሁ (ክጃሎት አናታችሁ ላይ ቢወጣ ሂሂ) እና በቃል ‹እናድርግ› ብላችሁ ለመጠየቅ እንዴት ነው የምትገልፁት .....ይገባኛል ሳትናገሩት በፊት አይናችሁ ሲስለመለም ገና ድሮ ‹ሃኒያችሁ › ልብሱን ሊያወልቅ ይችላል ግን በቃ ቃል አውጥታችሁ ብትናገሩት ብለን እናስብ ...የእኔ ጓኛ ሊዲያ ልትል የምትችለውን ስገምት እንዲህ ይመስለኛል ‹‹ሃኒ ወሲብ እንጠቀም ››)))

ጓደኛየ አለምነህ ታዲያ ይሄን ሁሉ ብሶቴን ያው እንደወትሮው ሳያምነኝ ሲሰማኝ ቆየ !ያው ከትዳር ለመሸሽ የምፈጥረው ሰበብ ነው የሚመስለው ! እየሳቀ አስተናጋጇን ጠራና ‹‹ እህቴ እስቲ ‹የተጠቀምንበትን› ሂሳብ አምጭልን›› አላት
አስተናጋጇ መጀመሪያ የታዘዘችን ልጅ ስላለበነረች እንዲህ ስትል ጠየቀችን

‹‹ይቅርታ ምንድን ነው የተጠቀማችሁት ››
‹‹ እኔ የተጠቀምኩት ሻይ ነው ....›› ብሎ የእኔን ሊናገር ሲል ፈጠን ብየ እንዲህ አልኩ
‹‹ እኔ ሁለት ቡና ጠጥቻለሁ !!›› ‹‹ጠጥቻለሁ›› ቃሉ ራሱ እንዴት ደስ ይላል ....

‹‹በል አብርሽ ያለችንን ጊዜ ተጠቅመን እንገናኝ አንጠፋፋ ››
‹‹ እሽ ››
ተሳሰቀን ተለያየን ....እኔም እሽ አበዛሁ መሰል !

እኛ ነው !

(አሌክስ አብርሃም)

አለናችሁ ያሉን ስመው ለመለየት ከንፈር ሲያዘጋጁ
አሉ ከጎናችን በከንፈራቸው ቃል ዘመን የሚዋጁ !
በድቅድቅ ጨለማ ንጋት የሚባጁ
የፈረሰ ስጋን ከፍቅር ችሮታ ከራህሩህ ስጦታ ዳግም የሚያበጁ !

ለርፍ የማይሸነፍ ለክብር የማይተኛ ክንድ የነበራቸው
ትንታግ ያገር ልጆች በችግር ሲረግፉ በራብ ሲታመሙ
ሰርግ ቤት ረግጠው ማቅ ከለበሱት ጋር አብረው የሚከርሙ
አሉ የቀን ሃኪሞች ኑሯቸውን ገድለው ኗሪ የሚያክሙ

ከችግሩ እኩል... ከራባችን እቻ
ያለም አፍ ሲገርፈን በአሸሙር እንቶፈንቶ በስላቅ ዘመቻ
አሉ አብረው የሚያዝኑ ደግ የዘመን ስንቆች እንደናት እንጎቻ !

በዘመነ ቆፈን ብርድ የፈሩ ነፍሶች ቁመው ሲሳቀቁ
ይሞቁናል ብለው የተማፀኗቸው ፀሃዮች ሲጠልቁ
አሉ ከጎናችን በሩህሩህ ክንዳቸው አቅፈው የሚያሞቁ

ሰው መሆን ሲያሳቅቅ እንኳንስ ከሌላው ሃቅ ከራስ ሲጣላ
አማኝ ባመነው ፊት እምነቱን ሲበላ
ሰጭ ተቀባይ ሲሆን የልመና መዳፍ እንዳሸን ሲፈላ
አለ በሃሩር ውስጥ እራሱን ዝግባ አርጎ የሚያስጠልል ጥላ

ምድር ሲኮሸልል በድፍን መንደሩ ከንፈር የሚያረጥብ
ጨዛ አከል ጠብታ ከቃየው ሲጠፋ
የቀን ፊት ጨፍግጎ ቸር ማጀት ሲከፋ
እናት ለሙት ልጇ እርም ታወጣበት አንድ ዘለላ እንባ ካይኖቿ ስታጣ
አለ እድል መሳይ ሰው ራሱን ምንጭ አርጎ ሸወች የሚያጠጣ !!

በድቅድቅ ጨለማ ...አለ የጫት ጀምበር ካድማስ የሚወጣ .....
የጨለመ ነጋ ....የተራበም በላ
የኮሰመነ ነፍስ ጨፈረ በተድላ
አገር ቀን ወጣለት ... የብራ ቀን ነጋ
ደህና ሁን አበሻ ትቀምሰው ካገኘህ ያ ነው ያንተ ዋጋ

የጥጋብ ቀን ሲዋጅ ክፉ ቀን ሲከስም
ሻንጣውን ሸክፎ ሊሰነባበተን ሲዘይረን አለም
የሰው ሰውነቱ ሆድ መሙላት አይደልም

ብሎ አብሮ የቆመ ለመጭ ቀናችን

አለ እኛን የሆነ ነበር መሃላችን !

ነበር በክፉ ቀን ነበር በደስታችን

እንዳ,ርባ ቀን እድል ድንገት ያገኘነው

አብሮን ቀን የገፋ ይሄ ሰው ‹‹እኛ›› ነው !!

እናቶቻችን ማጨስ ያቁሙ !!
(አሌክስ አብርሃም)

እናቶቻችን በአንድ ሰአት 400 ሲጋራ ያጨሳሉ ! በዚህም ኢትዮጲያ በአመት ሁለት ሽ እናቶችን በሞት ትነጠቃለች ! እንዴት ማለት ጥሩ ! በእንጨት ምድጃ እንጀራ የሚጋግሩ እናቶች በአንድ ሰዓት ውስጥ ብቻ ወደውስጣቸው የሚገባው ጭስ የ 400 ሲጋራወችን ጭስ ያህል ነው ! ይታያችሁ ‹‹የእናት እንጀራ ምናምን›› እያልን ! ዘፈን ስናሳምር እናቶቻችን ምን ያህል ስቃይና የጤና ችግር ውስጥ እንደኖሩ አስቡት ! ያውም እድሜ ልካቸውን !

እንደው አንዲት የገጠር እናት(ኧረ የከተማም) በቀን ስንት ሰአት ምድጃ ላይ ታሳልፋለች ...በእውነት አሳዛኝ ዜና ነው ! እና ለእናቶቻችን የቻልነውን ያህል እያደረግን ማጨስ ብናስቆማቸውስ ...ረዥም እድሜ ለእናቶቻችን ! (ጥናቱን ወርልድ ቪዥን ኢትዮጲያ ነው ያስጠናው ዜናውን ሸገር ሬዲዮ አሰማን)

ሌላ ዜና ...

ቦኮሃራም የተባለው የሽብር ቡድን ከዚህ በፊት አፍኖ ከወሰዳቸው ሁለት መቶ ምናምን ሴቶች በተጨማሪ ዛሬ ደግሞ 20 ተጨማሪ ሴት ልጆችን ከሰሜናዊ ናይጀሪያ አካባቢ ጠልፎ ወሰደ! (ለዝርዝሩ አልጀዚራ ላይ ፈልጋችሁ አንብቡ ! ድፍኑንም ዝርዝሩንም ለምን ከኔ ትጠብቃላችሁ እንዴዴዴዴ እኔ ስንት ስራ እያለኝ ዝርዝር ፍለጋ ልንከራተት እንዴ ..አሁንስ በዛ ለእናተ ብቻ በመፃፍ ቁጭ ብየ ስውል እኔስ ከመጠለፍ ምኑን ተሻልኩት ...የኔ ቦኮሃራሞች በሉ ተፋቱኝ)

የተንጨባረረ ሂወት በፍቅር ሚዶ ሲበጠር
(አሌክስ አብርሃም)

‹‹የኔ ጌታ !›› አለች ሚስት ባሏን በሚያማምሩ አይኖቿ እያየችው
‹‹ወይየ የኔ ማር›› አላት ድምፁ ውስጥ ቃል የለበሰ ፍቅር አለ !
‹‹ቆንጆ ባለማያዣ ማበጠሪያ ብትገዛልኝ ደስ ይለኝ ነበረ ፀጉሬ ተነጫጨብኝኮ አየሽው ? ›› አለች ለምትወደው ባሏ ሳይበጠር እንኳን ወርዶ ጀርባዋ ላይ የተነሰነሰ ውብ ፀጉሯን እያሳየችው ...እውነትም ቅባት ነገር ሽው ተደርጎ በጠር በጠር መደረግ አምሮታል ፀጉሯ ...ተጎሳቁሏል ! ይሁንና ማበጠሪያም ከባድ እቃ ሁኖ በቤታቸው አልነበረም !

ባልና ሚስት ናቸው ! አገር ምድሩ ፍቅራቸውን ያውቃል ....ገና ከድሮ ከልጅነታቸው ጀምሮ ‹‹ውይ የነሱ ፍቅር ካይን ያውጣቸው ›› የሚባሉ አይነት ! የፍቅር ማማወች ! እርሷ ያያት የሚመኛት ውብ ነች ከኋላዋ ሽ ከፊቷ መቶ ወንድ የሚሰግድላት አይነት ! ‹‹ከምን ፈጠራት›› ይላታል አገሬው ! እርሱም ቢሆን ይሄ ቀረህ የማይባል ወጣት ነው !

እንግዲህ አገጣጠማቸውና አገር ምድሩን ጉድ ባስባለ ፍቅር ወደቁ ....ተጋቡም !! ታዲያ ምንዋጋ አለው ፍቅራቸውን የሚክል ግዙፍ ድህነት ቤታቸው ውስጥ እንደትልቅ ቋጥኝ ተደላድሎ ቁጭ አለ !ቢገፉት የማይገፉ ጥቁር ቋጥኝ ባለፉ ባገደሙ ቁጥር ስሜትን የሚገጭ አብሮነትን ሊያደቅ ቢወድቁበት ቢወድቅባቸው እጣ ፋንታቸውን መድቀቅ ሊያደርግ ድህነት ይሉት ድንጋይ በቤታቸው ተጎለተ ! በልተው ከሚያድሩበት ቀን ያማቸውን የሚያድሩበት ይበዛል ! ያጡ የነጡ ድሆች ...ቆንጆ ድሆች ! ፍቅር ብቻ ሳይሆን ድህነትም ያፈቀራቸው ድሆች ! ይታያችሁ ማበጠሪያ እንኳን መግዣ ያጡ ደሆች ! ‹‹እንደነሱ አይነት ፍቅር የትም የለም ›› የሚለው ጎረቤት በተጨማሪ እንዲህ ይላል ‹‹ እንደነሱ አይነት ድህነት የትም የለም ››

እና ሚስት ‹‹ማበጠሪያ ግዛልኝ›› አለችው ባሏን ! ላይንና ለወዳጅ ትንሽ ይበቀዋል ባል በሚስቱ ጥያቄ ከፋው ‹‹ እንዴት ኪሴ ባዶ መሆኑን እያወቅሽ እንዲህ ትይኛለሽ ...እስቲ የእጇን ሰአት ተመልከችው መስተዋቱ ተሰንጥቆ ሰው ፊት እንኳን ሰዓት ማየት እያፈርኩ ቢኖረኝ ይችን መስተዋት አላስቀይርም ...›› ሲል ተነጫነጨ ሰአቱ በጣም የሚወዳት እናቱ ስጦታ ነበር

ሚስት በበኩሏ ‹‹ ከእኔ ፀጉር የእጅ ሰዓትህ በልጦብህ እንዲህ ትናገረኛለህ ... ? እኔ ላንተ እንዲህ ነበርኩ ? ›› ብላ እንባዋ ቀደማት ....ባል በብስጭት ጥሏት ከቤት ወጣ ትዳሬን ብሎ እንጅ እዚህና እዚያ እንደጓደኞቹ ቢዛለል ‹‹ጌታየ›› ብለው ወርቅ የሚያለብሱት በፍቅሩ እንግብግብ የሚሉለት ሃብታም ቆንጆ ሴቶች ሞልተዋል !! ሚስትም ብዙ አልቆየችም ተነስታ ወጣች ! ትዳሬን ብላ እንጅ ወጣ ብትል እንኳን ማበጠሪያ ‹‹እመቤቴ›› ብለው ...እግሯን ስመው ሙሉ ፀጉር ቤት የሚከፍቱላት ወንዶች በከተማው እየተርመሰመሱ ሞልተዋል !

ወደአመሻሹ ላይ ባል ወደቤቱ እየተጣደፈ ሲመለስ ግን በቀኑ ብስጭት አልነበረም እንደውም ፊቱ በፈገግታ ተሞልቶ በጉጉት ነበር እንጅ .... የእናቱን ውድ ስጦታ የሆነችውን ሰባራ ሰዓቱን ሽጦ ለሚወዳት ሚስቱ ቆንጆ የገዛውን ማበጠሪያ በኪሱ ይዞ ነበር

...እቤት ሲገባ ግን ባየው ነገር ደነገጠ ....ማመን አልቻለም ....ሚስት ያንን ጥቁር ፏፏቴ የመሰለ ውብ ፀጉሯን ሙሉ ለሙሉ ተቆረጣ ወንድ መስላ ተቀምጣለች .... በእጇ ግን ውድ የሆነ ባለወርቅ ማሰሪያ የወንድ ሰአት ይዛ በጉጉት ባሏን እየጠበቀችው ነበር ...ፀጉሯን ሽጣ ለምትወደው ባሏ የገዛችው ነው ! ሁለቱም በዝምታ እንባቸው በጉንጮቻቸው ላይ ፈሰሰ ....አዲሱ ሰአት... ቲክ ቲክ ቲክ ቲክ ይላል . . . ይህም መራር እውነት እንደሚያልፍ ሊነግራቸው የፈለገ ይመስላል !!

የእኔ አይደለችም ተርጉሚያት ነው !!

ልማደኛ ወ ሽ ካ ታ... !!
(አማርኛችን አንዳንዴ ዱላ ናት መቸስ)
(አሌክስ አብርሃም)

የሁለተኛ ክፍል ተማሪዎች እንደነበርን ስለየብስ መጓጓዣወች ስንማር ቲቸር ታዴ
‹‹ እስቲ ከዘመናዊ የየብስ መጓጓዣወች የምታውቁትን ንገሩኝ ›› አሉን እኛም በየአፋችን ተንጫጫን
‹‹ ባይስክል ››
‹‹ጎበዝ›› ብለው ያደንቃሉ ቲቸር
‹‹ መኪና ››
በጣም ጎበዝ
‹‹ግልባጭ መኪና ››
‹‹አይ! መኪና ያው መኪና ነው... ሙከራህ ግን ጥሩ ነው ››
‹‹ሞተር ሳይክል ››
‹‹ትክክል ››

ሁሉላችንም የምናውቀውን ዘርዝረን ክፍሉ ፀጥ እንዳለ ‹‹ሌላ የለም ? ›› እያሉ ቲቸር ሲጠይቁ .... አንዳርጌ እጁን አወጣ
‹‹እሽ አንዳርጌ ››
‹‹ባቡር ›› ሲል መለሰ
‹‹እጅግ በጣም ጎበዝ አጨብጭቡለት›› አሉ ቲቸር ከፍ ባለ አድናቆት ጀጀጀጀጀጀጀጀጀጀጀጀ...ግን ቀናን ! እያጨበጨብን ቀናን ! አንደኛ አንዳርጌ ባቡር የሚባለውን ነገር እንዴት አወቀው ? ...እኛ ስሙንም ሰምተነው አናውቅም ...ሁለተኛ ‹‹ እጅግ በጣም ጎበዝ ›› መባሉና ከእኛ መብለጡ አወራጨን ! ‹‹ ባቡር ምንድን ነው ?›› እየተባባልን ብንጠያየቅም ከመካከላችን ማንም የሚያውቅ አልነበረም ...እና አንዳርጌ ከየት አመጣው ? ..... በቃ በእረፍት ሰአት እንጠይቀዋለን ....

የእረፍት ሰአት ስንጠብቀው ደረሰ ‹‹ ስማ አንዳርጌ ባቡር ምንድን ነው ? ››
‹‹ እስከዛሬ ባቡር አታውቁም ? ›› ሲል ዝቅ አድርጎ እየተመለከተን እኛኑ መልሶ ጠየቀን የባሰ ተበሳጨን !

‹‹ አታካብዳ እኛ ስንት ነገር ስናስኮርጅህ አነጅበንበሃል ....?›› እውነታችንን ነው አንዳርጌን እኔ ራሱ ብዙ ቀን የቤት ስራ ሳይሰራ መጥቶ አስገልብጨዋለሁ ! ቁጣችንን ከቁብ ሳይቆጥር ኮራ ብሎ እንዲህ ሲል ስለ ‹‹ባቡር›› ተረከልን ...

‹‹ ባቡር ረዥም መቶ ጎማ ያለው አውቶብስ የሚመስል ነገር ነው ...ታዲያ በጣም ረዥም ነው ...ከዚህ ... እእእ .....እዛ ሶስተኛ ዲ ክፍል የሚደርስ ›› ሶስተኛ ዲ ክፍል ከእኛ በጣም ሩቅ ነው ቢያንስ አንድ የኳስ ሜዳ የሚሆን ርቀት ተገረምን ! ....ለካ ቲቸር ‹‹እጅግ በጣም ጎበዝ ›› ያሉት ረዥም ነገር ስለጠራ ነው ብለንም

አሰብን ! (በቁመት ሆነ እንዴ ጭብጨባ ?)

ቀጠለ አንዳርጌ ‹‹ባቡር ውስጡ የእግር ኳስ ሜዳ ፣የባስኬትቦል ሜዳ እና የመዋኛ ገንዳ ሁሉ አለው ….በጣም ያምራል አንዴ ከገባችሁ ውጡ ውጡ አይልም ››
‹‹ እና አንተ እንዴት አወክ …የት አየኸው ? ›› በየአፋችን ጠየቅነው ለማየት በቋመጠች የልጅ ጉጉት !አንዳርጌ ኮራ ብሎ እንዲህ አለን

‹‹አባቴ የባቡር ሹፌር ነው … ሁልጊዜ ምሳ ሰአት ላይ ባቡሩን እየነዳ ሰፈር ያመጣውና ያቆመዋል …..ያው ምሳ በልቶ እስከሚጨርስ እኔ ሰፈር ውስጥ እንደልቤ እየነዳሁ በባቡሩ እጫወትበታለሁ … ብዙ አልነዳውም በላይ በወፍጮ ቤቱ ጋ አድርጌ ቤተ ክርስቲያኑ ጋ ስደርስ አቆመውና ወርጀ እሳለማለሁ ከዛ በቃ ወደቤት እመልስዋለሁ ……እንደውም አንድ ቀን ቲቸር ስነዳው አይተው ‹አንተ ተጠንቅቀህ ንዳ አትንቀልቀል › ብለውኛል ! ›› ሁላችንም ቀናን ! ባቡር ነጭ ይሁን ጥቁር አናውቅም ግን ጓደኞችንን አምነነው ነበር ! የኛም አባቶች ለምሳ እቤት ሲመጡ ባቡር እየነዱ እንዲመጡ ተመኝተናል !

ሌላ ቀን ደግሞ ይሄው አንዳርጌ ስለቤት ሰራተኛ ሲወራ እንዲህ ብሎ አስደመመን ‹‹ እኛ ቤት ሰራተኛ የለም ስራውን የሚሰራው ማሽን ነው ..››
‹‹የምን ማሽን ? ›› ((ከባቡሩ በኋላ የፈለገውን ቢያወራ እናምነዋለን !))
‹‹ማሽን ነዋ …ማሽን አታውቁም ? አባቴ ከውጭ አገር ገዝቶ አመጣውና ቤት ውስጥ ግድግዳው ጋር አስጠግቶ አቆመው ….ከዛ ሁሉንም ነገር ስታዙት ያቀርብላችኋል ….. በቃ ለምሳሌ ልክ ማሽኑ እንደመጣ አባየ ‹ስ› ሲለው ገና ስኳር ዝቅ ዝቅ ዝቅ እያደረገ አወጣ…. ‹ዳ› ስትሉት ዳቦ ዱብ ዱብ ዱብ ያደርጋል ያውም ትኩስ ዳቦ …እ ስትሉት እንጀራ እጥፍ እጥፍ አድርጎ ቁጭ ነው የሚያደርገው ….በቃ ››

አፋችንን ከፍተን ስናዳምጠው ፊዮሪ የምትባል ብልጣብልጥ ጓደኞችን አንዳርጌን ያልታሰበ ጥያቄ ጠየቀችው ‹‹ አባትህ ‹ስ› ሲሉት ለምን ስጋ አላወጣም ማሽኑ ?›› አንዳርጌ ምንም ሳይደናገጥ አሰብ አድርጎ እንዲህ ሲል መለሰላት
‹‹ ዶም ነበር !! ››

ልጅነት ሽው ብላ አለፈች ……እና ጎረምሳ ሆንን የማርበት ‹ሃይ ስኩል ውስጥ ደግሞ አዚዛ የምትባል ቆንጆየ ልጅ ነበረች የምኞታችን መጀመሪያ …..እናም አብራው ያደገችው የአንዳርጌ የውሽት ማሽን ‹አ› ሲላት አዚዛን ዱብ አደረገችለት !! እንዲህ አለን …በናትህ ይች አዚዛ እንዲህ ስታያት ኮስታራ ትመስላለች በስማም ትላን ሰፈር ድረስ መጥታ አልተንጣጣችብኝም …..››
‹‹አዚዛ ተንጣጣች …›› ተገርመን ጠየቅነው አዚዛ እንኳን መንጣጣት ዝምታዋ ክላስ ውስጥም ስንት ጣጣ ያመጣባት ልጅ ነች !

‹‹አፈቀርኩህ ምናምን እያለች ነዋ …ከዛ ክላሴ ውስጥ ፋዘር ሳያየኝ አስገባኋት (ቤታቸው አንዲት ክፍል ናት ስናውቃት የምን ክላስ ነው) …በስማም አንተ እንዲህ ስታያት አንገት ደፊ .‹‹ ኪስ ›› ላይ…. በቃ ነፍስህን ነው የምታስትህ በዛ ላይ የሰውነቷ ልስላሴ ….›› አራጌ ሲያወራን ጆሮ ብቻ ሆንን የአዚዛ ሰውነት ልስላሴ በቃ ተሰማን …በዛ ላይ ቀይ ከንፈሯ ታሰበን (ምን ምን ይል ይሆን) የጎረምሳ ጅስማችን በአንዳርጌ ወሬ ብው ብሎ እሳት ለበሰ እሳት ጎረሰ ….ምኞት አናታችን ላይ ወጣ !! አዚዛን እኮ እንኳን መሳም ….እኛ ክላስ ስለሆነች ብቻ የሌላ ክላስ ተማሪወች እድለኛ እንደሆንን ነው የሚያስቡት ! በእርግጥ ያችን የመሰለች ቆንጆ ሙሉ ቀን ያለገደብ እስክንጠግብ ማየት እድለኝነት ነበር ! በቆፈናም ማለዳ ብቅ የምትል ጣፋጭ የጧት ፀሃይ ነበረች አዚዛ !

በኋላ ይሄ ወሬ አዚዛ ጋር ደረሰ !! ቀጥ ብላ ርእሰ መምህሩ ቢሮ ሂዳ ምን እንዳለቻቸው እንጃ አንዳርጌን ጠሩና እንደቅሪላ በዱላ አልፍተው ላኩት !ምን እሱ ብቻ ጓደኞቹን ሁሉ ተራ በተራ እየጠሩ ቀጠቀጡን እንጅ …. እኛ ውሽት መሆኑ ገብቶን እንዳናሳፍረው ዝም ብንልም ዱላ የጠገበ ጀርባውን እያሻሸ እንዲህ አለን ‹‹ እኔ

ተሳስመን ብቻ እንለያይ ነው ያልኳት እራሷ ገፋፍታ ላደረግነው ነገር ….›› ብትንትናችን ወጣ …ይሄ ሰው ሊያስጨርሰን ነው ! ለመሳሳም ይን ያህል የተወገርን ጭራሽ ነገር ይመዛል እንዴ …ርእሰ መምህራችን ጋሽ ዘነበ ይሄን ቢሰሙ የዘበኛውን ጠመንጃ ተቀብለው ነበር ተማሪ ፊት የሚረሽኑን !(ቀይ ሽብር እንደውም አዚዛ ቀይ ናት) የሚገርመው ግን እየሸሸንም አመነው ! መቸም በዛ ጉድ ዱላ መሃል ሰው ይዋሻል ተብሎ አይታሰብም ! በዛ ላይ ባናገኛትም የምንመኛትን ልጅ እንደሰው የምትዳሰስ የምትገኝ አድርጎ የሚያወራ ሰው መኖሩ በራሱ የሆነ ተስፋ ሰጭ ነገር አለው !

አንዳርጌ የማይፈወስ የውሸት ችግር ነበረበት …አብረን ያየነውን ነገር ቀይሮ ያወራል ! ያልሆነውን ነገር እንደሆነ አድርጎ ይነግረናል ! እንደውም ህፃን እንደነበርን ‹ስታይል › መስሎን በመሃበር ይሄን ውሸት እንወሸክተው ጀምረን ነበር ! ‹‹ፋዘር ፕሌን አብራሪ ነው›› አለን ያሬድ…. አባቱ ጋሽ ላቀው የታዋቂው ነጭ ሳር ዳቦ ቤት ዳቦ ጋጋሪ መሆናቸውን ሁላችን እናውቃለን እንደውም ትኩስ ዳቦ በሰፋፊ ኪሶቻቸው እያመጡ ከልጆቻቸው ሳይለዩ አብልተውናል …ስታይል ከሆነ ብለን ‹‹ፓይለት›› ሲሆኑ ዝም አልን ! ዳቦው እንዳይቀር እየሰጋን መቸስ ፓይለትም ባዶ እጁን አይመጣም ይባላል ! ይሁና !

‹‹ ወንድሜ አየር ወለድ ነበር ከአውሮፕላን ላይ ሲዘል ‹ፓራ ሹቱ › ተበጥሶበት ወድቆ ነው ሁለት እግሩ እንዲህ የሆነው አለን ታዲዮስ በበኩሉ ….የታዲዮስ ወንድም ያው ሁላችንም እንደምናውቀው በፖሊዮ(የልጅነት ልምሻ) ምክንያትነው እግሮቹ እንደዛ ሁነው በተሸከርካሪ ወንበር የሚሄደው ! እኔም በጓደኞቹ በመበለጤ በጣም ተበሳጨሁና በቃ ሌሊት ሳስብ አድሬ አሪፍ ቀደዳ መጣልኝ

‹‹ እናቴ አሴ አሁን ስታያት ያልተማረች ምናምን ትመስላለች አይደል ? ….ግን የሶስተኛ አመት የዩኒቨርስቲ ተማሪ ነበረች …..››
‹‹ኧረ አቡቹ አትፎግር ››
‹‹ማሪያምን! ….. መሬት ላራሹ ምናምን እያለች ንጉሱን ስታበሳጫቸው ከግቢ አባረዋት ነው ›› ቀደድኩት ! ብሩክ ታዲያ (አብረን የምንማር የሰፈሬ ልጅ) አንድቀን መፅሃፍ ሊዋስ እቤት መጥቶ ነገር አበላሽ
‹‹እትየ አሰለፈች ››
‹‹ ወይየ ብሩኬ ››
‹‹ ዩኒቨርስቲ እንደነበርሽ መሬት ላራሹ ምናምን ስትይ ግን ወታደሮቹ አልተኮሱብሽም ›› ብሎ አይጠይቃትም ? ተበላሁ ! ከዛ አካባቢ ብርርረርርርር ብየ ጠፋሁ ….ስመለስ ግን አሴ እሳት ለብሳ እሳት ጎርሳ ጠበቀችኝ !

‹‹ አንተ በምን ብትንቀኝ ነው እንዲህ የዩኒበርስቲ ተማሪ የምታደርገኝ ? እኔ መች ስራ አጣሁ …ደርግም መሰረተ ትምርት ብሎ ሴቱን ሁሉ ሲነዳው እኔ አሰለፈች አንድ ቀን ተማር ቤት ረግጬ አላውቅም ! … ሁለተኛ እንዲች አይነት ነገር ከአፍህ ብትወጣ ውርድ ከራሴ ….ሆሆ ለራሴ አብሲቱ አልቦካልሽ ብሎኝ ተቸግሪያለሁ ጨራሽ ዩኒበርስ ወስዶ አበሳየን ያሳየኛል …›› እያለች ወደጓዳ ገባች …

ያው አደግን ከሰፈር ልጆች ጋር የሂወት ጉዳይ ቶሎ ቶሎ አያገናኝንም …..በቅርቡ ታዲያ አንዳርጌን ድንገት መንገድ ላይ ታክሲ ከሚጠበቅ ሰልፈኛ መሃል አገኘሁትና ገና በወጉ ሰላምታ እንኳን ሳንለዋወጥ ‹‹ ምን እዚህ ሹፌሬ ጋ ስደውል ኔትወርክ አስቸግሮኝ ይሄው ተሰልፌ ታክሲ እየጠበኩ ›› አለኝ ! በቆምንበት አጭር ቅፅበትን ስላስጀመረው ህንፃና በቅርብ ከውጭ ስላስመጣት መኪና አተተልኝ ! በስኬቱ ደስ አለኝ ! (በኋላ እንዳወኩት ግን አንዳርጌ እንኳን በሹፌር የሚነዳ መኪናና ህንፃ ቀርቶ ለእለት ጉርሱ እና ሱሱ እናቱን አንቆ ብር እንደሚቀበል ከሰፈር ልጆች ሰማሁ)

እንግዲህ አሁን እኮ ነው የምሰማው ….ውሸትም በሽታ እንደሆነ !! ካወኩ በኋላ እነደው እንዴት አይነት በሽታ ይሆን የሆነ እንደምች የሚያጣፍር ይሆን ወይስ እንደመጋኛ ሰቅሶ የሚይዝ ? ብየ ሳፈላልግ የፈረደበት ኢንሳይክሎፒዲያ አንዲህ ሳያቋርጡ ውሸት የሚያወሩ መዋሸት ሱስ የሆነባቸው ሰወችን ሰወች አመል ሲተነትነው …Pathiogical Liar …..a person who tells lies frequently ….እያለ ይቀጥላል ! ያው ነገሮችን ወደአማርኛ ለመቀየር የኔ መዝገበ ቃላት እናቴ አሴ ነች !

‹‹አሴ ይሄውልሽ ከመሬት ተነስተው በተደጋጋሚ የሚዋሹ ሰወችን ፈረንጆቹ ትንሽ ህመም ወረፍ ያደረጋቸው ናቸው ይሏቸዋል የጤና አይደለም ››
‹‹ኤዲያ አመል ነው እንጅ ምን በሽታ ነው ይሄ ›› አለች
‹‹ እሱማ ነው ግን …ተንከባከቧቸው …ውሸታም ቀዳዳ ቱልቱላ ምናምን አትበሏቸው አለ አይደል ለስለስ አድርጓችሁ ጥሯቸው የስነልቦና ቀውስ ነው ይላሉ ፈረንጆቹ ›› አልኳት

‹‹ አሃ ምን ብለን እናለስልሰው ? ››
‹‹ በቃ መሃቀቅ የተሳናቸው (መሃቀቅ ሃቅ ማውራት ማለት ነው ሂሂ) …እእእ ትንሽ ከእውነት ወጣ የሚሉ ….ወይም በአንፃራዊነት ውሸታቸው በርከት የሚል …. …››
‹‹ ኤዲያ የምን ስም ማሽሞንሞን ነው እቴ ….ወሽካታ ወይ ቱልቱላ ማለት ነው እንጅ ›› አለች አሴ አቋርጣኝ
‹‹ኧረ አይባልም ለስለስ አድርጊው አሴ ››
‹‹ ይሄው ይዘናል ማለስለስ እኛ እየሻከርን ….ይሄው ይዘናል ማስታመም እኛ እየታመምን … እንናገርስ ብንል መች ያናግሩናል ሲወሸክቱ ዝም ብለን ጉዱን ማየት እንጅ ….›› አለችና ወደቴሌፊዥኑ በአገጯ ጠቆመችኝ …..ዜና ላይ ነበር አንባቢው እንዲህ ይላል . . .

‹‹ ለጉብኝት የመጡት አሜሪካዊ ባልና ሚስቶች ዊሊያምና ካትሪና እንዳሉት ከሆነ ህዝቡ ባስገራሚ ሁኔታ ኦሮው ተቀይሯልልልልልል….. በቅርብ አመታትም አገሪቱ ወደገነትነት ትቀየራለች ብለዋል ›› አሴ ከንፈሯን መጣ … ‹‹ፈረንጆቹም ተለክፈዋል በመወሸክት በቴሌቢዥን ሌላ ባቡቹ ኮመፒተር ሌላ …ቀልማዶች ›› እያለች ወደጓዳዋ ገባች !

እኔም ወደጎግል ….ጎግል እንዲህ ቀጥሏል ….
‹‹ልማደኛ ወሽካታ›› refers to a liar that is compulsive or impulsive, lies on ((regular basis)) ‹‹ አሁን ከምሽቱ ሁለት ሰአት ሁኗል እንዋሻለን›› እንደማለት …and is unable to control their lying…..ስጥ እንግዲህ ካለከልካይ ማለት እኮ ነው ….ራስህን ሃይ ካላልክ ማን ሃይ ሊለህ …በቃ ከቁጥጥርህ ውጭ ሁኖ ውሸት አናትህ ላይ ሲወጣ እንደወባ …. !!

አንዲት ቃል …2
(አሌክስ አብርሃም)

ከአሜሪካ ፡- ጆርጅ ቡሽ ልጃቸውም ትንሹ ቡሽ ፣ ክሊንተን ፣ ኦባማ ፣ሚሸል ኦባማ ፣ ቢዮንሴ ፣ሪሃና ፣ ማይክል ጃክሰን (ነብሱን ይማር) ኦፕራ ወዘተ …ከአውሮፓ ሁሉም የእግር ኳስ ተጨዋቾችና አሰልጣኞች እንዲሁም ደጋፊወች …..ከአፍሪካ ደግሞ ፡ - ሙጋቤ ፣ ማንዴላ (ነብሳቸውን ማርርርርርር ያድርጋቸው) እእእ ማነው ደግሞ ይሄ ትላንትና በወታደራዊ እርምጃ ተንደርድሮ ፕሬዝዳንታዊ ወንበር ላይ ጉብ ያለው የግብፁ ሰውየ … አዎ እሱ ! እና የአፍሪካ ህበረት የወቅቱ ሊቀመንበር ኧረ ብዙ መሪወች …ከኢትዮጲያ ደግሞ ፡ - ስማቸውን የማላውቃቸው ብዙ ሰወች ተሰልፈው ታክሲ እየጠበቁ ሲያወሩ … ካፊ እና ሆቴሎች ውስጥ ተቀምጠው ሻይ ቡና ሲጠጡ …

ይሄ ሁሉ ቱባ ቱባ ባለስልጣን አርቲስትና ህዝብ ((አንዲት ቃል)) ሲናገር በተለያየ ጊዜ ሰምቻለሁ ! ግን ሁሉም ቃሉ አፋቸው ላይ አያምርባቸውም ! በዚች አለም ቃሉ እጅጅጅጅጅጅግ በጣም የሚያምርባት (ምነው ሌላ ቃል ባልተፈጠረ እሰክል ድረስ)አንዲት ሴት ብቻ ናት የእኔ ፍቅረኛ ሊያ !! እውነቴን እኮ ነው ሊያ ያንን ቃል ስትናገረው .....በስማም !!

ሊያ አልፎ አልፎ የምትናገራት ግን የእኔ የሁልጊዜ ትዝታ የሆነች ያች አንዲት ቃል ሊያን አፍቅሬ እንድቀር አድርጋኛለች ! ውይ ያች ቃል ሊያ ላይ እንዴት እንደምታምር ....አቤት ያች ቃል ሊያ ከንፈር ላይ እንዴት ስእል እንደምትሆን ....ሙዚቃ እንደምትሆን ጃዝ ..ዶክተር ሙላቱ አስታጥቀቁ አቀናብሮ ሊያየ ከንፈር ላይ ያስቀመጠልኝ ነው የሚመስለኝ ! ይሄው ሃያ ሰባት አመት ሞላኝ እንደሊያ ያች ቃል የምታምርበት ሰው አጋጥሞኝ አያውቅም !! ወይኔ ያች ቃል !!

በነገራችን ላይ ሊያ ያችን ቃል ለሌላ ወንድ እንዳትናገራት አስምያት ነበር ! ቀልድ እንዳይመስላችሁ በምትወደው ታናሽ ወድሟ ስም ነው የማለችልኝ ...
‹‹ቤቢየ ይሙት ለማንም ይችን ቃል አልናገርም ››
‹‹አይ የምን ቤቢየ ነው በስሙ ማይልኝ ››

‹‹ ብሩክየ ይሙት አሌካ ...ለማንም ያችን ቃል አልናገራትም የግድ እንኳን ቢያስፈልገኝ ሌላ አማራጭ ምናምን እጠቀማለሁ ›› ከምር ! ልክ እንደዚህ ምላልኝ ቃሉ የእኔ ብቻ ሆነ ! እስቲ ፍቅረኞችሁ ለእናተ ብቻ የሚናገረው ቃል አለ ? ሁልጊዜ ወደስጦታ መሸጫ ሱቅ ከመሮጥ እንዲህ ቃል የምትሰጥ ፍቅረኛ ማግኘት መታደል ነው ! እና ልክ እንደጋብቻ ቀለበት ከሊያ ለእኔ ብቻ የሚነገር ቃል አለኝ ! ...ደግሞ ማስማሌ ልክ ነበር እኔን ጉድ የሰራኝ ቃል ሌላውንስ ምን እንደሚያደርገው ምን አውቃለሁ ... ? መጠንቀቅ ጥሩ ነው ! በእርግጥ ጓደኛየ መስፍን ‹‹ያው እንደማንኛውም ሰው ተራ ንግግር ነው ›› ብሎ ቃሉን ቢያናንቀውም ቆይቶ የገባኝ ነገር መስፍን የሊያን እንቁ የሆነ ቃል የሰማው በጆሮው ሲሆን እኔ ግን ሊያን የምሰማት በአይኔ ነበር ! አንድ ቀን ታዲያ መስፍንን ‹‹እስቲ ግዴለህም ስትናገር እያት›› አልኩት አያት
‹‹እሽ ምን ታየህ ›› አልኩት በኩራት

‹‹ ያው ከኋላዋ ያለውን አለም በግዝፈቷ የከለለች ልጅ ናታ ›› ብሎኝ በስልክ ወደሚጫወተው ‹‹ጌም ›› አቀረቀረ ! ድሮውንስ ጌም ያደነዘዘው ሰው ምን ይታየዋል ! ተበሳጨሁ ! እና ለዚህ ሁሉ ፍቅር ያበቃኝን ጦሰኛ ቃል ከላይ ነገርኳችሁ አይደል ? አ ል ነ ገ ር ከ ን ም ? .....እንዴዴዴዴዴዴዴ ! እና እስካሁን ቃሉን ሳልነግራችሁ ነው ይሄን ሁሉ የማወራው ...? (አቤት የሰው ልጅ ትእግስት ከምር አሳዘናችሁኝ ! ይሄን ሁሉ ነገር ሳወራ ካሁን አሁን ቃሉን ተናገረ ብላችሁ ላፕቶፓችሁ እና ስልካችሁ ላይ ቁልጭ ቁልጭ ስትሉ ታየኝ ? ለነገሩ ምን ላድርግ እኔም እኮ ሊያየ ስታወራ ካሁን ካሁን ያንን ቃል ተናገረችው እያልኩ እንዲህ እንደናተ ነበር አፍ አፏን እያየሁ የማፈጠው)

ለነገሩ ቃል አይደለም ቃላት ናቸው ያው ግን ከመኖር ብዛት አንድ ቃል ሁነዋል ...ምን መሰላችሁ ቃሉ ...‹‹ ኦ, ራ ይ ት ›› በቃ ይሄን ሁሉ አመት ከሊያ አፍ እንደጫጨት ስለቅመው የነበረው ቃል ...የፍቅሯ እስረኛ ያደረገኝ ቃል ኦ ራ ይ ት ነው ! ኦራይት የኔ ሙዚቃ... የኔ ትዝታ ባቲ ....አንችሆየ መዲና ዘለሰኛ ....ኦራይት የእኔ ስእል ... ኦራይት የእኔ ፊደል የለበሰ ፍቅር.... ኦራይት የኔ የኔ ሊያ ቃል !

ኦ ራ ይ ት .... ብትንትኔን እንዳወጣው በታትኘ እነግራችኋለሁ (እናተ ናችሁ ያላችሁኝ ለሌላ ለማን እናገራለሁ ታዲያ) የምናፈቅረው ሰው የምንወደው ሰው እኮ ውስጣችን የሚተዋቸው ብዙ ጭረቶች ብዙ መስመሮች አሉ ...ለእኛ ብቻ የሚገቡን ተቀላቅለው ትልቅ ምስል የሚከስቱ ግን በየትኛውም ቋንቋ ለሌሎች ልናስረዳቸው የማንችላቸው የእኛ የግላችን የውስጣችን ህመሞች ሁነው የሚቀሩ ስንት ጉድ ትዝታወች አሉ ...የወደድነውን ልጅ ‹‹በደፈናው ጥሩ ልጅ ነበር›› እንላለን ...ለእኛ ግን በአይምሯችን ውስጥ ጥሩነቱን የገነቡብን አነጋገሩ ፣ድምፁ ውስጥ ያለው ዜማ ከአይኖቹ የሚፈናጠቁት የደግነት ብርሃኖች ሁሉ ይታዩናል

....ለሰው ግን ምን ተብሎ ይወራል ....

‹‹ አፈቅራታለሁ ›› ስንል የምናፈቅራት ልጅ ጠረን ውስጣችን አለ ...የእጇ ልስላሴ ይሰማናል ...ተቀጣትረን ከዛጋ ስትመጣ እኛ ጋ እስክተደርስ ያለው ስሜት አረማመዷ ስታየን የፊቷ ገፅ ላይ የሚታየን ስሜት ደርሳ ስንሳሳም እቅፍ ስናደርጋት ሰውነታችን የሚሰማው ንዝርት ደስታ እረፍት ... ውስጣችን አለ..... ስሜቱ ስታቅፏት ከፀጉር ቤት መጥታ ይሆናል የሆነ የእርሷ ብቻ የፀጉር ሽታ አለ ...ጋውያ ነካክቶ ያገነነው ! የፀጉሯን ቁጥር ሁሉ ታውቁታላችሁ ...አዎ አንድ ሁለት ብላችሁ ቆጥራችሁት ሳይሆን ደመነፍሳችሁ የሰፈረው ስፍር የለካው ልኬት አለ !

ነፍስ ሲናበብ የፍቅረኛችሁ ትንፋሽ ይለካል .... በፍቅር ስርቅርቅ ስትሉ ያፈቀራችሁት ሰው... ነፍሱ ሳይቀር ስንት ግራም እንደሆነ ሹክ የሚላችሁ መንፈስ አለ ! የስልጣኔ ትልቁ ቁሽት ይህን የእኔነት ስሜት ይቀማናል የምናቅፋት ሴት የብዙ ...እኛም የእልፍ ሴቶች ንብረት የመሆን ስሜት ውስጥእንገባለን ! መንገደኞች ከሆንን ውስጣችን ስም ያላት ምስል ያላት ጠረን ያላት ሴት ሳትሆን ማንም ትሁን ማን ‹‹ሴት ›› ብቻ ትቀራለች ! ጠረኗ ዲዮድራን እና ሽቶ የሆነ ...ያንን የተጠቀመችውን ዲዮድራን ት የተጠቀሙ ሴቶች ሁሉ የሚጋሩት ጠረን ... ስለዚህ ተመሳሳይ ጠረን ያላቸው ሴቶች ከአንድ ሱቅ ተመሳሳይ ሽቶ ስለገዙ ብቻ አንድ ይሆኑብናል ...‹‹ሴት ያው ሴት ነው›› ይላል አይምሮህ ! አንድ አይነት ወሬ ያላቸው ወንዶች አንድ ዩኒቨርስቲ ጠፍጥፎ የሰራቸው አንድ ሚዲያ አንድ አይነት ዜና አንድ አይነት ድምፅ ያስቀመጠባቸው ... ‹‹ወንድ ያው ወንድ ነው ›› ይላል አይምሮ ...ማንም ቢያቅፈን ግድ አይሰጠንም ... መነካካቱ አደንዝዞን መተሸሸቱ አደንዝዞን ቃላችን ኳኳታ አብሮነታችን ድካም ሁኖብናል ! አንድ እይታ በስሜት የሚንጠን እኛ ...ደንዝዘን ስንቱ ትዳር አፈር ድቤ በላ ! ጭረት የለሽ ስእል ልሙጥ ነፍስ አሸክሞን ከተሜነቱ ! ስልጣኔ ....ያለችንን እኛነት እንደብቅል ዘቅዝቆ አራግፎን !

እነዚህ የስሜት ጭረቶች የነፍስ መስመሮች ካልተገጣጠሙና ውስጣችን ካልተጠራቀሙ ደግሞ ውበት እና የወሲብ ስሜት እንጅ ፍቅር አይገነቡም ! ሰዓሊ ጓደኛየ እያሱ እንደነገረኝ ‹‹ማንም ሰአሊ ስእል አይደለም የሚሰው ... ጭረት ነው ሸራው ላይ የሚያስቀምጠው መስመር ነው የሚዘራው እይታውን እንደዝናብ እያጠጣ በምናቡ እንደመስኖ እያረሰረሰ ጭረትና መስመሮቹን ሲያሳድጋቸው ራሳቸው የሆነ ምስል ይከስታሉ ....ሰውም ይሁን ቁሳቁስ የሚሊየን ጭረቶች ውጤት ነው !›› እውነቱን ነው ! መልክ ከመልክ የሚለየው በጥቃቅን ጭረቶቻችን ነው ! ...ስሜትም ጭረቶች የገነቡት መስመር... መስመሮች ያዋቀሩት ምስል ነው ! የድምፅ ጭረት አለ የምስል ጭረት አለ የጠረን ጭረት አለ የመንፈስ ጭረት አለ .... ይሄ አይምሯችን ይሄን ሁሉ ጉድ እንዴት ባንድ ላይ እንደሚመዘግበው የፈጠረው ይወቅ ! ቃል ደካማ ነው ምን ይገልፃል ....

እ.....ና ይሄውላችሁ እቤቴ ስትመጡ ግድግዳየ ላይ አራት ትንንሽ የፎቶ ፍሬሞች ተሰቅለዋል... ፍሬሞቹ ውስጥ አራት አፎች አሉ ...ሊያን እያንዳንዱን ፊደል እያስባልኩ ፎቶ አንስቻት እኮ ነው ! ኦ...ራ...ይ...ት ይሆናል ይሄ የፊደል ጭረት ተደማምሮ መስር ሲሆን ....

ኦ
‹‹ኦ›› ኦራይት የሚለው ቃል የመጀመሪያ ድምፅ ነው ! ሊያየ ‹ኦ › ስትል ቀይና ወፈር ያለ ከንፈሯ ሰብሰብ... ሞጥሞጥ ይልና እንዴት እንዳመሳሰልኩት እንጃ እንጅ ...የወዳጅ ጉርሻ መስሎ ፊቴ ይደቀናል ! ስትር ያለ በደንብ የተጠቀለለ ቀይ የዶሮ ፍትፍት ጉርሻ ይ መ ስ ላ ል ! ‹ኦ› ስትል የግንባሯ ቆዳ ወደላይ ሰብሰብ ይልና አይኖቿ ፈጠጥ ይላሉ ...እና ድምፁ ደግሞ ትንሽ ጎተት ይላል ...የሊያ ከንፈር ከሌሎች ከንፈሮች የሚለየው ‹ኦ› ን በመጥራት የተለየ ቅርፅ ስለሚይዝ ነው የ ተ ለ የ!

ብዙ ሰወች ‹‹የአንጀሊና ጆሊ ከንፈር ያምራል ›› ይላሉ ...አንጀሊና ብዙ ፊልሞቿ ላይ ‹‹ ኦራይት ›› ስትል ‹ኦ› ላይ በሪሞት ኮንትሮል እያቆምኩ ከንፈሯን ከተለያየ አቅጣጫ አጥንቸዋለሁ .....ምን ያደርጋል የሊያ ከንፈር ላይ እግሩ ስር አይደርስም !! (ከንፈር እግር አለው እንዴ ...ያው እግር እስኪቀጥን ያንከራትታል እንጅ እሱማ እግር የለውም) ሊያየ ‹ኦ› ን በጠራች ቁጥር ኦ ላይ በከንፈሬ አቋርጣታለሁ ...ከዛ ከንፈሯን በመዳፏ ጠርጋና

ወደኋላ ገፋ አድርጋኝ ..‹‹ ራይት ›› የሚሉትን ፊደላት ትጨርሳቸዋለች (ይሄ ትትትትትንሽ ግነት አለበት ሂሂ) በርግጥ ቤታችን ከሆንን እንኳን ‹‹ኦ›› ‹‹..ጨ ›› ብትልም ኦ ያለች ነው የሚመስለኝ !

ራ

ሊያ ከ ‹‹ኦ›› ወደ ‹‹ራ›› ስትሻገር ድንገት ሰብሰብ ያለው ከንፈሯ እንደርችት ይበተንና ከንፈሮቿ ግራና ቀኝ ሸሸት ብለው አፏ በመጠኑ ከፈት ይላል ...የታችኛው ከንፈሯ ጠልጠል ብሎ የላይኛው ከንፈሯ የሚያምር የግማሽ ክብ ቅርፅ ይይዛል ! የምላሷ ጫፍ የታችኛው ጥርሷን ነካ አድረጎ ይቆማል ‹‹ራ›› ደምፅ አለው ከኦ ድምፅ እንደ ማስቲካ የሚለጠጥ ...ኦርርርርርርራ....አቤት ከንፈሮቿ ከፈት ብለው ጥርሶቿ በመጠኑ ሲታዩ ሊያ ፊት መቀመጥ ፈተና ነው ....ያው ራ ላይም አቋርጣታለሁ !!

ይ

ይ ስትል ከንፈሮቿ ወደግራና ቀኝ ልጥጥ ይላለ የላይኛው ጥርሷ በደንብ ይታያል ....ከንፈሮቿ ሲለጠጡ ስስ ይመስላሉ ቅድም ኦ ላይ ሙጥሙጥ ያለ ጉርሻ የሰራው ከንፈር አይመስልም ! ይ ስትል የበለጠ የሚያምረው የታችኛው ከንፈሯ ነው ! በጣም ይቀላል ! ደም የቋጠረ ይመስላል !

ት

ግርም የሚለኝ የሊያ ‹‹ት›› ነው ! በምኗ እንደምትጠራው እግዜር ይወቅ ! ብዙ ቀን በትኩረት አፏን አየሁት ከንፈሯን አጠናሁ ፎቶም አነሳኋት ...ግን ‹‹ት››ን በከንፈሯ ትጥራው ..በጥርሷ ትበለው በምላሷ ታዚመው አላውቅም ...እኔ ‹‹ት›› ስል ምላሴና የላይኛው ትናጋየ ተጋጭቶ ነው ፊደሉ የሚፈጠረው ሊያ ግን እንጃ !

አንድ ቀን
‹‹ሊያየ ›› አልኳት
‹‹ወይየ ››
‹‹ት›› ን የምትፈጥሪያት የት ነው
‹‹ኦራይት ስል ‹‹ት›› ኦሚት ስለምትሆንብኝ ነው ›› አለችኝ ! ‹‹ኦሚት›› ስትል አሁንም ‹‹ት›› አመለጠችኝ ...ላጣራ በጣም ተጠግቻት ‹‹ት ት ት ት ት ት ›› ሳስብላት ሳላስበው በጣም ተጠግቻት ነው መሰል ሁሉን ነገር ‹ት›ተነው ወደጉዳያችን !!! ድሮስ በዚህ ርቀት በዚህ ቅርርብ ያውም የሚከጃጀሉ ልጆች መሃል .....አማርኛ ይጠናል ? ግን እንኳንም አጠናን !! ተሳስመን ተሳስመን ተሳስመን ከንፈሯን ነከስኳት መሰል ...‹‹ ሶሪ ነከስኩሽ ›› አልኳት

‹‹ አም ኦ ራ ይ ት ›› አለችኝ ሙትት ባለ ድምፅ !!

አማርኛ ለዘላለም ትኑር በተለይ ‹‹ት ›› !! ጥርስ ላይ ትፈጠር ትናጋ ላይ ከፈለገች ለምን የእግር አውራ ጣት ላይ አትፈጠርም .....የትስ ብትፈጠር ምናገባኝ ! ! አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የቋነቋና ስነ ምንትስ የትምህርት ክፍል ምን ሰርቶ ይብላ !?

ይቀጥላል

በፍቅር ደብዳቤ የተገረሰሰው ዙፋን ¡
ለአዲስ ጉዳይ መፅሄት የተፃፈ
(አሌክስ አብርሃም)

‹‹ .... ጓዶች ይሄን የበሰበሰ ዙፋን አናታችን ላይ ተሸክመን ነገ ዛሬ ማለት የለብንም !! ›› አሉ ጓድ መንግስቱ ሃይለማሪያም አይናቸው ቡብስጭት እየተንቀለቀለ . . . በዚህ ጉዳይ የደርጉ አባላት ፈራ ተባ ስላሉ ጓድ መንግስቱ ደማቸው ፈልቶ ነበር
‹‹ ጓድ መንግስቱ ! መረጋጋት አለብህ አሮጌ ቤት ስታፈርስ ተደርምሶ ሊጫንህም እንደሚችል ማሰብ ደግ ነው ...ደርሶ ምሰሶውን መጎተት ምንድን ነው ›› አሉ በእድሜ በሰል ያሉ የደርግ አባል ... የኮሮኔል መአረግ ስላላቸው ወታደራዊ ግልፍታ ምን እንደሚያስከትል ያውቁታል ....!

‹‹ ይጫነና ! አፍርሰነው እንፍረስ .... ቀሪው ትውልድ በእኛ ሬሳ ላይ ተረማምዶ ነፃ እና የሰለጠነች ኢትዮጲያን ይፍጠር ›› አሉ ጓድ መንግስቱ ከበፊቱ የበለጠ ተቆጥተው ጠረንቤዛውን በቡጢ እየወገሩ . . .

የተሰበሰቡባት ክፍል በጭንቀት ልትፈነዳ ሆነ ። የደርጉ አባላት ይሄን ጥቁር ወጣት ቀልባቸው ፈርቶታል ። ተው ብለው አይናገሩ ነገር በዚህ አካሄዱ ነገ ጧት ወደስብሰባው አዳራሽ ታንክ ይዞ ከመምጣት የማይመለስ ጉድ ነው ። ዝም አይሉ ነገር ያሳደጓቸውን ያስተማሯቸውን ህዝቡ ሁሉ ከማክበር አልፎ የሚያመልካቸውን ንጉስ ነገውኑ ከዙፋናቸው ላይ ጎትተን እናውርዳቸው እያለ ነው . . . አጣብቂኝ !

‹‹ ምንም ውጣ ውረድ የለውም ሽማግሌው አብቅቶለታል ቀጥ ብለን ገብተን በቃህ ማለት ነው ›› አሉ ጓድ መንግስቱ
‹‹ ማ...ንን ..ጃንሆይን ?›› አለ አንዱ በድንጋጤ አማትቦ
‹‹ አዎ ! ››
‹‹ አባባ ጃንሆይን ?››
‹‹ ምን ነካህ ጓድ አዎ አልኩህኮ ! ››
‹‹ እኮ.....ቀ...ቀ.....ቀዳማዊ ኃይለስላሴ ንጉስሰ ነግስ.....? ››
‹‹ እችን ይወዳል መንጌ ... ዝጋ ! የምን ስም ማንዘላዘል ነው ....›› አሉና ጠያቂው ላይ አፈጠጡበት . . . እንደገና አማትቦ አቀረቀረ

በፍርሃትና ጭንቀት በታፈነው አዳራሽ ውይይቱ ቀጠለ ...አንዳንዶቹ ‹‹የንጉሱ መውረጃ ጊዜ አሁን አይደለም ትንሽ እንረጋጋ ›› ሲሉ ሌሎቹ ‹‹ እንደው ንጉሱ ባይወርዱስ አድባር ናቸው ፣ ዋርካ ናቸው ውረዱ ብንላቸው እርግማናቸውም መንፈቅ አያከርመን ....ዝም ብለው ለወጉ ይቀመጡና ደርጉ ስልጣኑን ይዞ አገር ይምራ ››
‹‹ ጓዶች የግማሽ ክፍለዘመን ዙፋን ከነስንክሳሩ አናታችን ላይ ተሸክመን እንኳን ለአመታት የዛገ ስልጣን ላይ ቀርቶ መርከብ ላይ ብንቆም ስንዝር አንርቅም ! እኛንም አገራችንንም ተጭኖ ነው የሚያሰምጠን ›› ሲሉ ጓድ መንግስቱ ተናገሩ !

‹‹ የለም የለም ጓድ ይሄ ፈጥነን እንድንደርስ ብሎ የጫነንን መኪና ሹፌር ከመግደል አይተናነስም ...ሹፌሩ ነው ጉድጓዱን የሚያየው ገደሉን የሚመለከተው ....ረጋ ብሎ ይንዳው ግዴለህም ›› አሉ አንድ አባል ።

ደርጉ በዚህ ጉዳይ አንድ ቀን ከግማሽ ሲከራከር ዋለና ንጉሱ መውረዳቸው ላይ እያቅማማም ቢሆን ተስማማ ።
ቃለ ጉባኤ ፀሃፊው
እያቅማማን
ተስማማን ! ብሎ ፃፈ ። (አብዮት ከፈነዳ በኋላ ይህ ሰው በወሳኝ ሰብሰባ ላይ ግጥም በመፃፍ ተከሶ ተረሽኗል)

‹‹ ጓዶች እኔም ቆራጥ የኢትዮጲያ ወንድሞቹ ጋር እንደተሰበሰብኩ ከጅማሬው ቀልቤ ነግሮኛል ›› አሉና ጓድ መንግስቱ ሽንጎውን አሞካሹት ። የተሞካሸው ሽንጎ ደረቱን ነፋ ትከሻውን ሰፋ አድርጎ ለዋናው ውሳኔ ተዘጋጀ
‹‹ ጃንሆይ እንዴት ይውረዱ ? ›› ዋናው ጥያቄ ፈነዳ ። ዝምምምምም!
‹‹ ህዝቡ ጠልቶሃል አገር ምድሩን በኋላ ቀርነት ፣ በእርሃብ ፣ በባርነትና በፍትህ እጦት አጎሳቅለኸዋል በቃህ ቦታህን ለተረኛው ልቀቅ ›› ብሎ መንገር ነዋ !! ›› አሉ ጓድ መንግስቱ
‹‹ ኧረ ጓድ ቀስ ... የቤት ሰራተኛ እንኳን ስትባረር ስርአት አለው እንኳን ይሄን ያህል ዘመን የመራ ንጉስ ››

‹‹ እና እነዴት እናውርደው ? ሃሳብ አምጡ ›› አሉ ጓድ መንግስቱ ወንበራቸው ላይ እየተቁነጠነጡ ይሄ ደረቅ ወንበር አልተመቻቸውም ‹‹ መደገፊያ ያለው ባለስፖንጅ ወንበር ቢገኝ . . . አለ አይደል እንደዙፋን ያለ ነገር ›› ብለው አሰቡና በውስጣቸው ፈገግ አሉ !

‹‹ ባይሆን በደብዳቤ ፅፈን እንላክላቸውና መልስ ብንጠብቅ ›› አለ ያማተበው ወታደር
‹‹ የባሰው መ.....ጣ !›› አሉ ጓድ መንግስቱ ..... አሁን የእውነትም የግርምት ሳቅ ፊታቸው ላይ ላጭር ጊዜ ፍንትው ብሎ ነበር ...‹‹ ንጉስ ሆይ ዙፋንወትን እንዲለቁና ‹ለቅቄላችኋለሁ ኑ › ብለው እንዲጠሩን አራተኛ ተሰብስበን እየጠበቅነዎት ነው ›› ብለን ደብዳቤ እንላክና መልስ እንጠብቅ ...? ጓዶች ወይ የስብሰባው መርዘም እንቅልፍ ለቆብን እየቃዣን ከሆነ እስቲ ወጥተን ንፋስ እንቀበልና እንመለስ ›› አሉ

‹‹ ኧረ ምን ንፋስ አለ ጓድ ? ድፍን አገሩ ታፍኖ እንኳን በኮሚቴ በግለሰብም የሚተነፈስ አየር የለም ›› አለ ሌላኛው ... አዳራሹን ሳቅ ሞላው ...በእርግጥም ከተማው በተማሪ አመፅ በወታደሮች የደመወዝ ጥያቄ በደርጉ ሹክሹክታ ታፍኖ ነበር ።

በመጨረሻም ደርጉ ኮሚቴ እንዲመረጥና ለንጉሱ ውሳኔውን በፅሁፍ እንዲያሰማ ወስኖ ፅሁፉ ...ሲዘረዝና ሲደለዝ አምሽቶ ግሩም የሆነና ለንጉሱ የሚመጥን ታሪካዊ ንግግር ተዘጋጀ ። ለንጉሱ መልእክቱን የሚያደርስ ኮሚቴ ተቋቋመ ። ቀጥሎ ደብዳቤውን ንጉሱ ፊት የሚያነብ ድምፁ የሚያምር የኮሚቴ አባል ለመምረጥ ደብዳቤው እየዞረ ተራ በተራ ሁሉም እንዲያነቡ ተወሰነ ። የመጀመሪያው ሰውየ ደብዳቤው ሲሰጠው
‹‹ ምን ላርገው ›› ሲል ጠየቀ
‹‹ አንብበዋ ››
‹‹ ማንበብና መጣፍ አልችልም ጓዶች ! እኔ የገበሬ ልጅ ... ኋላም ለእናት አገሬ በዱር በጫካ ስንከራተት የኖርኩ ወታደር ነኝ ›› ሲል አስተዛዝኖ ተናገረ (በእርግጥ ይህ ሰው የኋላ ኋላ ጋዜጣ ሲያነብ ተገኝቶ አቢዮቱን በመዋሸት በሚል እንደተረሸነ የታሪክ ድርሳናት ያትታሉ)

ቀጣዩ ሰው ሰው ፅኑ የእይታ ችግር እንዳለበትና መነፅሩን ረስቶ መምጣቱን በመናገሩ ታለፈ .... በመጨረሻም አንድ ቆፍጣና ወጣት ‹‹ ፅሁፉን ወዲህ በሉት›› ብሎ ሲያንበለብለው ሁሉም ደስ አላቸው ‹‹ በቃ አንተ አንብበው ›› ተባለ ። ሲያጠናው እንዲያድር ስለተነገረው ደብዳቤውን ይዞ ወደ ማደሪያው ሄደ።

በቀጣዩ ቀን ኮሚቴው ወደቤት - መንግስት መንገድ እንደጀመረ አንባቢው ወጣት እነዲህ ሲል ኮሚቴውን ጠየቀ
‹‹ ጓዶች ለድፍረት እዚች ማንአህሎሽ ግሮሰሪ ገባ ብለን አንድ ሁለት ብለን ብንሄድስ ?››
‹‹ የተቀደሰ ሃሳብ›› አለ የተጨነቀው ኮሚቴ ... ኮሚቴው ወደግሮሰሪው ገባ አለና ለሰላሳ ደይቃ ያህል በቁሙ ጠንከር ያለ መጠጥ ቀማምሶ ድፍረት በድፍረት ሁኖ ወደቤተመንግስት ገሰገሰ . . . ንጉሱ ፊትም ሳተና ሁኖ በመቆም የተመረጠው ወጣት ደብዳቤውን መዝረጥ አድርጎ ከኪሱ በማውጣት ማንበብ ጀመረ

‹‹ ሰላም ከፀሃይ ለደመቁ አይኖችሽ ... ሰላም የሃር ጉንጉን ለመሰለ ፀጉርሽ ... ሰላም እንደወፍ ለሚስረቀረቅ ድምፅሽ ... ሰላም እንደሚሳኤል ለተቀሰሩ ጡቶችሽ . . . አንች የውቦች ውብ የአለም ልእልት ...›› እያለ ማንበብ ጀመረ ። ጃንሆይ ግራ በመጋባት

‹‹ እኛን ነው ? ›› ሲሉ ጠየቁ ።

ኋላም ፊታቸው ቁሞ እንደዳዊት ደብዳቤውን የሚደግመውን ወጣት በጥሞና አደመጡና

‹‹ ምድረ ወታደር ሊገለብጠን ነው ስንል ለካስ ልጃችንን ውቢን ልእልት ለጋብቻ ሊጠይቅ ነው ተንጋግቶ የመጣው ›› ሲሉ ዙፋናቸው ላይ ተመቻችተው ፈገግ አሉ . . . አንባቢው ወታደር ግን ከጎኑ በቆመ ሌላ ወታደር ክንድ ሲጎሸም ደንግጦ ወረቀቱን ወደአይኑ ጠጋ አድርጎ ተመለከተው ... ላፊቀራት ቆንጆ የፃፈውን ደብዳቤ ነበር አላውጦ ከኪሱ በማውጣት በሞቅታ ያንበለበለው ! ንጉሱ በአክብሮት ነበረ ከዙፋናቸው የተነሱት . . . .መልሰው ዙፋናቸው ላይ አልተቀመጡም .... !

የንጉሱ ፀጉር አስተካካይ የነበሩት ጋሽ አፍለኛው እንደሚሉት ከሆነ ግን ንጉሱ ወደሰማይ እያዩ ተራግመዋል ‹‹ በፍቅር እንዳታለላችሁን ፍቅር ይንሳችሁ ... ያባላችሁ ያናጫችሁ ››ብለው

አንዳንድ የራስ ተፈሪያን እምነት አራማጆች ታዲያ እስከዛሬ ድረስ ‹‹ የኛ ንጉስ በፍቅር ደብዳቤ እንጅ በደርግ ማስፈራሪያ አይደለም ከዙፋናቸው የወረዱት ›› እያሉ ሲናገሩ ይደመጣሉ ።ስለፍቅር ደግሞ እንኳን እሳቸው ክርስቶስም ከሰማይ ወርዷል እንደማለት የጀማይካ ህፃናት መዝሙር ሁሉ አላቸው
‹‹ጃ ፍቅር እንጅ አይፈሩም ጠመንጃ !››

አንዲት ቃል !
(አሌክስ አብርሃም)

ለጠየቁኝ ሰወች ሁሉ ሊያን ያፈቀርኩበትን ምክንያት ስነግራቸው የምቀልድ ይመስላቸዋል !እኔ ግን ከልቤ ነው ! ለምንድነው ሰው ሁሉ ራሱ በተያዘበት ወጥመድ ሌላ ሰው ካልገባ በስተቀር ከእርሱ ውጭ ሌላው የተጠመደ የማይመስለው ! ? ሊያን አፈቅራታለሁ ያውም ሁለት አመት ሙሉ የገባችበት ጉብቻ ነው ያፈቀርኳት ! እርሷም ታፈቅረኛለች (እና ባታፈቅረኝ . . . .) ብቻ ብዙ ነገሯን አሳልፋ ሰጥታኛለች ተቀብያለሁ !

የግቢው ተማሪ ሁሉ ሊያን ያፈቀርኳት የሃብታም ልጅ ስለሆነች ይመስላቸዋል ....በእርግጥ የሃብታም ልጅ ናት ቤተሰቦቿ ((ከተማ)) አላቸው (ምን ልበል ታዲያ) ነዳጅ ማደያ ጋራዥ ሆቴል ካፍቴሪያ የቆዳ ጫማ ፋብሪካ ወርቅ ቤት ሱፐርማርኬት ግሮሰሪ የጤና ሳይንስ ኮሌጅ የመኪና ማከራያ ይሄ ሁሉ አላቸው .....እኔስ

ምን አለኝ ...እግዜሩ ብቻ ! ላአከአምላክ የሚባል ዲያቆን ወዳጀ ይሄን ብነግረው ‹‹ ብቻ አይባልም ወዳጀ አብርሃም .....እነሱ ከተማ አላቸው አንተ ደግሞ የአለም ጌታ አለህ በቃ ሁሉ አለህ ....›› አለኝ !ተፅናናሁ !

ጓደኞቸ ሁሉ ‹‹አብርሃም ባንክ ጠበሰ ›› እያሉ ያሙኛል ....ኧረ ፊት ለፊትም እንደዛ ነው የሚሉኝ ...ቸሩ መዳኒያለም ያውቀዋል ሊያ ከተዋወቅንበት ቀን ጀምሮ ሰባራ ሳንቲም አውጥታ አታውቅም ! እግዜር ይባርካት የፈለገ ትልቅ ሆቴል ብትገባ ከቡናና ከሽሮ ውጭ አታዝም ! ቢሆንም ሊያየ የኔ ‹‹ ንግድ ባንክ ›› ብር አታስወጣኝም ! ታውቀዋለች ጎኔን ! ደግሞም የምር ሃብታሞች ብር አይደንቃቸውም ! ሰው ነው ረሃባቸው ! እናም እኔን ጥግብ እስክትለኝ እንዳሻት እንድታደርገኝ ፈቀድኩላት እነዳሻትም አ,ረገችኝ

ድፍን የዩኒቨርስቲው ተማሪስ አኔና ሊያ በመፋቀራችን ምን አስገረመው ብለን ብንጠይቅ ...‹‹የሊያ ሰውነት›› የሚል መልስ ነው የምናገኘው . . . ሊያ ‹‹ትንሽ ደልደል›› ያለች ናት...እኔ ብቻ ነኝ‹‹ ደልደል ያለች›› የምላት ...ሌላው ሰው አገር ናት ይላታል ....ዝግባ ነው የምታክለው ይላታል .....እንደአብርሃም አይነት ሰባት ሚስኪኖች እንደችቦ ባንድ ላይ ታስረው ታክላለች ይሏታል ....የኛ ሰው ስም ለመለጠፍ ማን ብሎት ! ዋናውን ስም አጣርቶ ሳያውቀው እኮ ነው ቅፅል ለመቀጠል የሚሮጠው !

እና እንደነገርኳችሁ ሊያየ ደልደል ያለች ልጅ ነች ...ሰማኒያ ሰባት ኪሎ ብቻ ! ግን ሰማኒያ ሰባት ብቻ መሆኗ ይገርመኛል ... እኔ መጀመሪያ ‹‹አብርሃም ባንክ ጠበሰ›› ሲሉ በግንዘቧ ሳይሆን በሰውነቷ ቅርፅ መስሎኝ ነበር ...ክብ ናት
ልክ እዚህ ሰንጋ ተራ እንዳለው ወርቃማው ባንክ ቤት! በእርግጥ ማጋነን ይመስላል ግን በሁለት እጆቸ ሳቅፋት እጀን ከኋላዋ ማነካካት አልችልም (እጅ ያጥረኛል) እንደምንም እጆቸን ለማገናኘት ስሞክር በጭንቀት እየተነፈሰች ‹‹አንተ ጨመከኝ ›› ትለኛለች ! የኔ ቆንጆ ! እኔን ይጭመቀኝ ብየ እጀን ትከሻዋ ላይ ብቻ ጣል አደርገዋለሁ ! የማይናወጥ ተራራ የተደገፍኩ ይመስለኛል ለስላሳ ተራራ ከወደአናቱ የፍቅር ምንጭ የሚንፎለፎልበት

የሊያ ውፍረት በህመም ወይም በሌላ ምክንያት አይደለም መረሳት ነው ! በቃ ቤተሰቦቿ ቢዝነስ ሲያሯሩጡ ረሷት ...ያገኘችውን ስትበላ ‹‹ኧረ ቀስ ››የሚል ዘመድ ጠፋ ....እንደውም ወንድሞቿ ባዶ እጃቸውን እቤት አይገቡም አንዱ ቸኮሌት አንዱ የታሸገ ምግብ ነገር ሌላው ሌላ... ሊያየ የኔ ውድ ሪሞቷን ይዛ ሶፋዋ ላይ ቁጭ ትልና ፊቷ የተከመረውን የምግብ ተራራ ታወድመዋለች ! ‹‹አንበጣ ነበርኩ ›› ትለኛለች ስታወራኝ ...ጥሩው ነገር ማንም ምንም ይበል መንገደኛው ሁሉ አንገቱን እየቆለመመ በግርምት ሲመልከታት ሊያ ሲበዛ በራሷ የምትተማመን ውፍረቷ የማያሳቅቃት ልጅ ነበረች !

ሊያን ለመጀመሪያ ጊዜ ያስተዋወኳት ለአጎቴ ነበር ‹‹ዛላዋ ከበድ ያለች ጓደኛ መያዝህ ጥሩ ነው ...ብቻህን ውልብ ውልብ ከማለት እንዲህ ጥላዋ ሲያርፍብህ አንተም ከበድ ትላለህ ›› ብሎ መረቀልኝ ! ቀጥየ ለእናቴ አስተዋወኳት እናቴ በጣም ወደደቻት ! ምክንያቱን ግን አልነገረችኝም ! ሊያም እናቴን ከልቧ ነበር የወደደቻት ‹‹ ምናልባት የእናቴ ቡናና ሽሮ ከአፍሪካ አንደኛ ከአለምም አንደኛ ስለሆነ ይሆናል ! ›› ስላት ሊያየ ‹‹ጉረኛ ›› ትለኛለች !

ሊያን እንዴት ለፍቅረኝነት እንደጠየኳት ነገርኳችሁ እንዴ ? ያው ቅኔ ተዘራርፈን ነው ....ጓደኞች ነበርን እኔ ግን ፍቅር ጀማምሮኛል ሲመስለኝ እርሷም ጉብቷታል ...ታዲያ አንድ ቀን ካፌ ውስጥ ተቀምጠን ቡና ስንጠጣ....ዝናብ እየዘነበ ነበር ...እኔ ደግሞ በቲሸርት ብቻ ብርድ እያጫወለኝ ኩርምት ብየ ቡናየን ቶሎ ቶሎ እጠጣለሁ
‹‹ በረደህ አይደል ›› አለችን ድምጿ ውስጥ ርህራሄ ነበር
‹‹ በጣም ››
‹‹ እንደኛ ደልደል ብትል ኖሮ ብርድ አይደፍርህም ነበር ሃሃሃሃ›› ተሳሳቅን ...ስትናገር ትከሻዋን ከፍ አድርጋ በቀልድ ጉራ ነበር
‹‹ እኔ የምልህ አብርሽ አንድ ሰባት ኪሎ ስጋ ላውስህ እንዴ ለብርዱ ›› አለች ክንዷ ላይ ያለውን ትርፍ ስጋ

ቆንጥጣ አንድ እጇን እንደቢላዋ እየመተረች (እየው እንግዲህ ኢላማውን የመታ ተኩስ የሆነ ምላሽን)

(((((‹‹ አይ ሊያየ ስጋ ማንም ይሰጣል ነፍስ የሚያበድረን ነው ያጣነው ...››)))) ፓፓፓፓፓፓፓፓፓ አንዳንዴ የራሴ ንግግር ይጥመኛል ! በቃ ባለቅኔስ ከዚህ በላይ ምን ሊናገር ይችላል ....አሪፍ ቅኔ ማለት ሰው ሊለው የሚፈልገውን በየትኛውም መንገድ በትክክለኛው ሰላት ማለት መቻሉ አይደል ! መፅሃፉም ይላል ‹‹በወቅቱ የተወረወረች ቃል ምንኛ መልካም ናት ››

ሊያ ፊት ላይ ሃፍረት አይሉት ደስታ አይሉት ፍርሃት አይሉት አንጃበበ ‹‹ በስርአት ማስቀመጥ ከቻልክ ›› ብላኝ እርፍ !ከዛ ዝምታ ቡናዋን ስታነሳ እጇ ትንሽ የተንቀጠቀጠ መሰለኝ . . . በቃ ይሄው ነው ....ሌላ ቀን ቅኔ ሳይዘረፍ የዙሪያ ሳይኬድ እንደው ተጠጋግተን እንደተቀመጥን ...የእኔ የራሴ ከንፈር ጠፍቶብኝ ‹‹አሁን እዚህ አልነበር እንዴ የት ሄደ ›› ብየ ስፈልግ ከንፈሬ ሊያ ከንፈር ላይ ተገኘ !!

ስንሳሳም በሃፍረት እየሳቀች (ሳቋ ራሱ ደልደል ያለ ነው) እንዲህ አለችኝ ‹‹ አንተ እንደ ውሃ ተነንኩ መሰል ሰውነቴ ቀለለኝ ›› ሃሃሃሃሃ የኔ ሊያ እኔ ግን ሰውነቴ ከበደኝ አጎቴ እንዳለው ጥላዋ አረፈብኝ መሰል .... ‹‹አይዞሽ የኔ ቆንጆ ገና ሽንቅጥቅጥ እስከምትይ ነው የምናተነው ››

ግን ሊያን ከመሳሜ ...ከመጠየቄ ...ከመቅረቤ በፊት ...ለምን የወደድኳት ይመስላችኋል ....አይኗ ....አፍንጫዋ ... ጥረሷ.....ሁሉም አይደለም ‹‹ ቃሏ ››...አንድ ቃል ብቻ አለች ሊያ ላይ ብቻ የምታምር እንግሊዝኛ ቃል ....ለነገሩ ይች ቃል አማርኛ ከመሰለችኝ ቆይታለች ....እና በዛች ቃል ምክንያት ሊያን ማየት ሱስ ሆነብን ...አልቀለድኩም !!

ይቀጥላል

እርቃን ጭንቅላቶች አይወክሉንም !!

(አሌክስ አብርሃም)

ባለፈው አንዲት ትዳርና እርግዝናን ተገን በማድረግ ‹‹ የመታየት ሱሷን ›› ለማርካት ፍዳዋን ስለምታይ ልጅ አንስተን የከበረውን እናትነት አረከሰችው ብለን ነበር ...አንዳንድ በጎ አሳቢ አስተያየት ሰጭወች ‹‹ስልኳ ተሰርቆባት እንጅ እርሷ ያንን ፎቶ አለጠፈችም ›› በማለት ተከራክረዋል .... ይሁንና ትላንትም ስለእርሷ መወራቱ ቀዝቀዝ ስላለ እንደገና እንድናወራላት ያንኑ ርቃኗን እራሷ ፔጅ ላይ ለጥፋልናለች (እንደገና ስልኳ ተሰርቆባት ይሆናል)

ይህ ‹‹ምን ታመጣላችሁ›› አይነት መደዴነት የልጅቱን ለአቅመ እናትነት አለመድረስና . . .አጠቃላይ በዛ እርሷ

በተሰማራችበት ሙያ ውስጥ ያሉ መሰሎቿ ምናይነት አስተሳሰብ ላይ እንዳሉ የሚያሳይ ድርጊት ነው ! ይህ የምትመለከቱት ምስል ደግሞ የባህል አልባሳቶቻችንን ‹‹በዘመናዊ መንገድ ›› በመስራት ለስራ ምቹ ለማድረግ በ‹‹እውቅ›› የልብስ ዲዛየነሮቻችን የተዘጋጀ ልብስ ነው ! ልብሱን ለብሳ የቆመችውም በ 2012 ‹‹ኢትዮጲያዊየንን እወክላለሁ›› የምትለን ቆንጆ ናት ! በአጠቃላይ ይህ አገራችን ላይ እየተከናወነ ያለው የፋሽን እና ተያያዥ ትርኪ ምርኪ (ሙያውን ለበጎ የሚያውሉትን አይጨምርም) የከሸፉ ሴቶችን መፈብረኪያ ፀያፍ ንግድ እንደሆነ በፅኑ አምናለሁ !

ግን ይች ኢትዮጲያ በቃ በሴት ርቃን ሆነ መታወቂያዋ ? በሴተኛ አዳሪነት በዝሙት የውጭ ዜጎች ስጋንም ነፍስንም በሚሸጡ ርካሽ ጥቅም በሚያሳድዱ የርካሽ ሰብእና ባለቤቶች ሆነ ለአለም የምትተዋወቀው ? ! ይህች አገር እኮ የክርስቲያኑ የሙስሊሙ የሌሎችም እምነቶች ባህልና እሴቶች አገር ናት እነዚህ መንፈሰ ጎደሎ ፍጥረቶች እንዴት ነው እኛን ወክለው ለአለም የሚያስተዋውቁን ! ?

ኢትዮጲን ወክለው በአደባባይ ህዝብ በሚያየው ሚዲያ ወሲብ የሚፈፅሙ ሴቶች እናቴን እህቴን እንዴት ነው የሚወክሉት ....በፊልም ተዋናይነት በቁንጅና ተወዳዳሪነትና በሌላም ሽፋን ‹‹የክብር ሴተኛ አዳሪነት›› ስራቸውን እየሰሩ አንቱ ሊባሉ የሚችሉ ሴቶች እንዴት ነው እኔ በሌላ መንገድ የማውቃትን አገሬን ወክለን ለአለም እናስተዋውቅ የሚሉት ... ለነገሩ አሁን ማካበድ ይመስለናል አንዱ ደባደቦ ጥቁር ለአፍሪካ ህብረት ስብሰባ ጎራ ብሎ እህትህን ከአስር ዶላር ባነሰ ዋጋ ‹‹ላወጣት እችላለሁ ›› ብሎ በሞቅታ ሲወራረድህ ግን ይገባሃል እነማን አገርህን እየወከሉ እንደሆነ !

አሁንም ቢሆን ለእነዚህ ተልካሻ ፍጥረቶች የአገር ስም አሸክመን ባንዲራ ሰጥተን እንደደህና ነገር ርቃናቸውን በአለም ፊት እንዲቆሙና ስማችንን እንዲያቆሽሹ እውቅና መስጠት የለብንም ... እዛው ራሳቸውን ወክለው ይጨማለቁ !! ነገሩ ስላበሳጨኝ ስሜታዊ ሁኘ ይሆናል.... ግን እነዚህ በአለም ዙሪያ ኢትዮጲያዊያን ሴቶችን የአለም ወንዶች የወሲብ እቃ አድርገው የሚያስተዋውቁ የጥፋት ልጆች በየአረብ አገሩ በሌላውም ህዝብ ዘንድ ሴቶቻችንን መጥፎ ስም እያሰጡ ለወሲብ ብቻ እንዲፈለጉ እያደረጉ ነው ! አለም የሚያደርገው ነገር ነው በሚል ጭፍን ዘመናዊነት ገባማ ኩረጃ ድህነት መድረሻ ያሳጣቸው እህቶቻችንን ስጋቸውን ሽጠው ማደርን እንደትልቅ አማራጭ አናመላክታቸው !!

መጠጥ ...
አደንዛዥ እፅ
የወሲብ ንግድ ያላደገው የመዝናኛ ፋሽን ኢንዳስትሪያችን ቱርፋቶች !!

አገርን በበጎ የሚያስጠሩ ‹ሞዴሎች› ከእርቃን ሰውነት ውስጥ ሳይሆን ክብር ከተጎናፀፉ ራሱንም ህዝቡንም ከሚያከብር አይምሮ ውስጥ ነው የሚወጡት !!